ሕመም ያልጣለው ፣ ችግር ያልፈታው ማንነት



ገጽ 16

ለስልጡን ከተማ እውንነት



ገጽ 14



# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

82ኛ ዓመት ቁጥር 231 ሚያዝያ 21 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጉብኝት ሀገራቱ የኢትዮጵያን ነባራዊ የሰላም ሁኔታ እንዲረዱ አስችሏል

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- የምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ የአፍሪካ ሀገራት ጉብኝት ኢትዮጵያ ከሀገራቱ ጋር ያላትን ግንኙነት ያጸናና አሁን ያለችበትን የሰላም ሁኔታ በትክክል ለማስረዳት ዕድል የፈጠረ መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን በምሥራቅ አፍሪካ የታላላቅ ሐይቆች ሀገራት ያደረጉትን የሥራ ጉብኝት፣ በኢትዮጵያ ስለተካሄደው የዓለም አቀፍ ኢንቨስትመንት ጉባኤና በሱዳን ያለውን ግጭት አስመልክቶ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ሚዲያዎች ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቷል።

ጋዜጣዊ መግለጫውን የሰጡት የውጭ ጉዳይ


የምክትል ጠቅላይ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ፎቶ፡ ፀሐይ ንጉሤ

## የአቶ ግርማ የሺጥላ የአስከሬን ሽኝት በመጪው እሑድ በአዲስ አበባ ይከናወናል

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የአቶ ግርማ የሺጥላ የአስከሬን ሽኝት በመጪው እሑድ በአዲስ አበባ እንደሚከናወን የቀብር ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አስታወቀ። የቀብር ሥነ ሥርዓቱ በወላጆቻቸው ፍላጎት እና ጥያቄ መሠረት በተወለዱበት ሰሜን ሸዋ ዞን መሐል ሜዳ እንደሚፈጸም ተገልጿል።

የቀብር አስፈጻሚ ኮሚቴው ትናንት በሰጠው መግለጫ የብልጽግና ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልና የአማራ ክልል ብልጽግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ በነበሩት በአቶ ግርማ የሺጥላ ላይ የተፈጸመው ድንገተኛ ግድያ እንዳሳዘነው በመግለጫው ገልጾ ድርጊቱ የሚወገዝ ነው ብሏል።

የሰኔ 15 የልብ ስብራት ሳይጠገን ሌላ ስብራት መከሰቱ አሳዛኝ ነው ያለው የቀብር አስፈጻሚ ኮሚቴው ወንድምን በመግደል አሸናፊ መሆን አይቻልም፤ የድል ባለቤትም አያደርግም ነው ያለው። የቀብር አስፈጻሚ ኮሚቴው ድርጊቱ የሕዝቡን ባሕል እና ሥነልቦና የማይመጥን እንደኾነም ገልጿል።

የአማራ ሕዝብ በባሕሉ መሪውን ይጠብቃል፤ ይንከባከባል፤ አልመራኝም ብሎ ሲያስብም እንዳይመራው ያደርጋል እንጂ ሰው እንዲሞት አይፈቅድም ነው ያለው የቀብር አስፈጻሚ ኮሚቴው። ድርጊቱ ሀገርንም ክልሉንም እንደሚጎዳ አብራርቷል።

ድርጊቱ ከተሰማ በኋላ የቀብር ሥነ ሥርዓቱ ከፍ ባለ ሁኔታ እንዲፈጸም የተለያዩ ኮሚቴዎች መዋቀራቸውን አስረድተዋል።

ዋናው ኮሚቴ በክልል ደረጃ መዋቀሩን የገለጸው ኮሚቴው የቀብር ቦታው በወላጆቹ ፍላጎት እና ጥያቄ መሠረት በተወለደበት ሰሜን ሸዋ ዞን መሐል ሜዳ እንዲሆን ፍላጎት በመኖሩ ሌላ ኮሚቴም እንዲዋቀር መደረጉ ነው የተገለጸው።

ቀብሩ ወደ ትውልድ ቀየው ከመሄዱ በፊት በአዲስ አበባ የሽኝት ፕሮግራም እንደሚኖር የቀብር አስፈጻሚ ኮሚቴው አስረድቷል።

የሽኝት ፕሮግራሙም በወዳጅነት አደባባይ ባልደረቦቹ፣የፌዴራል እና የክልል የሥራ ኃላፊዎች እንዲሁም ወዳጅ እና ዘመዶቹ በተገኙበት እንደሚከናወን ነው የተብራራው።

የሽኝት መርሐ ግብሩም እሑድ ሚያዝያ 22 ቀን 2015 ዓ.ም ጠዋት ከአንድ ሰዓት ጀምሮ እንደሚካሄድ ገልጾ በፕሮግራሙ ላይ ወዳጅ ዘመዶቹ እንዲገኙ ጥሪ ቀርቧል።

በመጨረሻም የቀብር አስፈጻሚ ኮሚቴው የብልጽግና ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልና የአማራ ክልል ብልጽግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ለነበሩት አቶ ግርማ የሺጥላ ፈጣሪ ነፍሳቸውን በአፀደ ገነት እንዲያሳርፍ እና ለወዳጅ ዘመድ መጽናናትን እንዲያድል ተመኝቷል።








## በትብብርና በእኩልነት መንፈስ በሚከናወኑ የልማት ሥራዎች ሀገርን ማሳደግ ይገባል

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- በትብብርና በእኩልነት መንፈስ በሚከናወኑ የልማት ሥራዎች ሀገርን ማሳደግ እንደሚገባ የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንትና የፓርቲው ጽሕፈት ቤት ዋና ኃላፊ አቶ አደም ፋራህ ተናገሩ። የትግራይን ሕዝብ ጥቅም በዘላቂነት ለማስከበር ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር በፍትሐዊነትና በጋራ ማልማት ይገባል ብሎ መንግሥት ያምናል ሲሉም ገልጸዋል።


በትብብርና በእኩልነት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## ከአንድ ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ዶላር በላይ የኢንቨስትመንት ስምምነት ተፈረመ

### - ኢንቨስት ኢትዮጵያ 2023 ፎረም ትናንት ተጠናቋል

ዘሳሰም ግዛው

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ከአንድ ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ዶላር በላይ የኢንቨስትመንት ስምምነት ከአምስት የተለያዩ ኩባንያዎች ጋር ተፈራረመ። "ኢንቨስት ኢትዮጵያ 2023 በኢትዮጵያ ኢንቨስት በማድረግ በልጽጉ-ማራኪ የኢንቨስትመንት


ከአንድ ነጥብ ስድስት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





# የሰላም ስምምነቱ ሂደቱን ጠብቆ ተግባራዊ መደረጉ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን ይረዳል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ ፡- ከሰሜኑ ጦርነት በኋላ የተፈረመው የሰላም ስምምነት ሂደቱን ጠብቆ ተግባራዊ መደረጉ እንደሀገር ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን የሚያግዝ መሆኑን የፖለቲካል ሳይንስ ምሁራን ገለጹ።

የአምቦ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህር አቶ ሰለሞን ተፈራ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሰላም ስምምነቱ ትግበራ የሀገሪቱን ሰላም ዘላቂ ለማድረግ ሚናው የጎላ ነው።

የሀገር ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ዕድገት ሊረጋገጥ የሚችለው ዘላቂ ሰላም ሲኖር ነው። የሰላም ስምምነቱ ተግባራዊ እየተደረገ መዝለቁ ዘላቂ ሰላም እንዲኖር ከማድረጉም ባሻገር ለዲፕሎማሲያዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መፋጠን እገዛ ያደርጋል ብለዋል።

በሀገሪቱ ዘላቂ ሰላም ሲፈጠር ዓለም አቀፍ የልማት አጋሮችና የውጭ ባለሀብቶች ኢንቨስት ማድረግ የሚችሉበት አጋጣሚ ይፈጠራል ያሉት አቶ ሰለሞን፣ በዚህም ሀገሪቱም ሆነች ማኅበረሰቡ በኢኮኖሚ ተጠቃሚ መሆን እንዲችሉ ያደረጋል ሲሉ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

በስምምነት ትግበራው መሠረት በትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር እንዲቋቋም መደረጉ፤ ሕወሓት ከሽብርተኝነት መዝገብ መሰረዙ፣ ሕግ የማስከበር ሥራዎች በታቀደላቸው ጊዜያት እየተከናወኑ መሆኑና ሌሎችም ርምጃዎች የሀገሪቱ አንድነት ተጠናክሮ እንዲቀጥልና ሕልውናዋ እንዲከበር ይረዳል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ሀገር ዘላቂ ሰላም ማምጣት የሚቻለው በመተባበር፣ በመወያየት፣ በመነጋገር፣ የግልን ጥቅም ባለማስቀደም እና በይቅርታ ማመን ሲቻል በመሆኑ ሁሉም ማኅበረሰብ ይህንን ተቀብሎ ለተግባራዊነቱ ጥረት ማድረግ አለበት ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የፖለቲካል ሳይንስ ምሑር ዶክተር ደጉ አስረስ



በበኩላቸው፤ የሰላም ስምምነቱ ተግባራዊነት ሀገር ተረጋግታ እንድትመራና ዘላቂ የልማት ሥራ ለማከናወን ወሳኝ ጉዳይ ነው ብለዋል።

ከሰሜኑ ጦርነት በኋላ የተደረሰው የሰላም ስምምነት ሀገሪቱ ወደ ሰላም እንድትመጣ ያደረገ ነው ያሉት ዶክተር ደጉ፤ የስምምነቱ ትግበራም የየትኛውንም ቡድን ጥቅም ያልነካ በመሆኑ ዘላቂ ሰላም እንዲፈጠር መንገድ አመላካች መሆኑን ገልጸዋል።

በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረገው የሰላም ስምምነት በሀገሪቱ ሰላም እንዲፈጠር ከማድረጉም ባለፈ ሌሎች ሸብርተኛ ቡድኖች ትጥቅ ፈትተው የልማት እንቅስቃሴ ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ በር ይከፍታል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ሰላም መምጣት የሚችለው ሁሉም የድርሻውን ሲወጣ ነው ያሉት ምሑሩ፤ መንግሥት ከሕወሓት ጋር ያደረገው ስምምነትና ከሌሎች ታጣቂ ኃይሎች ጋር የጀመራቸው ጥረቶች ሀገሪቱን ወደዘላቂ ሰላም የሚወስዱ በመሆናቸው የሚበረታታ ነው ብለዋል።

በተጨማሪም ቀሪ የሰላም ስምምነት ትግበራዎች ውጤታማ እንዲሆኑ የመገናኛ ብዙኃን፣ መላው ዜጎችና እና ሲቪክ ማኅበራት የድርሻቸውን መወጣት እንዳለባቸውም ገልጸዋል።

# በድርቅና በጎርፍ የተጎዱ ወገኖችን ለመታደግ የተደረገው ጥረት አበረታች ነው

**መክሊት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ፡- በድርቅና ጎርፍ አደጋ የተፈናቀሉ ወገኖችን ለመታደግ የተደረገው ጥረት የሚደነቅ መሆኑን የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ገለፀ። በቀጣይ ቅድመ ጥንቃቄና የፈጣን ምላሽ ሰጭነት አደረጃጀትና አሠራርን ማጠናከር ያስፈልጋል ብሏል።

የኢትዮጵያ የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ሰሞኑን ባዘጋጀው ፕሬስ ኮንፈረንስ ላይ የተቋሙ የአስተዳደር በደል መከላከል ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ አዳነ በላይ፤ ተቋሙ ለተጎጂዎች እያደረገ ያለውን ድጋፍ በተመለከተ ቁጥጥር እና ምልከታ ማካሄዱን ገልጸው፤ ጉዳት የደረሰባቸውን ወገኖች ለመታደግ የተደረገው ጥረት የሚደነቅ መሆኑን ተናግረዋል።

በቀጣይ ከዚህ በበለጠ ለሚፈጠሩ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች ቅድመ ጥንቃቄና የፈጣን ምላሽ ሰጭነት አደረጃጀትና አሠራርን ማጠናከር እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

ቁጥጥርና ምልከታ በተከናወባቸው ቦታዎች የተፈጠረው ድርቅ እና የጎርፍ አደጋ ከችግሩ ስፋትና ጥልቀት አንጻር ሲታይ ሰብዓዊና ቁሳዊ ጉዳት ለመታደግ በመንግሥት አካላት፣ በኅብረተሰቡ፣ በለጋሽ ድርጅቶችና ባለሃብቶች በኩል የተደረገው ድጋፍ ሊበረታታ እንደሚገባ ተናግረዋል።

ድርቅና የጎርፍ አደጋ በተከሰተባቸው አንዳንድ ዞኖችና ወረዳዎች ላይ ቅድመ ማስጠንቀቂያና ለኅብረተሰቡ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራዎች አለመሠራታቸውን እንደ ክፍተት አንስተዋል።



**አቶ አዳነ በላይ**

መሠረተ ልማት፣ በማኅበራዊ አገልግሎቶችና በመልሶ ማቋቋም እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎች ውስንነት ስለሚታይባቸው የሰብዓዊ ድጋፍና እርዳታ ፈጣን፣ ቀልጣፋ እና ፍትሐዊ አለመሆኑ እንዲሁም የተጎጂዎችና ተፈናቃዮችን መረጃ በፆታ፣ በአባወራ፣ በዕድሜና በአካል ጉዳት ተለይቶ አለመያዙ ጎላ ብለው የታዩ ክፍተቶች መሆናቸው በተደረገው ቁጥጥርና ምልከታ ማግኘት መቻሉን ገልጸዋል።

እየተደረገ ያለውን ድጋፍ አድንቀው፤ መልሶ የማቋቋም ሂደቱ መርሐ ግብር ተቀርጾ መጠነ ሰፊና ዘላቂነት ያለው ሥራ በሁሉም አካላት በትኩረት ሊሠራበት እንደሚገባ ጠቁመዋል።

የቁጥጥር ሥራው በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን፣ በደቡብ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን እና በሶማሌ ክልል በዳዋ ዞኖችና በተመረጡ 10 ወረዳዎች እንዲሁም በመጠለያ ጣቢያዎች ከመጋቢት 11 እስከ 25 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ መከናወኑን ተናግረዋል።

# በትግራይ ክልል ከዛሬ ጀምሮ የንግድ ባዛር ይካሄዳል

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በትግራይ ክልል ተቋርጦ የቆየውን የንግድ እንቅስቃሴ ለማስቀጠልና የተሻለ ቀጠናዊ ትስስር ለመፍጠር በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች ባዛር መዘጋጀቱን የክልሉ የንግድ ምክር ቤት ገለጸ።

የትግራይ ክልል የንግድ ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አታኽልቲ ስዩም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ትግራይ ላይ ተቋርጦ የቆየውን የንግድ እንቅስቃሴ ለማስቀጠልና የተሻለ ትስስር ለመፍጠር እየተሠራ ነው።

በዚህም የንግድ ባዛሩ በክልሉ የንግድ እንቅስቃሴ እና አጠቃላይ ቀጠናዊ ትስስርን ለማጠናከር ዓላማ አድርጎ የተዘጋጀ መሆኑን የጠቀሱት አቶ አታኽልቲ፤ በአጠቃላይ ባዛሩ በሁለት ዙር የሚደረግ መሆኑን አስረድተዋል።

የንግድ ባዛሩ ከዛሬ ጀምሮ የመጀመሪያ ዙርን በመቀሌ፣ ውቕሮ፣ ዓዲግራትና ማይጨው እንደሚያደርግ ጠቅሰው፤ ይህም ለአንድ ወር የሚቀጥል መሆኑን ተናግረዋል። ሁለተኛው ዙር ደግሞ በዓብይ ዓዲ፣ ዓድዋ፣ አክሱምና ሽረ የሚቀጥል ይሆናል ብለዋል።

እንደ አቶ አታኽልቲ ገለፃ፤ ባዛሩ ከመከፈቱ በፊት ከባለ ድርሻ አካላት በዋናነት የፌዴራል ንግድና ፋይናንስ ተቋማት ጋር ጥናታዊ ጽሑፍ ቀርቦ የፓናል ውይይት ይደረጋል። የትግራይ የፋይናንስ ተቋማት ከየት ተነስተው አሁን ምን



**አቶ አታኽልቲ ስዩም**

ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ይዳሰሳል። እንዲሁም የትግራይ ክልል ቀጠናዊ የንግድ ትስስር የሚሄድበት አቅጣጫ ለውይይት ይቀርባል።

የንግድ ባዛሩ በጦርነት ምክንያት ተቋርጦ የቆየውን የንግድ ትስስር በጥሩ ሁኔታ ለማስቀጠልና የኮንትሮባንድ ንግድ ለማስቆም እንዲሁም ነጋዴዎች ከአጋር ድርጅቶች ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ ታስቦ የተዘጋጀ እንደሆነና፤ በክልሉ ያጋጠመው የገንዘብ እጥረት ለማስተካከል ከባንኮች ጋር በመሆን ለመሥራት እንደሚያግዝ ጠቁመዋል።



አቶ ወንድወሰን ግርማ

# ዲያስፖራው በዘጠኝ ወራት ለሀገራዊ ጥሪዎች 19 ሚሊዮን ዶላር አበርክቷል

- ለሦስት ሺህ ሰዎች የሥራ ዕድል ፈጥሯል
- በስምንት ወራት 3 ነጥብ 8 ቢሊዮን ዶላር ወደ ሃገር ውስጥ ልኳል

**በዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የዲያስፖራው ማኅበረሰብ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ለሀገራዊ ፕሮጀክቶችና ወቅታዊ ሀገራዊ ጥሪዎች ከ19 ሚሊዮን ዶላር በላይ አስተዋፅዖ ማበርከቱን የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት አስታወቀ።

ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከ27 ቢሊዮን ብር በላይ ያስመዘገቡ 223 የዲያስፖራ ባለሀብቶችም ሦስት ሺህ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር እንደቻሉ ተገልጿል።

የአገልግሎቱ የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ወንድወሰን ግርማ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ዲያስፖራው ባለፉት ዘጠኝ ወራት ለሀገሩ ከፍተኛ አስተዋፅዖ በማበርከት ለሀገራዊ ፕሮጀክቶችና ወቅታዊ ሀገራዊ ጥሪዎች ከ19 ሚሊዮን ዶላር በላይ ወደ ሀገር ውስጥ ልኳል።

ዲያስፖራው በቅርብ ለተጀመረው ለገበታ ለትውልድ የቱሪዝም ፕሮጀክት 123 ሺህ ዶላር በላይ ማበርከቱን የገለጹት አቶ ወንድወሰን፤ በቦረና አካባቢ ለተከሰተው ድርቅ ከ2 ነጥብ 3 ሚሊዮን ብር በላይ መላኩን ጠቁመዋል።

ዲያስፖራው በተለያዩ ግጭቶች ጉዳት የደረሰባቸውን አካባቢዎች መልሶ ለማቋቋም የሚያግዝ የ5 ነጥብ 2 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ ማቅረቡንም አስታውቀዋል።

የጤና ሥርዓቱን ለማሻሻል የሚረዱ ከ12 ነጥብ 2 ሚሊዮን ዶላር በላይ የሚያወጡ የሕክምና ቁሳቁሶች በዲያስፖራው አማካኝነት ወደሀገር ውስጥ መግባታቸውን አቶ ወንድወሰን ገልጸው፤ በተጨማሪም ለልዩ ልዩ የበጎ አድራጎት ተግባራት ዲያስፖራው 35 ሚሊዮን ብር ማበርከት መቻሉንም ተናግረዋል።

እንደ አቶ ወንድወሰን ገለጻ፤ ዲያስፖራው በተለያዩ ሀገራዊ እንቅስቀሴዎች ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እያደረገ ይገኛል። ባለፉት ዘጠኝ ወራት ለዓባይ ግድብ 815 ሺህ ዶላር አበርክቷል።

በስምንት ወራት ውስጥ ሦስት ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ዶላር ወደ ሀገር ውስጥ መላኩን አቶ ወንድወሰን ጠቁመው፤ የፋሲካና ኢድአልፈጥር በዓላትን ጨምሮ በዘጠኝ ወራት ውስጥ የተላከው አጠቃላይ የገንዘብ መጠን ሲታወቅ ከፍተኛ እንደሚሆን ገልጸዋል።

የዲፕሎማሲ ሥራን በሚመለከትም ዲያስፖራው ማኅበረሰብ ባለፉት ዘጠኝ ወራት በርካታ ተግባራት የከወኑበት መሆናቸውን የገለጹት አቶ ወንድወሰን፤ ዲያስፖራው ማኅበረሰብ የኢትዮጵያን ዕውነታ ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በማሳወቅና የውጪ ጣልቃ ገብነትን ከመቃወም አንፃር ያበረከተው አስተዋፅዖ ከፍተኛ መሆኑን አስታውሰዋል።

በሰሜን ኢትዮጵያ የነበረውን ጦርነት ለመፍታት ከተደረገው የሰላም ስምምነት በኋላ ስምምነቱን በመደገፍና ተከታታይ መግለጫዎችን በማውጣት የተለያዩ የዲያስፖራ ማኅበረሰብ አደረጃጀቶች ድጋፍ ማሳየታቸውንም የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል።

ዲያስፖራው በአካልና በዲጂታል አማራጮች ባከናወናቸው የዲፕሎማሲ ሥራዎች የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም የሚያስጠብቁ ተግባራት መከወናቸውንም አመላክተዋል።

በኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት መረጃ መሠረት በተለያዩ የዓለም ሀገራት ከሦስት ሚሊዮን በላይ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አባላት እንዳሉ ይገመታል።

# የተለያዩ ተቋማት በአቶ ግርማ የሺጥላ ሕልፈተ-ሕይወት የተሰማቸውን ጥልቅ ኃዘን ገለጹ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የተለያዩ ተቋማት በብልጽግና ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ አባልና የአማራ ክልል የብልጽግና ፓርቲ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ በአቶ ግርማ የሺጥላ ሕልፈተ-ሕይወት የተሰማቸውን ጥልቅ ኃዘን ገልጸዋል።

የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት፣ ብልጽግና ፓርቲ፣ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤትና የክልል መንግሥታት ባወጡት መግለጫ፤ በአቶ ግርማ የሺጥላ ሞት የተሰማቸውን ጥልቅ ኃዘን ገልጸዋል።

የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደገለጸው፤ የብልጽግና ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ አባልና የአማራ ክልል የብልጽግና ፓርቲ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ግርማ የሺጥላ ሚያዚያ 19 ቀን 2015 ዓ.ም በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን መንዝ ጌራ ወረዳ ልዩ ስሙ ኋሳ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ የታጠቁ ፅንፈኛ ኃይሎች ባደረሱት ጥቃት የግል ጠባቂዎቻቸውን ጨምሮ ሕይወታቸው በግፍ ሊያልፍ ችሏል።

ምክር ቤቱ እንዳለው፤ አቶ ግርማ የሺጥላ በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል የመቻቻልና የመከባበር የፖለቲካ ባሕል እንዲያብብ፣ አብሮነትና ወንድማማችነት እንዲጠናከርና እንዲፀና ደከመኝ ታከተኝ ሳይሉ ሲለፉና ሲጥሩ ነበር።

እኩልነትና ማኅበራዊ ፍትሕ የነገሠባት ጠንካራ ኅብረብሔራዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት በሚደረገው ርብርብ ክቡር አቶ ግርማ የሺጥላ ከሌሎች የሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን የተሰጣቸውን ታላቅ ሕዝባዊ፣ ድርጅታዊና መንግሥታዊ ኃላፊነት በልበ ሙሉነት፣ በትጋትና በኃላፊነት ስሜት የተወጡ አመራር መሆናቸውን ምክር ቤቱ ገልጿል።

አቶ ግርማ የሺጥላ ሀገር ወዳድ፣ ብልህ ቁርጠኛ የፖለቲካ አመራር የነበሩ ሲሆን ለሀገርና ለወገን ሲሉ ሙሉ ጊዜያቸውን፣ ጤናቸውን በመጨረሻም የማይተካውን ውድ ሕይወታቸውን ሰውተዋል፤ በመሆኑም የአቶ ግርማ የሺጥላ ጉልህ ሀገራዊና መንግሥታዊ አበርክቶ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ታሪክ ማሕደር ፈፅሞ የሚዘነጋ አይሆንም። ታሪክ መዝግቦ የሚይዘው ይሆናል ብሏል።

የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአቶ ግርማ የሺጥላና በግል ጠባቂዎቻቸው በደረሰው አደጋ የተሰማውን ኃዘን በመግለጽ፤ ለወገኖቻችን ሞት ምክንያት የሆነውንም አሳፋሪ ጽንፈኛ ድርጊትና ጥቃት በጽኑ አውግዟል።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት በበኩሉ በአማራ ክልል ብልጽግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ግርማ የሺጥላ ግድያ የተሰማውን ጥልቅ ኃዘን ገልጿል።

አገልግሎቱ ባወጣው የኃዘን መግለጫ ፡- ጽንፈኝነት



ብዙዎችን ሕዝብ ልጆች አሳጥቶናል፤ ጽንፈኞች ሰው መሆንን ይጠየፋሉ ብሏል።

የአማራ ክልል ብልጽግና ፓርቲ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ እና የፓርቲው ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ግርማ የሺጥላ ባደገበት ቀዬ በጽንፈኞች በግፍ ተገድሏልም ነው ያለው።

ይህም የጽንፈኛው ኃይል የመርዝ ፖለቲካ በቀየ የማይወሰን፤ ከጓዳ ጭምር ገብቶ ቤተሰብን የሚበትን መሆኑን አሳይቶናል ብሏል አገልግሎቱ በመግለጫው።

አገልግሎቱ ውዱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፥ አጀንዳ አልባ የጥላቻ ፖለቲካ ዘርተው ጽንፈኝነትን በማብቀል ልጆችህን በአደባባይ የሚቀጥፉ የደም ነጋዴዎችን ማስቆም ካልቻልክ፣ የግፍ በትራቸውን የብዙኃኑን ቤት ማንኳኳቱ አይቀሬ ነው ሲልም መልዕክቱን አስተላልፏል።

ዓላማቸው ማተራመስና ሀገራችንን ዕረፍት መንሣት የሆኑ አካላት አሉ ያለው አገልግሎቱ፣ የእነዚህ አካላት አርዓያዎቻቸው ዓለም አቀፍ አሸባሪዎች ናቸው ብሏል።

የእነርሱን ተግባር በኢትዮጵያ ለመድገምና ኢትዮጵያን ለማጥፋት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ያልተፈጸሙ ዘግናኝ ተግባራትን ሁሉ ይፈጽማሉም ነው ያለው በመግለጫው።

የብልፅግና ፓርቲም በአማራ ክልል ብልጽግና ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ግርማ የሺጥላ ሕልፈት የተሰማውን ኃዘን ገልጿል።

ፓርቲው ባወጣው የኃዘን መግለጫው አቶ ግርማ የሺጥላ በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ልዩ ቦታው መንዝ ኋሳ በተባለ አካባቢ ለሥራ እየተንቀሳቀሱ ባሉበት ወቅት በታጠቁ ጽንፈኞች በደረሰባቸው ጥቃት ሕይወታቸው በመጥቀስ በአቶ ግርማ ሞት የተሰማንን መሪር እና ጥልቅ ኃዘን እየገለጽን ለመላ ቤተሰቦቹና ባልደረቦቹ ፈጣሪ ያፅናችሁ ማለት እንወዳለን ብሏል።

ለመላ የአማራ ሕዝብ፣ ለፓርቲያችን አባላትና ደጋፊዎች በሙሉ መጽናናትንም እንመኛለን። ፓርቲያችን የአቶ ግርማ የሺጥላን ገዳዮች በአፋጣኝ ተከታትሎ ለሕግ እንደሚያቀርብ እና በፍትሕ አደባባይም ደሙን በፍትሕ እንደሚመልስ ለማረጋገጥ እንወዳለን ብሏል ፓርቲው።

በሃሳብ የተለየን ሰው በሃሳብ ሞግቶ፤ በአመለካከት የተለየን በአመለካከት ረትቶ መነጋገርና የሚበልጠውን የሚበጀውን ለሀገርና ለወገን ፍሬ የሚያፈራውን ሃሳብ ማስፋትና ማሳደግ ሲቻል የሰውን ልጅ የመሰለ ክቡር ፍጡር፣ ያውም እንደ ግርማ የሺጥላ ዓይነቱን የሀገር የሕዝብና የወገን አለኝታ የሆነ ምሑር ፖለቲከኛ በእንዲህ ዓይነት መልኩ መግደል መሸነፍ መሆኑን አሁንም ደግመን መናገር እንፈልጋለን ነው ያለው።

የአቶ ግርማ በጽንፈኛ ኃይሎች ጥቃት መቀጠፍ ስንሰማ ልባችን በኃዘን ደምቷል። በዚያውም ልክ ጽንፈኝነትን አምርረን መታገልና ማክሰም ግዜ የማይሰጠው ተግባር እንደሆነ አሳይቶናል ሲል በመግለጫው አመልክቷል።

በሀገራችን እየታየ ያለው የጽንፈኝነት አስተሳሰብ እና ከአስተሳሰቡ የሚነጩ እኩይ ድርጊቶች ከፍተኛ አደጋ ውስጥ ሊከቱን እንደሚችሉ ምንም ጥያቄ የለውም ነው ያለው በመግለጫው።

በመሆኑም ብልጽግና ፓርቲ ምልዓተ ሕዝቡን ያሳተፈ ጠንካራ የፖለቲካ ትግል በማድረግ እና ሕግ የማስከበር እርምጃዎችን በማጠናከር ጽንፈኝነትን ለመግታት ከምንግዜውም በበለጠ ጠንክሮ እንደሚሠራ አስታውቋል።

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት በበኩሉም በግርማ የሺጥላ ላይ በደረሰው አሰቃቂ ግድያ የተሰማውን ኃዘን ገልጿል።

ምክር ቤቱ ባወጣው የኃዘን መግለጫ፥ አቶ ግርማ የሺጥላ ለሕዝባቸው መሻሻል እና ለክልላቸው ልማት፣ ብሎም ለሀገሪቱ ዕድገት የበኩላቸውን ሲወጡ ኖረዋል ብሏል።

የአመለካከት ልዩነቶችን እና ስብራቶችን እርስ በርስ በመገዳደል ለውጥ ማምጣትና ማስተካከል እንደማይቻልም ነው ምክር ቤቱ የገለጸው።

ሥር የሰደዱ ግጭቶች እንኳን ቢሆኑ በአመጽ ሳይሆን በመነጋገር፣ በመወያየት፣ በመግባባትና በመደማመጥ እንዲሁም በመተባበር ብቻ መፈታት ይኖርባቸዋል ሲል ምክር ቤቱ ገልጿል።

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ድርጊቱን በጽኑ እንደሚያወግዝ ገልጾ መንግሥት ይህን አስነዋሪ ተግባር የፈጸሙ አካላትን በአፋጣኝ በቁጥጥር ስር በማዋል ተገቢውን የሕግ ተጠያቂነት እንዲያረጋግጥ ጠይቋል።

የተለያዩ ክልሎችም በአቶ ግርማ የሺጥላ ሕልፈተ ሕይወት የተሰማቸውን ኃዘን በመግለጽ ድርጊቱንም በጥብቅ አውግዘዋል።

# የኢትዮጵያ ባሕርና ሎጀስቲክስ አገልግሎት ከ32 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ መሰብሰቡን አስታወቀ

- ትግራይ የሚገኘውን የወደብና ተርሚናል አገልግሎት ለማስጀመር እየተሠራ ነው

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ባሕርና ሎጀስቲክስ አገልግሎት በዘጠኝ ወራት ውስጥ 32 ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር መሰብሰቡን አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ባሕርና ሎጀስቲክስ አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዶክተር መሪሶ አመሎ በትናንትናው ዕለት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳስታወቁት፤ ድርጅቱ ባለፉት ዘጠኝ ወራት 34 ነጥብ 89 ቢሊዮን ብር ለማስገባት አቅዶ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል።

በዚህም በተጠቀሱት ወራት ውስጥ 32 ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር መሰብሰቡን ገልጸዋል። የሥራ አፈፃፀሙ 93 በመቶ መሆኑን ተናግረዋል።

ገቢውን ለመሰብሰብ ባለፉት ዘጠኝ ወራት የተለያዩ ሥራዎች መከናወናቸውን የጠቀሱት ዶክተር መሪሶ፤ አጠቃላይ የድርጅቱን የኦፕሬሽን አገልግሎት መጠን አራት ሚሊዮን 131 ሺህ 929 ቶን ማድረስ መቻሉን አብራርተዋል።

በጭነት ማጓጓዝ አገልግሎት የድርጅቱንና የኪራይ መርከቦችን በመጠቀም ሁለት ሚሊዮን 885 ሺህ በላይ ቶን በማጓጓዝ ከእቅድ በላይ ተከናውኗል ብለው፤ በተጠቀሱት ወራት በጭነት አስተላላፊነት አገልግሎት በኩል በመልቲ ሞዳል የትራንስፖርት ሥርዓት 66 ሺህ 194 ኮንቴይነር ለማጓጓዝ ታቅዶ 70 ሺህ 742 ኮንቴይነር ማጓጓዝ እንደተቻለ አስረድተዋል።

ድርጅቱ ከሚሰጠው አገልግሎት በተጨማሪ ሀገሪቱን በማስተዋወቅ በተለይ በባሕር ትራንስፖርት ዘርፍ ላይ ከብዙ ዓለማት ጋር በማገናኘትና አምባሳደር በመሆን ኢትዮጵያን እያስተዋወቀ ይገኛል ያሉት ዶክተር መሪሶ፤ ድርጅቱ ከቢዝነስ ሥራው ባሻገር ማኅበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ ነው ብለዋል። በዚህም 37 ሚሊዮን ብር ለማኅበራዊ ኃላፊነት ማውጣቱን ተናግረዋል።

በተያያዘ የድርጅቱ የፖርት ተርሚናል አገልግሎት ዘርፍ ምክትል ሥራ አስፈፃሚ አቶ ምሕረትአብ ተክሉ በበኩላቸው በሰጡት መግለጫ፤ ትግራይ የሚገኘው የወደብና ተርሚናል አገልግሎት ሥራ እንዲጀምር እንቅስቃሴዎች መጀመራቸውን ጠቁመዋል።

ከፕሪቶሪያው ስምምነት በኋላ አንድ ልዑክ ወደ መቀሌ በመላክ ተቋርጦ የቆየውን የወደብና ተርሚናል አገልግሎት ለማስቀጠል ንግግር መጀመሩንና በአሁኑ ወቅት አጠቃላይ በሰው ኃይል፣ በቴክኖሎጂ እንዲሁም መሣሪያዎችን ጠግኖ ወደ ሥራ ለመግባት ዝግጅቱ ተጠናቋል ብለዋል። የወደብ ተርሚናሉንም በቀጣይ ሳምንት አገልግሎት ለማስጀመር እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

ዜና

# በአዲስ አበባ መምህራን ከከንቲባ አዳነች አቤቤ ጋር እንደሚወያዩ ተገለጸ

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከሁሉም ክፍል ከተሞች የተወጣጡ አምስት ሺህ የሚደርሱ መምህራን ከከንቲባ አዳነች አቤቤና ከከፍተኛ አመራሩ ጋር ውይይት ሊያደርጉ እንደሆነ ተገለጸ፡፡

የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዘላለም ሙላቱ በሰጡት መግለጫ፣ በመጪው ሰኞ ሚያዚያ 23 ቀን 2015 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከሁሉም ክፍል ከተሞች የተውጣጡ አምስት ሺህ የሚደርሱ መምህራን በትምህርት ልማት ዙሪያ በጎ ተፅዕኖ መፍጠር የሚያስችል ውይይት ከከንቲባ አዳነች አቤቤና ከከፍተኛ አመራሩ ጋር እንደሚያደርጉ አስታውቀዋል፡፡

ውይይቱም ባለፉት አምስት ዓመታት በትምህርት ዘርፉ የተገኙ ውጤቶችን ሊያስቀጥሉ የሚችሉ፣ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን እንዴት መቅረፍ እንደሚቻል የሚያመላክቱ ሀሳቦች የሚንጸባረቁበት እንደሆነ ገልጸዋል። የተቀራረበ አስተሳሰብ ያለው የትምህርት ማኅበረሰብ ማፍራት ከውይይቱ የሚጠበቅ ውጤት ነው ብለዋል።

የቢሮ ኃላፊው እንዳሉት፤ ለአራት ቀናት የሚቆይ የመምህራን ውይይት በትላንትናው ዕለት የተጀመረ ሲሆን፤ 63ሺህ 470 መምህራንና የትምህርት አመራሮችን ያካተተ ውይይት በ77 የመወያያ ማዕከላት እየተካሄደ ይገኛል፡፡ ሰኞ ዕለት የሚደረገው ውይይትም የዚሁ አካል ሲሆን፤ ውይይቱ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ሀገራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ተሳታፊ በመሆን አስተዋፅዖ ለማበርከት ያስችላል፡፡ በውይይት ሂደቱ ውስጥ ለሀገር የሚበጁ ምክንያትን የተከተሉ ሀሳቦች ለሚመለከተው አካል የሚቀርቡ ይሆናል፡፡

በዕለቱ በተለያዩ ምዕራፎች የሚደረጉ ውይይቶች ላይ እንደ ከተማም ሆነ እንደ ሀገር በከንቲባዋ ሊመለሱ የሚገቡ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥባቸው ይሆናል፡፡

በውይይቱ የተቀራረበ አስተሳሰብ ያለው የትምህርት ማኅበረሰብ ለመፍጠር የሚያስችሉ ሀሳቦች እንደሚስተናገዱና፣ ይህም የትምህርት ልማት ግቦችን ለማሳካት እንደሚረዳ አንስተዋል፡፡ ሀገር የገጠማትን ችግር በሰለጠነና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ በመነጋገር የጋራ መግባባት ለመፍጠር ውይይቱ ጠቃሚ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

የትምህርት ማኅበረሰቡ በተለይም መምህራን በመማር ማስተማር ሂደት ላይ የጎላ ሚና ያላቸው በመሆኑ ውይይቱ በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ በጎ ተፅዕኖ ለማምጣት ያስችላል ነው ያሉት፡፡

የውይይቱ ዓላማ የትምህርት ሥርዓቱን የተሳለጠ እንዲሆንና ዘመኑን የዋጀ የመማር ማስተማር ሂደትን ለመፍጠር እንደሆነ በመጥቀስ፤ ኢትዮጵያ ባለፉት አምስት ዓመታት ያስመዘገበቻቸውን ውጤቶችና በሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን መሠረት በማድረግ የሚካሄድ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ለትምህርት ልማት ሥራው ውጤታማነት መምህራንም ሆኑ የትምህርት አመራሮች የአንበሳውን ድርሻ እንደመውሰዳቸው የትምህርት ጥራትን በማረጋገጥ የተማሪዎችን ውጤትና ሥነምግባር ለማሻሻል ውይይቱ የጋራ መግባባት ላይ የሚደረስበት መሆኑንም አስረድተዋል።

ከየትምህርት ቤቱ ከተውጣጡ መምህራን እና የትምህርት አመራሮች ጋር በየክፍለ ከተማው ውይይት ከመካሄዱ ባሻገር በነገው ዕለት 500 የሚሆኑ መምህራን በከተማ አስተዳደሩ የተከናወኑ የልማት ሥራዎችን የሚጎበኙበት መርሐ ግብር መዘጋጀቱንም ኃላፊው ጠቁመዋል፡፡

## በትብብርና በእኩልነት...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

አቶ አደም ፋራህ የክልል አመራሮችንና ከፍተኛ የመንግሥት ሥራ ኃላፊዎችን በመምራት በትግራይ ጉብኝት ካደረጉ በኋላ ባደረጉት ውይይት ላይ እንደገለጹት፤ የትግራይ ሕዝብ ጥቅም በዘላቂነት ሊከበር የሚችለው ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር በፍትሐዊነትና በጋራ ማልማት ሲቻል ነው።

የትግራይ ሕዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋር በልማት እንዲያድግ መንግሥት በቁርጠኝነት ይሠራል ያሉት አቶ አደም፤ በትብብርና በእኩልነት መንፈስ በሚከናወኑ የልማት ሥራዎች ሀገርን ማሳደግ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

የትግራይ አጎራባች አፋርና አማራ ክልሎች የሕዝብ ለሕዝብ ጉድኝቱን የሚያጠናክሩ ሁነቶችን ለማከናወን ዝግጅት ላይ ናቸው ብለዋል።

ከትስስሩ ባለፈ መንግሥት በጦርነቱ ወቅት የወደሙ አገልግሎት መስጫዎችን በመጠገን አስፈላጊውን ድጋፍ ሲያደርግ መቆየቱን አስታውሰው፤ በቀጣይም በጦርነት የተጎዱ አካባቢዎችን መልሶ ለመገንባት በውጭ ሀገራትና በሀገር ውስጥ የሚገኙ አቅሞችን አስተባብሮ ለመሥራት ትኩረት እንደተደረገ አስታውቀዋል።

በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ዲያስፖራዎችና ተቋማት በተለያዩ ክልሎች ለሚከናወኑ የመልሶ ግንባታ ሥራዎች ድጋፍ እንዲያደርጉ አቶ አደም ፋራህ ጥሪ አቅርበዋል።

የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ በበኩላቸው፤ ችግሮች ተፈጥረው የጠፋውን መመለስ ባይቻልም ለቀጣዩ ግን ተቀራርቦ መሥራትና በጋራ ትብብር የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን ማጠናከር እንደሚገባ ተናግረዋል።

ካለፈው ችግር ተምረን ወደፊት ጉዳዮቻችንን በሰላማዊ ውይይት መፍታት የምንችልበትን መንገድ ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው የሚል መልዕክት በክልላችን ሕዝብ ስም ማስተላለፍ እፈልጋለሁ ብለዋል።

በትብብር መንፈስ ለመወያየትና በጋራ ለመሥራት የሚያስፈልገው ዝግጁነት ነው ያሉት ዶክተር ይልቃል፤ ተቀራርቦ መሥራትና በትብብር መንቀሳቀስ አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል።

የአፋር ክልል ርዕሰ መስተዳድር ሐጂ አወል አርባ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ቀጣይነት ያላቸው ውይይቶችን በማከናወን ቁርሾ የፈጠሩ ችግሮችን ማስወገድና የሕዝቦችን የጋራ ተጠቃሚነት ማሳደግ ይገባል።

መነጋገር መፍትሔ ያመጣል፤ ከጦርነት የሚገኝ ትርፍ እንደሌለ ታይቷል ያሉት ሐጂ አወል አርባ፤ ካለፈው ስህተት ትምህርት ወስዶ በመቀራረብ ለሕዝቦች የሚጠቅም ልማትን ማከናወን ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

የትግራይ፣ የአፋርም ሆነ የአማራ ሕዝብ ችግር የሌላውም ኢትዮጵያዊ ነው። እንደሀገር ያሉብንን ችግሮች ለማስወገድ በፍትሐዊነት ልማቱ ላይ መሳተፍና በትብብር መንፈስ መጠናከር ይኖርብናል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ፕሬዚዳንት አቶ ጌታቸው ረዳ፤ ጦርነቱ በሰላም ከተቋጨ በኋላ የክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች፣ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባዎች እንዲሁም የተለያዩ የሥራ ኃላፊዎች ግንኙነቱን ለማጠናከር ወደትግራይ በማቅናት ጉብኝት ማድረጋቸውን አድንቀዋል።

ጉብኝቱ በጋራ ትብብር ለመሥራት የሚያስችል መንፈስ የተፈጠረበት መሆኑን ጠቁመው፤ የትግራይ ሕዝብ ባገኘው ሰላም ተጠቅሞ ለማደግ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር በጋራ የሚሠራ መሆኑን አስረድተዋል።

## የምክትል ጠቅላይ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ ዓለም እንደገለጹት፣ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን በአራት የምሥራቅ አፍሪካ ሀገሮች ጉብኝት አድርገዋል። ጉብኝቱ በየትኛውም መመዘኛ ስኬታማ የሚባል ነው ብለዋል።

እንደ አምባሳደሩ ገለጻ፣ አራት ቀን የተካሄደው የዲፕሎማሲ ማራቶን፤ ሀገራት ከኢትዮጵያ ጋር ካላቸው ግንኙነት አንጻር የተለያየ ውጤት አስገኝቷል፤ ኢትዮጵያ አሁን ያለችበትን የሰላም ሁኔታ በተመለከተ በተሻለ ሁኔታ ለማስረዳት ትልቅ ዕድል የፈጠረ ነው።

በታንዛኒያ፣ በኮሞሮስ፣ በብሩንዲና በዩጋንዳ ያደረጉት ጉብኝት ወዳጅነትን ለማጠናከር ያለመ ስለመሆኑ የተናገሩት አምባሳደሩ፤ በጉብኝታቸው ወዳጅ የማብዛትና የኢትዮጵያን ወቅታዊ የሰላም ሁኔታን የማስገንዘብ ሥራ መሠራቱን ገልጸዋል።

ጉብኝቱ ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ሀገራት ጋር ያላት ግንኙነት ይበልጥ ለማጠናከር ከማስቻሉም በላይ የነበረውን ጠንካራ ትስስርም ያጸና ነበር ብለዋል።

እንደ አምባሳደር መለስ ማብራሪያ፤ በተለይ የጋራ ጉዳይ በሆነው የዓባይ ግድብ ዙሪያ በአፍሪካ ኅብረት ጥላ ስር በውይይት ሁሉም ሀገራት አሸናፊ በሚሆኑበት ሁኔታ መካሄድ እንዳለበት ጉብኝት የተደረገባቸው ሀገራት መሪዎች አጽንዖት ሰጥተው ተናግረዋል። የዓባይ ግድብ ፖለቲካዊና ዓለም አቀፍ መልክ እንዲኖረው ማድረግ ጠቃሚ እንዳልሆነ መግባባት ላይ ተደርሶበታል። ግድቡ አፍሪካዊ ግድብ ነው። በድርድሩ የሚሳተፉ ሀገሮች አፍሪካውያን ናቸው። አደራዳሪውም አፍሪካዊ አካል ነው። ሌላ አካል አጀንዳውን ጠልፎ የዕለት ተዕለት አጀንዳ የሚያደርግበት ሁኔታ ተገቢ አለመሆኑን ከመግባባት ተደርሷል።

ከሱዳን ጋር በተገናኘም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከሱዳን ጦር ዋና አዛዥ ጀኔራል አብዱል ፈታህ አልቡርሃን እና ከሱዳን ፈጥኖ ደራሽ ኃይሎች ዋና አዛዥ ሞሐመድ ሃምዳን ዳጋሎ ጋር የስልክ ውይይት አካሂደዋል ያሉት አምባሳደር መለስ፤ በውይይቱ የሱዳን ሕዝብ ሰላም እንደሚያስፈልገውና ሰላም እንዲመጣ ሁለቱም መሪዎች ዕድል መፍጠር እንዳለባቸው ተነጋግረዋል ብለዋል። የኢትዮጵያ መንግሥት ሰላም እንዲመጣ በትኩረት እንደሚሠራና የሱዳን ሕዝብ የውስጥ ችግሩን ለመፍታት ብቃቱም እውቀቱም እንዳለው ገልጸውላቸዋል ሲሉ አብራርተዋል።

ከሱዳን ጦርነት ጋር በተገናኘ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቋቋመ ኮሚቴ መኖሩን ያነሱት ቃል አቀባዩ፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ድንበር ድረስ ባለሙያዎችን ልኮ ጉዳዩን እየተከታተለ ነው። ሌሎች መሥሪያ ቤቶችም ባለሙያዎችን ወደ ድንበር አሠማርተው ሥራ እየሠሩ ነው። ካርቱም ያለው ኢትዮጵያ ኤምባሲና ገዳሪፍ ያለው ቆንስላ አገልግሎት እየሰጠ ነው፤ ነገር ግን በካርቱም ባለው የፀጥታ ችግር ምክንያት የተወሰኑ ዲፕሎማቶች ወደ ገዳሪፍ ተዛውረዋል። ለዜጎቻችንና ለተለያዩ ሀገራት ዜጎች የቆንስላ አገልግሎት እየተሰጠ ወደ ሰላም ቦታ እንዲመጡ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ይገኛል ብለዋል።

እንዲሁም ከባለፈው ረቡዕ ጀምሮ በኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የኢንቨስትመንት ፎረም ጉባኤ እየተካሄደ ነው ያሉት ቃል አቀባዩ፤ በአንድ ሀገር የሚካሄድ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ የመጨረሻ ግቡ ገቢ ማስገኘትና የሥራ ዕድል መፍጠር ነው። እናም ከሁለት ዓመት የቀውስ ዲፕሎማሲ ወጥተን ጠንካራ የሚባል የኢኮኖሚ ፖሊሲ ማካሄድ መቻሉ ትርጉሙ ትልቅ ነው ብለዋል። የተካሄደው ጉባኤ በኢትዮጵያ ያሉ የኢንቨስትመንት እድሎችን ለመጠቀም ያለው ጠቀሜታ ጉልህ ነው ብለዋል።

## ከአንድ ነጥብ ስድስት...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

አማራጮች ያሏት ምድር” በሚል መሪ ሃሳብ በአዲስ አበባ ለሦስት ቀናት ሲካሄድ የነበረው ፎረም ትናንት ተጠናቋል።

በማጠናቀቂያው እለት ከተለያዩ የውጭ ኩባንያ ተወካዮች ጋር የኢንቨስትመንት ስምምነት የተፈራረሙት ኮሚሽነሯ ሌሊሴ ነሜ ከአምስቱ ኩባንያዎች አራቱ አዳዲስ ፕሮጀክቶችን ይጀምራሉ ብለዋል። አጠቃላይ ካፒታላቸውም አንድ ነጥብ 645 ቢሊዮን ዶላር የኢንቨስትመንት ስምምነት እንደሆነ ተናግረዋል።

ባለሀብቶቹ በግንባታ ግብዓቶች፣ በምግብ፣ በግብርና በጣውላና እንጨት ሥራዎች ላይ እንደሚሠማሩ የተገለጸ ሲሆን፤ ኮሚሽኑ የተፈራረመው ትልቁ ኢንቨስትመንት የአንድ ቢሊዮን ዶላር ስምምነት እንደሆነም ታውቋል።

ኩባንያው በእንጨት ምርትና ማሽነሪ ማምረቻ፣ ግብይትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት እንዲሁም በበጎ አድራጎት ድርጅት ላይ የሚሠሩ ስድስት የቢዝነስ ዘርፎች እንደሚኖሩት ኮሚሽነሯ ገልጸዋል።

ሁዋጃን የተባለው የግል ኢንዱስትሪ ከ21 ባለሃብቶች ጋር ስምምነት የተፈራረመ ሲሆን፤ ባለሃብቶቹ በአጠቃላይ 96 ሚሊዮን 200 ሺህ ዶላር የሚገመት ኢንቨስትመንት ያመጣሉ ተብሏል።

ከኮሚሽኑ ጋር የተፈራረመው 30 ሚሊዮን ዶላር ፈሰስ በማድረግ የማስፋፊያ ሥራ ይሠራል የተባለው ኢትዮ ቺክን ኩባንያ በኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናን ለማስፈን በሚደረገው ጥረት ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደሚያበረክት ኮሚሽነር ሌሊሴ አመልክተዋል። የውስጥ ፍላጎትን በማሟላት ለውጭ ገበያ እንደሚያቀርብም ተስፋቸውን ገልጸዋል።

በሲሚንቶና ግንባታ ሥራዎች ላይ የሚሠማራው የቻይና ኩባንያም 500 ሚሊዮን ዶላር ፈሰስ ያደርጋሉ ከተባሉት መካከል ይጠቀሳል።

በስምምነቱ ላይ ኮሚሽነር ሌሊሴ ከሁለት ዓመት ፈተና በኋላ አዳዲስ ባለሀብቶች ወደ ኢትዮጵያ እየገቡ እንደሚገኙ አመልክተዋል። የኢትዮጵያ መንግሥት የውጭ ባለሃብቶችን ለመሳብ እና ለመደገፍ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችን ማድረጉን እና በርካታ ሕጎችና አሠራሮችን ማሻሻሉንም ጠቁመዋል።

ፎረሙ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ከ22 ሀገራት የተውጣጡ ከአንድ ሺህ በላይ ባለሀብቶች እና የንግዱ ማኅበረሰብ አባላት ተሳታፊ ሆነዋል። መቀመጫውን በአዲስ አበባ ያደረገው የዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ የኢትዮጵያን የኢንቨስትመንት አቅም ለማሳደግ ሚና ተጫውቷል ብለዋል።

ኢትዮጵያ እንደሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ያልተነካ የኢንቨስትመንት አቅም እንዳላት እና ሰፊ የሰው ኃይል ያላት በመሆኑ ባለሃብቶች ይህንን እምቅ አቅም ሊጠቀሙበት እንደሚገባ ጠቅሰዋል።

የኢንቨስትመንት ዘርፉ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት በሙሉ ባለሃብቶችን ለመደገፍ ቃል መግባታቸውንና ፎረሙ በየዓመቱ ሊካሄድ መታቀዱንም ተናግረዋል።

የፕላንና ልማት ሚኒስትር ዶክተር ፍጹም አሰፋ በበኩላቸው፤ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ታሳቢ ያደረገ የሀገር ውስጥ ኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳ ተቀርፆ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

መንግሥት የበለጠ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የንግድ ሕጎችን በመከለስ እየሠራ ነው ያሉት ዶክተር ፍጹም፤ ከባለሀብቶች ጋር በመተባበር ሁሉንም የኢንቨስትመንት አማራጮች ለመክፈት በማቀድ እየተሠራ ነው ብለዋል።

ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያውም ሆነ የ10 ዓመቱ የኢኮኖሚ ዕቅድ የውጭ ባለሃብቶች በኢትዮጵያ እንዲሠማሩ የሚጋብዝ መሆኑንም ጠቁመዋል።

‹‹በኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስት ማድረግ ትርፍን ከፍ ለማድረግ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ አካል መሆን ነው›› በማለትም ተናግረዋል።

በግብርና፣ በማዕድን፣ በቤት ልማት፣ በማምረቻ ኢንዱስትሪ፣ በቱሪዝም፣ በታዳሽ ኃይል እና በሌሎች ዘርፎች ዕምቅ የኢንቨስትመንት አማራጮች መኖራቸውንና የውጭ ባለሃብቶች እንደፍላጎታቸው ሊሠማሩ እንደሚገባም ነው ዶክተር ፍጹም የጠቆሙት።

# የዘመን እንግዳ

# «ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ ከተፈለገ የሁሉም ወገን መብት መከበር አለበት»

-አቶ ካሳሁን ፎሎ
የኢሠማኮ ፕሬዚዳንት



ፎቶ: ፀሐይ ንጉሤ

**ያለመረዳት ካልሆነ በስተቀር ለሙያ ደህንነትና ጤንነት ሲባል የሚወጣው ወጪ ጠቀሜታው ለሠራተኛ ብቻ ሳይሆን ለአሰሪውም ጭምር ነው**

አስቴር ኤልያስ

ለሥራ ጉዳይ ወደጅማ እያቀኑ ባሉበት በአንድ ዕለት አንድ የስልክ ጥሪ ይደርሳቸዋል።የስልክ ጥሪው ለጊዜው ስሙን መጥቀስ ከማይፈልጉት ድርጅት ውስጥ ከሚሠራ የሠራተኛ ማኅበር ሊቀመንበር የመጣ ነው።የማኅበሩ ሊቀመንበር መረር ባለ ድምጸት በሚሠራበት ድርጅት ውስጥ ባለ አንድ ማሽን ላይ የሚሠራ የአንድ ልጅ እጅ በማሽኑ መቆረጡን ይነግራቸዋል።ልጁም የአካል ጉዳት ስለደረሰበት ሥራውን ለቆ ይሄዳል።

እዚያው ማሽን ላይ ምንም ዓይነት ጥንቃቄ ሳይደረግ ሌላ ሠራተኛ እንዲሠራ መደረጉንና የዚያም ሠራተኛ እጅ መቆረጡን ይገልጽላቸዋል።በዚህ ሳያበቃ ያለምንም ጥንቃቄ ሦስተኛ ሠራተኛ እዚያው ማሽን ላይ እንዲሠራ ይደረግና አሁንም የዚያ የሦስተኛው ሠራተኛ እጅ ልክ እንደቀደሙት ሁሉ ተቆረጠ ይላቸዋል።በዚህ መሃል ሌላ ሠራተኛ እስከሚገኝ በሚል ራሱ የማኅበሩ ሊቀመንበር ገብቶ እንዲሠራ መደረጉን ቅር እያለው ያወጋቸዋል።ጉዳዩን ከጅማ ሥራ መልስ እንደሚያዩት ያወጉትና የመረጃ ልውውጡ ያበቃል፡፡

እርሳቸውም ወደጅማ የሔዱበትን ጉዳይ ፈጽመው ከመመለሳቸው በፊት የዚሁ የሠራተኛ ማኅበሩ ሊቀመንበር እጅ ለአራተኛ ጊዜ መቆረጡን ይሰማሉ።በዚህም በጣም ያዝናሉ።ይህ የጥንቃቄ ጉድለት ያመጣው መከራ ነው እንጂ መቼም በድርጅቱ የተገጠመው የሰው እጅ ብቻ እየመረጠ የሚበላ ማሽን አይደለም ሲሉ ኀዘናቸውን ይገልጻሉ፤ የዛሬው የዘመን እንግዳችን የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ኮንፌዴሬሽን (ኢሰማኮ) ፕሬዚዳንት አቶ ካሳሁን ፎሎ።

አቶ ካሳሁን ተወልደው ያደጉት በኦሮሚያ ክልል ነው።በሕግ የመጀመሪያ ዲግሪ አላቸው፤ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ደግሞ ከሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በዓለም አቀፍ ሕግ አግኝተዋል።እኚህ የዛሬ እንግዳችን በመጀመሪያ የኦሮሚያ መንገዶች ድርጅት ተቀጥረው ሕግ ክፍል ውስጥ ሠርተዋል።እዚያ እያሉ የድርጅቱ ሠራተኞች የማህበራቸው ፕሬዚዳንት አድርገው ይመርጧቸዋል። በኋላም የኢሰማኮ ፕሬዚዳንት ሆነው ወደ 13 ዓመት ያህል ሠርተዋል፤ በመሠራት ላይም ይገኛሉ።እኛም ዘንድሮ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ134ኛ እንዲሁም በአገራችን ለ48ኛ ጊዜ የሚከበረውን የዓለም አቀፍ የሠራተኞች ቀንን ምክንያት በማድረግ እንግዳችን አድርገናቸዋል።

**አዲስ ዘመን፡- አሰሪዎች ሠራተኛው እንዲደራጅ ፍላጎት እንደሌላቸው ይነገራል፤ ስመሆኑ የሠራተኞች በማኅበር መደራጀት እንደ ስጋት የሚቆጥሩት ለምን ይሆን ከሚለው ጭውውታችንን ብንጀምር?**

**አቶ ካሳሁን፡-** መልካም ነው፤ የሠራተኛው መደራጀት ስጋት የሚሆነው ከሁለት ነገር በመነጨ ምክንያት ነው፤ የመጀመሪያው ሠራተኛው ሲደራጅ ስለመብቱ ይጠይቃል ከሚል ስጋት ነው።ከአሰሪው ጋር የመደራደር አቅም ይፈጥራል።ሌላው ቀርቶ በደመወዝ ጭማሪ ጉዳይ መደራደር ይችላል በሚል ነው። ይህ ደግሞ የሠራተኛው ጥቅም ስለሚሆን አሰሪዎች መደራጀቱን እንደ ስጋት ሊቆጥሩት ይችላሉ። ሁለተኛው ስጋት ደግሞ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ጉዳይ ነው።የሙያ ደህንነትና ጤንነት ሲባል በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ላይ በግልጽ የተቀመጠ ነው፤ ይህ ስለማይከበር ለሙያ ደህንነትና ጤንነት ወጪ ያወጣሉ።

ያለመረዳት ካልሆነ በስተቀር ለሙያ ደህንነትና ጤንነት ሲባል የሚወጣው ወጪ ጠቀሜታው ለሠራተኛ ብቻ ሳይሆን ለአሰሪውም ጭምር ነው። አንድ ድርጅት ሲቋቋም ለሠራተኛው የሚያስፈልገው ሁሉ ተሟልቶ መሆን ሲገባው አሰሪዎች ያንን አያደርጉም፤ ሠራተኛው ከተደራጀ ደግሞ ይህንንም ጨምሮ ሌሎች መብቶቹን ስለሚጠይቅ መደራጀቱን እንደስጋት ሊያዩት ይችላሉ።

**አዲስ ዘመን፡- አንዳንድ አሰሪዎች ሠራተኛው ከተደራጀ የሥራ አድማ ለማድረግ ቅርብ ነው የሚል ፍራቻ አላቸው፤ እዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**አቶ ካሳሁን፡-** በነገራችን ላይ የሠራተኛ ማኅበር ከተቋቋመበት ድርጅትና ካልተቋቋመበት ድርጅት የሥራ አድማው የሚበረታው ማኅበሩ በሌለው ድርጅት ነው። ሠራተኛ ማኅበር ሲቋቋም ሕጋዊ ሰውነት አለው። ሠራተኛው ሕገ ወጥ ነገር ከሠራ ይከሰሳል። ነገር ግን ሠራተኛ ማኅበሩ በሌለበት ሠራተኛው ሥራ ሲያቆም ወደሥራ የመመለሱ ጉዳይ በራሱ አስቸጋሪ ይሆናል።

ለአብነት የማነሳልሽ አንድ ገጠመኝ አለኝ፤ ወደአራት ሺ ሠራተኞች ያሉት አንድ ኢንዱስትሪ ሠራተኞቹ ሥራቸውን በአድማ አቆመው ወደየቤታቸው ሔዱ። በወቅቱ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተደወለልኝና ምን ማድረግ እንችላለን አሉኝ፤ የእኔም ምላሽ የነበረው ማኅበር ስለሌላቸውና ሠራተኛውንም ማግኘት ስለማይቻል ምንም ማድረግ አይቻልም የሚል ነበር።ነገር ግን ሠራተኛው መጠራት አለበት ወደሚል ቢመጣም ማኅበር ስላልነበራቸው በምን አግባብ ይቻላል የሚለው በወቅቱ አነታራኪ ነበር፡፡

የሠራተኛው መደራጀት ለዚህ ሁሉ ችግር መድኃኒት ነው፤ ምክንያቱም ማኅበር ሲኖር ሠራተኛው ሥራ ለማቆም ቢፈልግ እንኳ የራሱ የሆነ ቅደም ተከተል አለው፤ የትኛውም ሠራተኛ ስላልተመቸው ብቻ ከእንቅልፉ ብንን ብሎ ሥራ ማቆም አይችልም፤ መደራደር አለ። ልምድ ያለውን ሠራተኛ ማጣት ደግሞ ለአሰሪውም ለአገርም ጭምር ጉዳት ነው።ስለዚህ የማኅበሩ መኖሩ ጥቅሙ ከፍ ያለ ነው።

በነገራችን ላይ የሠራተኛውን መደራጀት አሰሪው ብቻ ሳይሆን መንግሥትም ይፈራል።እንዲያውም በኢትዮጵያ ውስጥ የመንግሥት ሠራተኞች በብዛት ያለመደራጀታቸው ጉዳይ መንግሥት ስለሚፈራ ጭምር ነው።የመንግሥት ሠራተኞች እንደማንኛውም የኢንዱስትሪ ሠራተኞች በማኅበር የመደራጀት መብት አላቸው። የኢንዱስትሪውም አሰሪ ሆነ የመንግሥትም ስጋት አንድ ነው፤ ሠራተኛው በማኅበር ከተደራጀ የደመወዝ ጭማሪ ይጠይቃል የሚል ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ ሠራተኛው ከአገሪቱ አቅም በላይ የሆነ የደመወዝ ጭማሪ ይደረግልኝ የሚል ጥያቄ ያነሳል ብሎ ማሰብ ሲቪል ሠራተኛው አያስብም እንደማለት የሚቆጠር ነው። ነገር ግን ሠራተኛው አገሩ ያለችበትን ሒደት ስለሚያውቅ ያስባል። ስለሆነም ከአገሪቱ አቅም በላይ ጥያቄ አያቀርብም።የግል ድርጅት አሰሪዎች ዘንድም ቢሆን የሚፈሩት የሥራ ማቆም አድማ ማኅበር ባይኖርም አይቀርም።

በመሆኑም በዚህ በሰለጠነ ዘመን መደራጀት ማለት ሕጋዊ መሆን ማለት ነው። በተለይ በማኅበራዊ ትስስር ገጽ አንድ ሚሊዮን አባላትን ማንቀሳቀስ በሚቻልበት በዚህ ዘመን በማኅበር እንዳይደራጁ መከልከል ወይም እንደ ስጋት መቁጠር ተገቢነቱ አይታየኝም። ስለዚህ አደረጃጀት ለተጠያቂነትም የሚያመች በመሆኑም ይከሳል፤ ይከሰሳል፤ ይደራደራልም ባይ ነኝ።

በመሠረቱ ሲቪል ሠራተኛው እንዳይደራጅ የመከልከሉ ምስጢር ሙሰኞች በየመስሪያ ቤቱ የሚፈጽሙት ሙስና እንዳይጋለጥም ስለሚፈለግ ይመስለኛል። እንዲያውም አንዳንድ ቦታ ከመጀመሪያው ጀምሮ ሠራተኛው እንዳይደራጅ ያደርጋሉ፤ አሻፈረኝ ብሎ ሠራተኛው እንዲደራጅ የሚያስተባብሩ ካሉ ወይ ቀድመው ያዘዋውሯቸዋል፤ አሊያም ሰበብ ፈልገው ከሥራ ያሰናብቷቸዋል።

አንዳንድ ተቋማት ደግሞ ልክ ሠራተኛው ተደራጅቶ ኮሚቴው ሲመረጥ የኮሚቴ አባላትን ወደማኔጅመንት ያሳድጓቸዋል። ወደእዛ ካደገ ደግሞ ማኅበር ሊሆን አይችልም። ስለመብትም ሊከራከር አይችልም። እነርሱም ለሁሉም ሠራተኛ ጥቅም ከሚሰጡ ጥቂት የኮሚቴ አባላትን መጥቀምን ይመርጣሉ። በዚህ አካሄድ ማኅበሩ ከጨዋታ ውጪ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡

አንዳንድ ቦታ ደግሞ እስርም አለ፤ በተለይ የኮሚቴ አባላት ሁሉ ይታሠራሉ። ለምሳሌ በቅርቡ በአዳማ አካባቢ በአንድ ኢንዱስትሪ ያሉ ሠራተኞችን አደራጅተን ነበር። ይሁንና አምስቱንም የኮሚቴ አባላት አሰሯቸው። አሰሪዎቹ ምክንያት ሲባሉ የተደራጁት ለአመጽ ነው የሚል ምላሽ ሰጡ።ነገር ግን ለአመጽ በሕጋዊ መንገድ መደራጀት አያስፈልግም፤ ሠራተኛው ሥራ ማቆም ካስፈለገው እንኳ ሕጋዊ መስመርን ተከትሎ እንጂ እንዳሻው አይሆንም። ምክንያቱም ሥራ ለማቆም በማኅበር የተደራጀ ሠራተኛ ለአሰሪው ቢያንስ የአስር ቀን ጊዜ ይሰጠዋልና ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የሙያ ደህንነትና ጤንነት እንዲጠበቅ የወጡ መመሪያዎችና ሕጎችን አሰሪዎች ምን ያህል ተግባራዊ እያደረጉ ነው? ተግባራዊ እየተደረገ ካልሆነ ደግሞ መፍትሔው ምንድን ነው?**

**አቶ ካሳሁን፡-** የሙያ ደህንነትና ጤንነት በተመለከተ አስቀድሜ ለመጥቀስ እንደሞከርኩ አስፈጻሚ አካል ዘንድ የግንዛቤ ችግር ይታያል። ሌላው የሥራውን ሁኔታ በማየት በሚቆጣጠረው ላይ የባለሙያ እጥረት አለ።ዘርፉን የሚቆጣጠር የሰው ኃይል ማነሱ ብቻ ሳይሆን በጀትም የሌለው ነው።ስለዚህ ይህ በራሱ በመንግሥት መሟላት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡

ለምሳሌ በርከት ያሉ ኢንዱስትሪዎች ባሉባት በእኛ አገር ያለው የሙያ ደህንነትና ጤንነት ባለሙያ 500 ያህል ብቻ ነው። ይህ ለአዲስ አበባ ብቻ እንኳ ቢወሰድ የሚችል አይሆንም። ቢያንስ አንድ ድርጅት አንዴ እንኳ መታየት መቻል አለበት ባይ ነኝ።የሙያ ደህንነትና ጤንነት ባልተጠበቀበት ድርጅት ከሚፈጠረው ጉዳት የተነሳ ድርጅቱ ተከሶ እስከመዘጋት ሊደርስ የሚችል ቢሆንም ይህን መብት በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ የለም። ይህ ችግር ደግሞ በየቦታው ጉዳት ሲያመጣ ተስተውሏል።በየቦታው ያሉ ማሽኖች ከጥንቃቄ ጉድለት የተነሳ በሠራተኛው አካል ላይ ጉዳት ሲያደርሱ ይስተዋላል።

በኮንስትራክሽን ዘርፉ ደግሞ በጥንቃቄ ጉድለት የሚፈጠረውን ሞትና የአካል ጉዳት በየቀኑ የሚሰማ ጉዳይ ሆኗል።በግንባታ ላይ ያለ ሕንፃ ላይ ሠራተኛው የሚወጣጣበት ስካፎል (መወጣጫ) በብረት መሠራት ሲገባው እየተሠራ ያለው በእንጨት ነው። ያውም የሚሠራው በበሰበሰ እንጨት በመሆኑ ሠራተኛው ለአደጋዎች ተጋላጭ ይሆናል።ለምሳሌ በእኛ መስሪያ ቤት አካባቢ አንድ እየተገነባ ያለ ሕንፃ አለ፤ ይህ ሕንፃ ግንባታው ሳይጠናቀቅ በመሃል ቆሞ ነበር። እስካሁን ሕንፃው ሳይጠናቀቅ በጥንቃቄ ጉድለት ስምንት ሰው ሕይወቱን አጥቶበታል። ይህ በየቦታው የሚጠፋው የሰው ልጅ ሕይወት ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል ማሳያ ነው።

ይህ በዓይን የሚታይ ነው፤ የማይታይ የውስጥ የሆነ ጉዳት ደግሞ አለ፤ የኬሚካል ተጠቂ ሆነው የሚሠሩ ሰዎች ለምሳሌ የሙያ ደህንነትና ጤንነት በማይጠብቁ የአበባ አምራች ድርጅቶች ላይ የሚሠሩትን መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ ሠራተኞች የሚያጋጥማቸው የጤና እክል የአጭር አሊያም የረጅም ጊዜ ጉዳት ሊሆን ይችላል። የዚህ ሠራተኛ ሕይወት ያልፋል፤ ግን አይቆጠርም።

በረጅም ጊዜ ጉዳት ሕይወቱ ሊያልፍ ይችላል።በዚህ ዓይነት የአካል ጉዳት የደረሰበት ሠራተኛ ‹ካሳ› ተብሎ እንደዋዛ ጥቂት ነገር ተሰጥቶት ድርጅቱን ለቆ ይሄዳል፤ በተከታታይ ለሚያጋጥመው መከራ ምንም ዋስትና አይኖረውም፤ መጨረሻ ላይ የሚበላውን ሲያጣ ወጥቶ መለመን ዕጣ ፈንታው ይሆናል።

መንግሥት በእንዲህ ዓይነት ግዴለሽነት በሠራተኛው ላይ በሚፈጠረው ጉዳት መሥራት የማይችለውን ሠራተኛ ሁሉ መቀለብ አይችልም፤ ምክንያቱም ከአቅሙ በላይ ይሆናልና ነው። ይህ እንዳይሆን ግን በጋራ መከላከል ይቻላል። በሌላ አገር ያለ ልማድ ሠራተኛ ከመቀጠሩ በፊት አንድ ድርጅት ምን ያህል ሠራተኛ እንደሚቀጥርና ምን ዓይነት ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት አስቀድሞ የሚያውቅና ሕግ ሲተላለፍም የሚቀጣ ይሆናል።

በእኛ አገር ለምሳሌ አንዳንድ ድርጅቶች ብየዳ ላይ ለሚሠሩ ሠራተኞች ወተት ያቀርቡላቸዋል፤ ለዚያ ሠራተኛ ደህንነት የሚያስፈልገው በመጀመሪያ ዓይኑ እንዳይጎዳ የሚያግዝ መሣሪያ ነው ሊሰጥ የሚገባው።በእርግጥ ወተት የሚያስፈልግበት ቦታ ሊኖር ይችላል።ስ ለዚህ የሙያ ደህንነትና ጤንነት መጠበቅ አማራጭ ሊሰጠው የሚገባ ሳይሆን ግዴታ ነው፤ ያንን ሳናደርግ ስንቀር ግለሰብ፣ ቤተሰብ ብሎም አገር ተጎጂ ይሆናልና ሊታሰብበት የግድ ይላል፡፡

በእኛ አገር ነባራዊ ሁኔታ ደግሞ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ምናልባት ሥራ ሊኖረው የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ሊሆን ይችላል፤ ያም ሰው የአካል ጉዳት ከደረሰበት ኀሮሮው የሚዘጋው የቤተሰቡ ሁሉ ነውና ይህ ግንዛቤ ውስጥ ገብቶ ትኩረት ቢሰጠው መልካም ነው፤ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራም ቢሠራ ጉዳቱን ለመቀነስ አጋዥ ነው። አሰሪውም ቢሆን ተጎጂ ነው፤

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## «ምርትና ምርታማነት...



ለምሳሌ የአስር ዓመት ልምድ ያለውን ሠራተኛ ከጥንቃቄ ጉድለት አጥቶት ከሆነ ሌላ እስከሚያላምድ ድረስ ብዙ ዋጋ ይከፍላል። ለተጎዳውም አካል ካሳ ከመክፈልና እስከሚድንም ድረስ ከማሳከምም ይድናል።

**አዲስ ዘመን፡-የተረጋጋ የኢንዱስትሪ ሰላም እንዲሰፍንና ምርታማነት እንዲያድግ ከመንግሥትም ሆነ ከሠራተኛው ምን ይጠበቃል?**

**አቶ ካሳሁን፡-** የተረጋጋ የኢንዱስትሪ ሰላም እንዲፈጠር እንዲሁም ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ ከተፈለገ የሁሉም ወገን መብት መከበር አለበት። ምክንያቱም መብት ከተጓደለ መብት ጠያቂ አካል ይኖራል።ስለዚህ ሥራው ይቀርና አሰሪውም ሠራተኛውም ወረቀት ይዞ ፍርድ ቤት መመላለስ ይሆናል።ይህ በመሆኑ ጊዜና ገንዘብ ይጠፋል።ይህ ከሚሆን ሠራተኛውም ተደራጅቶ አሰሪውና መንግሥትም በጋራ ተወያይተው መፍትሔ ማምጣት ይኖርባቸዋል።

ማህበራዊ ምክክር ለምርት ማደግ ፋይዳው ከፍተኛ ነው።ማህበራዊ ምክክር ለሁሉም ችግር መፍቻ ቁልፍ ነው ብለን እንደተቋም እናምናለን። በመሆኑም እስከ ታች ድረስ ለጉዳዩ ትክረት ቢሰጠው መልካም ነው። እኛ ደግሞ ሠራተኛው የኢንዱስትሪ ዲሲፒሊን እንዲያውቅ በጋራ እንሠራ እያልናቸው ነው። ሠራተኛው ሲያጠፋ ብቻ አይደለም መጠየቅ ያለበት፤ ለሥራ ቅጥር ሲመጣም ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ሊሰጠው ይገባል። የሥራ ባህሉን እንዲያሻሽል ግንዛቤ መስጠት ያስፈልጋል።ሌሎች አገሮች ያደጉት ሠራተኛን አክብረውና ከእርሱም ጋር ተወያይተው በሚገኘው ጠቀሜታ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ለተመጣጣኝ ሥራ ተመጣጣኝ ክፍያ በመክፈሉ ረገድ እንደ አገር የት ላይ ነን? የሠራተኛውን ዝቅተኛ የደመወዝ መነሻ ለመወሰን የወጣው አዋጅ ከምን ደረሰ?**

**አቶ ካሳሁን፡-** ለተመጣጣኝ ሥራ ተመጣጣኝ ክፍያ በእኛ አገር የለም፤ እንዲያውም አይታወቅም።ምክንያቱም ሁሉም የሚከፍለው በራሱ መዋቅር እያጠና ነው።ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል ይወሰን ቢባልም እስካሁን ተግባራዊ አልሆነም፡፡

በአገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ በ2011 ዓ.ም የደመወዝ ወለል እንዲወሰን የሚጠይቅ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ወጥቷል።አዋጁን መተግበር የሚያስችል ደንብ ባለመውጣቱ፤ አዋጁ አራት ዓመት ቢያስቆጥርም እስካሁን ተግባራዊ አልሆነም።

በአሁኑ ወቅት ሠራተኛው እየተጋፈጠ ያለው የኑሮ ውድነት ግልጽ ከመሆኑ የተነሳ ማስረዳት አይጠበቅም።በዚህ የኑሮ ውድነት ውስጥ አንድ ሰው በወር 800 ብር ደመወዝ ተቀብሎ በእውነት እንነጋገር ከተባለ መኖር ያስችለዋልን? ምክንያቱም የሠራተኛው የወር ደመወዝ ዝቅተኛው 800፤ ከፍተኛው ደግሞ አንድ ሺ 200 ብር ነው።

አንድ ሺ 200 ቢሆን እንኳ ይህ ብር ከወር እስከ ወር ማድረስ ይችላል? ተብሎ ሲጠየቅ በዘርፉ ሰዎች የሚሰጠው ምላሽ ‹ይህ ሁሉ ሥራ አጥ ባለበት አገር ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል አይወሰንም› የሚል ነው። የወጣውን ሕግ አሰሪው በተቀበለበት ሁኔታ ተግባራዊ አለመደረጉ መልካም አይደለም።

አንዳንዶች የሚሉት ነገር ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል ከተቀመጠ ባለሀብቶች ብዙ ሰው አይቀጥሩም ይላሉ፤ እንዲያ ከሆነ ታድያ ኢንቨስትመንቱን ከመቀላቀሉ በፊት ያጠናው ነገር የለም እንደማለት ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ሥራ አጥ ስላለ ብቻ ብዙ ሠራተኛ በትንሽ ብር እቀጥራለሁ የሚባል ነገር የለም። ሥራው ራሱ በጥናት እና በእቅድ የሚመራ እንጂ በዘፈቀደ የሚካሄድ ባለመሆኑ ባስጠናው ጥናት መሠረት ነው መሠራት ያለበት።

**አዲስ ዘመን፡- የዝቅተኛ ደመወዝ ወለል መቀመጥ ጥቅሙ ምንድን ነው?**

**አቶ ካሳሁን፡-** የዝቅተኛ ደመወዝ ወለል መቀመጥ ምርታማነትን ይጨምራል።አንዳንዶች ‹የኢትዮጵያ ሠራተኛ ምርታማ አይደለም› ሲሉ ይደመጣሉ።እንዴ! በልቶ ከማያድር ሰው ነው እንዴ ምርታማነት የሚጠበቀው? በቅጡ በልቶ ከማያድር ሠራተኛ እንዴት ምርታማነት ይጠበቃል።በወር አንድ ሺ ብር ተከፋይ ሆኖ ይህን እየበላህ ምርታማ መሆን ይጠበቅብሃል ማለት ምን ማለት ነው?

መኖር የማይችል፤ መንቀሳቀስ የማይችል ሰው እንዴት ሆኖ ነው ምርታማ የሚሆነው። ስለቤት ኪራይና ስለሚበላ እያሰበ እንዴት ሆኖ ውጤታማ መሆን ይቻላል።በአሁኑ ወቅት ሠራተኛ በሚያገኘው የወር ገቢ መተዳደር እያቃተው ነው። እንዲያውም አሁን የተጀመረ ነገር ቢኖር አንዳንድ ሠራተኛ ቀን ቀን ሥራ ውሎ ወደማታ መለመን ጀምሯል። ከሆቴል ፍርፋሪ እየለመኑ የሚሠሩ እንዳሉም እናውቃለን።

አንዳንድ ሠራተኛ ደግሞ ምሳ ይዞ ወደሥራ ቦታው መሄድ ስለማይችል በምሳ ሰዓት ጥላ ስር ተቀምጦ ያሳልፋል። ወደሥራው የሚመለሰው ባዶ ሆዱን ነው።ይህ ሁኔታ ቢስተካከል ተብሎ ጥያቄ ሲነሳ ስንት ሥራ አጥ ባለበት አገር የሚል ምላሽ የሚሰጡ አካላት አሉ።ሰብዓዊነት ሊሰማቸው ግን ይገባል፡፡

በአሁኑ ወቅት ሌላው ቀርቶ የመንግሥት ሠራተኛው ራሱ መኖር አቅቶታል። እሱ ግን አብቃቅቶ በቀን አንድ ዳቦ ሊበላ ይችል ይሆናል። አሁንም መንግሥትን የምንጠይቀው ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል እንዲቀመጥ እንወያይ ብለን ነው፤ ችግር ካለም በውይይት መፍታት ይቻላል እንላለን።

**ያዘንኩበት ጊዜ ብዙ ነው፤ በተለይ ሠራተኛ በሚሠራበት ቦታ ከጥንቃቄ ጉድለት በሠራተኛው ላይ የሚደርሰው የሕይወት ኅልፈትና የአካል ጉዳት ውስጤን ያሳምመዋል**

**አዲስ ዘመን፡- የሥራ ግብሩን በአግባቡ እየከፈለ ያለው ሠራተኛ ብዙ ጊዜ የሥራ ግብሩ እንደበዛበት ሲናገር ይደመጣል፤ በዚህ ላይ ምን እየሠራችሁ ነው?**

**አቶ ካሳሁን፡-** የኑሮ ውድነቱ መናሩን ተከትሎ መንግሥትን ደመወዝ ጨምር ማለት አንችልም፤ ምክንያቱም የድሃ አገር ስለሆነ ከየትም እንደማያመጣ መረዳት አያዳግትም። ነገር ግን ከሚሰበስበው ግብር አስተያየት እንዲያደርግልን ነው የምንጠይቀው። ይህን ጥያቄ አቅርበን ጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ድረስ አስገብተናል፤ ምላሽ ግን እስካሁን አልተሰጠበትም።

ለሚመለከተው ለገንዘብ ሚኒስቴርም ደብዳቤ ጽፈናል።ነገር ግን ደብዳቤያችሁ ደርሶናል አሊያም አልደረሰንም የሚባል መልስ የለም።ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይዩት አይዩትም እስካሁን አላወቅንም። ጥያቄያችሁ ትክክል ነው ወይም አይደለምም መልስ ነበር፤ ግን ምንም የለም።ይህ አንድ ዓመት ሊሞላው ነው። ስለዚህ ከመጠበቅ ወደየለም ስለሄድን ተስፋ ቆርጠናል።እኛ የሥራ ግብር ይቀር ሳይሆን ማሻሻያ ይደረግበት ነበር።

ለምሳሌ 35 በመቶ የሥራ ግብር ከሚከፍሉት ላይ ቢያንስ ትንሽ ዝቅ ይበል ነው እያልን ያለነው።የኑሮ ውድነት አይሏል። እኛ በቻልን ጊዜ መንግሥትን እንደየአቅማችን ደግፈናል። ለምሳሌ የህዳሴ ግድብ ላይ እንደ ሠራተኛው ያዋጣ የለም። መንግሥትን ረዳን ማለት አገርን ረዳን ማለት ነው።መንግሥትን የሚረዳው ሠራተኛው ተርፎት ሳይሆን ለአገሬ በሚል ነው።

ገበታ ለአገር በሚለው ፕሮግራም ላይ ከእኛ ሴክተር ካሉ ድርጅቶች አንዱ ድርጅት ብቻ እንኳን የከፈለው አንድ ቢሊዮን ብር ነው።ይህም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሠራተኛ ነው። አሁን የኑሮ ጫና ሠራተኛውን እያስጎነበሰው ነውና ቀና ይል ዘንድ ልጅ ለአባቱ እንደሚናገረው ሁሉ እኛ ለመንግሥት እየተናገርን ነው፡፡

ለምሳሌ ከ500 ብር በላይ የሚከፈል ውሎ አበል ላይ ታክስ ይደረጋል። ይህ ግን የማደሪያ አልጋ ብሎም ምግብ ይችላል የሚለው በራሱ አጠያያቂ ነው። ስለዚህ ሰኞ በሰላማዊ ሰልፍ በምናከብረው የዓለም አቀፍ የሠራተኞች ቀን ላይ አንዱ ጥያቄ የሚሆነው ይህ ጉዳይ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በማኅበሩ የሥራ ቆይታዎ ያዘኑበት ጊዜ አሲያም አሳካቸዋለሁ ብለው የተደሰቱበት ጉዳይ ይኖር ይሆን?**

**አቶ ካሳሁን፡-** ያዘንኩበት ጊዜ ብዙ ነው፤ በተለይ ሠራተኛ በሚሠራበት ቦታ ከጥንቃቄ ጉድለት በሠራተኛው ላይ የሚደርሰው የሕይወት ኅልፈትና የአካል ጉዳት ውስጤን ያሳምመዋል። ከዚህ ውስጥ አንዱን ልጠቀስልሽ፤ በአንድ አጋጣሚ ለሥራ ጉዳይ ወደጅማ እየተጓዝኩ ለጊዜው ስሙን መጥቀስ ከማልፈልገው በአንድ ድርጅት ውስጥ ከሚሠራ የሠራተኞች ማኅበር ሊቀመንበር ስልክ ተደወለልኝ። የደወለልኝ የማኅበሩ ሊቀመንበር በጣም በማዘን ከዚህ ቀደም በድርጅቱ በአንድ ማሽን ላይ ተመድቦ የሚሠራ ልጅ እጅ በመቆረጡ መሥራት ስለማይችል ከሥራ መሰናበቱን አሳወቀኝ።በዚያው ቦታ ሌላ ሠራተኛ መመደብ የግድ ስለነበር ሌላ ሠራተኛ ቢመደብም በተመሳሳይ እርሱም እጁ በማሽን መቆረጡንና ከሥራ መልቀቁን ነገረኝ። ያው ስህተት ተደግሞ የሦስተኛ ሠራተኛ እጅ መቆረጡንና ከሥራ ውጪ መሆኑን አሳውቆኝ ለጊዜው በዚያ ቦታ እርሱ እየሠራ ስለመሆኑ ነገረኝ።በዚህ በጣም እያዘንኩ ወደጅማ አቀናሁ።ጅማ የነበረኝን ሥራ አጠናቅቄ ከመመለሴ በፊት ግን የዚያ የሠራተኞች ማኅበር ሊቀመንበር እጅ መቆረጡን ሰማሁ።ይህ በእውነት በጣም የሚያሳዝን ክስተት ሆኖብኛል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ብቻ ሳይሆን በሥራ ዘመኔ ባይሳካ አዝነ የነበረው የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ማጣታቸው ነው። እኔ ወደዚህ ኃላፊነት ከመምጣቴ በፊት በግል ድርጅት ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች አገልግለው ያለጡረታ ይሰናበቱ እንደነበር አስታውሳለሁ። እነዚህ ሠራተኞች መሠረታዊ የሆነ ጡረታ እንዲያገኙ እመኝ ስለነበረ ወደኃላፊነቱ ስመጣ የተሳካልኝ ነገር ቢኖር ይህ ነው ብዬ እላለሁ። ይህም የተሳካው በእግዚአብሔር ኃይል ነው፡፡

ሌላው ደስተኛ የሆንኩበት በ2008 እና 2009 ዓ.ም ጸድቆ ቢሆን ኖሮ ሠራተኛውን መጉዳት ብቻ ሳይሆን ባሪያ ያደርግ የነበረ የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ በመጀመሪያ እኛ ተወያይተንበት ወደሚኒስትሮች ምክር ቤት የተላከው ረቂቅ አንዳንዶች አስተካክለናል ባሉት መንገድ ጸድቆ ቢሆን ኖሮ ከባድ ነበር። በወቅቱ በረቂቁ ላይ ውይይት ከሚያደርጉት መካከል ‹‹ይህ አዋጅ ሠራተኛ ሠራተኛ ይሸታል፤ መልሱና ሌላ አዋጅ አምጡ›› ተብሎ ነበር።

ይሁንና አሰሪዎች፣ ሠራተኞችና የመንግሥት ተወካዮች በጋራ ተወያይተን የላክነው ረቂቅ ነው።ነገር ግን ይህ አይሆንም ተብሎ ሌሎች ረቂቁን እንዲያዘጋጁ ተደርጎ ወደእኛ ተላከ፤ በዚያ ረቂቅ ውስጥ የሰፈረው ነጥብ ሲታይ እርግጠኛ ሆኜ የምናገረው ሁሉም ሠራተኛ ተባራሪ እንደሚሆን ነበር።

ምክንያቱም በረቂቁ መሠረት የኢንዱስትሪ ሠራተኛው አንድ ቀን ከሥራ ከቀረ ይሰናበታል።በሌላ በኩል ደግሞ 14 ቀን የነበረው የዓመት እረፍት ወደ ሰባት ቀን ዝቅ እንዲል የተደረገበትም ረቂቅ ነበር። ሰባቱም ቀን ፈቃድ የሚሰጠው ደግሞ አሰሪው ከፈቀደለት ነው።ሌላው ቀርቶ ሁለት ቀን አንድ ሠራተኛ ካረፈደ ከሥራ ይባረራል የሚልም የተካተተበት ነበር።

የላኩልንን ረቂቅ በተመለከተ ለውይይት በጠሩን ጊዜ መቀበል አለባችሁ ብንባልም፤ አንቀበልም የሚል አቋም ያዝን።በወቅቱ ይህን ረቂቅ አስመልክተን መግለጫ እንኳ መስጠት የማይቻልበት የኢህአዴግ ሥርዓት ስለነበር እሱ ደግሞ ‹ቁረጠው› ነው መርሁ በሚል መግለጫውን ትተን በአገሪቱ ያሉትን ሠራተኞች ተከፋፍለን ለማወያየት ትግል ጀመርን።

ኢትዮጵያውያኑ ሠራተኞችም ለመብታቸው ለመታገል የሚታሙ አልነበሩምና ወደዚያው አቀናን፤ ይህን ስናደርግ ረቂቁ ከመጽደቁ በፊት መስተካከል እንዳለበት የሚገልጽ ደብዳቤ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት አስገብተን ስለነበር የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ጉዳዩ ለውይይት እንደሚቀርብ መልዕክት አስተላለፉልኝ። ጉዳዩም እርሳቸው እንዳሉት ወደውይይት ተመልሶ ባለበት ግማሽ ላይ እንደተደረሰ የለውጡ መንግሥት መጣ። ይሁንና ከቆምንበት በመጀመራችን የጥያቄያችን 95 በመቶ ምላሽ አግኝቷልና በዚህ ደስተኛ ነኝ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ዘንድሮው የዓለም አቀፍ የሠራተኞች ቀን በአገር አቀፍ ደረጃ የሚከበረው በምን ዓይነት መርሃግብር ነው?**

**አቶ ካሳሁን፡-** የዘንድሮውን በዓል ለየት የሚያደርገው በዓሉ የሚከበረው በአደባባይ መሆኑ ነው። አስቀድሜ ያነሳኋቸው የሠራተኛው ችግር እንዲቀረፍ በሰላማዊ መንገድ ለመንግሥት የሚቀርብበትም ይሆናል።ከዚህ ጎን ለጎን መንግሥት ለውይይት በሩን እንዲከፍትም የምንጠይቅበት ዕለት ነው።በዚህ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ የኑሮ ውድነቱ ላይ ትኩረት እናደርጋለን እንጂ የፖለቲካ አሊያም የተለየ የኃይማኖት ጥያቄ አናነግብም።

ጉዳዩን ለመንግሥት ከማሳወቅ ጎን ለጎን ከከንቲባ ጽሕፈት ቤትም ተፈቅዶልን ወደፖሊስ ደብዳቤ ተጽፎልናል።በመሆኑም አስፈላጊው ጥበቃ ይደረግልናል ማለት ነው።እኛም ጨዋነት የተሞላበት ሰልፍ እናካሂዳለን የሚል እምነት አለኝ።እንዲያውም በሰላማዊ ሰልፍ ሐሳብን ሥነ ምግባር በተሞላበት ሁኔታ እንዴት መግለጽ እንደሚቻል ሌላውም ከእኛ ይማራል ብለንም እናስባለን።የሰላማዊ ሰልፍ መሪ ሐሳብ ‹‹ለሠራተኛው ጥያቄ ምላሽ፤ ውይይት መፍትሔ›› ነው የሚል ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ እጅግ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ካሳሁን፡-** እኔም አመሰግናለሁ።የኢትዮጵያ ሠራተኞችን ለዓለም አቀፍ የሠራተኞች ቀን እንኳን አደረሳችሁ ማለት እወዳለሁ።

# ማህደረ ጤና

# ስጋት እየሆኑ የመጡት በሽታዎች

አስናቀ ፀጋዬ

በጤናም በኢኮኖሚም ከፍተኛ ጫና እያሳደሩ ከመጡ በሽታዎች ውስጥ ይመደባሉ። ከሰው ወደ ሰው አይተላለፉም። በጤና ላይ ጉዳት የሚያስከትሉትም ቀስ በቀስ ነው። አንዴ ከተከሰቱ መቆጣጠር እንጂ ማከም አይቻልም። እድሜ ዘለቅ መሆናቸው ደግሞ ረጅም የህክምና ክትትልን ይሻሉ። ለዚሁ የህክምና ክትትል የሚጠይቁት ወጪም ቀላል የሚባል አይደለም። በዝምታ ገዳይነታቸውም ወደር አልተገኘላቸውም። የሰዎችን ኪስ ከማራቆት በዘለለ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ መናጋት እያስከተሉ ይገኛሉ- ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች።

መረጃዎች እንደሚያሳዩት በኢትዮጵያ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች የሞት ምጣኔ 43 ከመቶ ደርሷል። እ.ኤ.አ በተጠና ጥናት ደግሞ አንድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ዋና ዋና በሚባሉት ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ያለእድሜው ወይም ከ70 አመት በፊት የመሞት እድሉ 18 ነጥብ 3 ከመቶ መሆኑ ተረጋግጧል። እ.ኤ.አ በ2018 የአለም ጤና ድረጅት በኢትዮጵያ በልብና በደም ቧንቧ በሽታ የሚሞቱ ሰዎች ቁጥር 47 ሺ 712 መድረሱን አረጋግጧል።

እ.ኤ.አ በ2015 ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ስቴፕ ዳሰሳ ጥናት መሰረት በኢትዮጵያ የደም ግፊት ስርጭት መጠን 16 ከመቶ መድረሱንና መከተሞች 22 በገጠር ደግሞ 13 ከመቶ መሆኑን አመላክቷል። የግሎባል በርደን ኦፍ ዲዚዝ በስትሮክ ላይ ባጠናው ጥናት በሽታው በኢትዮጵያ ሁለተኛ ደረጃን በመያዝ 44 በመቶ ለልብና ለደም ቧንቧ በሽታ እንደሚያጋልጥ አመልክቷል።

በሌላ በኩል እ.ኤ.አ በ2019 በተሰራ ጥናት በኢትዮጵያ ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች የሚከሰት ሞት 32 ነጥብ 4 መድረሱንና ከዚህ ውስጥ 14 በመቶ ያህሉ በልብና በደም ቧንቧ በሽታ፤ እንዲሁም 4 በመቶው በስኳርና ኩላሊት በሽታዎች እንደሚከሰት ታውቋል። እ.ኤ.አ ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ላይ በተሰራ የዳሰሳ ጥናት የስኳር በሽታ ስርጭት 5 ነጥብ 2 በመቶ መሆኑና ይህም በአዋቂዎች ላይ 3 ነጥብ 2 በመቶ መሆኑ ታውቋል።

በማእከላዊ ኢትዮጵያ በተደረገ የማህረሰብ አቀፍ ጥናት መሰረት ደግሞ የስኳርና የደም ግፊት በሽታዎች 25 በመቶ ለሚሆኑ የጎልማሶች ሞት ምክንያት እንደሆነ ተረጋግጧል። በተመሳሳይ እ.ኤ.አ በ2017 አለም አቀፉ የስኳር ህመም ፌዴሬሽን እንዳስታወቀው ኢትዮጵያ ከ2 ነጥብ 6 ሚሊዮን በላይ የስኳር ህመምተኞች ያሏትና በአፍሪካም በዚሁ በሽታ ከቀዳሚዎቹ ተርታ እንደምትመደብ ተጠቁሟል።

ምንም እንኳን እነዚህ መረጃዎች ትንሽ ቆየት ያሉ ቢሆንም በኢትዮጵያ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ጫና ከግዜ ወደ ግዜ እያደገ መምጣቱንና በነዚሁ በሽታዎች ምክንያት የሚሞቱ ዜጎች ቁጥር ከግዜ ወደ ግዜ እየጨመረ መምጣቱን ያመለክታሉ። በሽታዎቹ ያለግዜ ህመምና ሞት እንዲከሰት በማድረግ የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊ እድገት እያዘገዩ መሆናቸውንም ይጠቁማሉ።

ከነዚሁ በሽታዎች ጋር በተያያዘ እ.ኤ.አ አቆጣጠር በተሰራ ጥናት መንግስት ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች በየአመቱ የሚያወጣው ወጪ 4 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር መድረሱን አመልክቷል። በተለየ መልኩ ደግሞ ለልብና የደም ቧንቧ በሽታዎች 1 ነጥብ 97 ቢሊዮን ብር፣ ለካንሰር በሽታ 0 ነጥብ 98 ቢሊዮን ብር፣ ለስኳር በሽታ 0 ነጥብ 58 ቢሊዮን ብር እንዲሁም ስር ለሰደዱ የመተንፈሻ አካላት በሽታዎች በተመሳሳይ 0 ነጥብ 85 ቢሊዮን ብር ለህክምና ወጪ እንደሚያወጣ ጠቁሟል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ በበሽታዎቹ ምክንያት በስራ ላይ አቅም መቀነስና ሞት 26 ነጥብ 9 ሚሊዮን ብር በየአመቱ ወጪ እንደሚያደርግ ጥናቱ አሳይቷል። ይህም ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች በጤና ላይ ከሚያስከትሉት ጉዳት በዘለለ በሀገሪቱ ኢኮኖሚም ላይ በጎ ያልሆነ ተፅእኖ እያሳደሩ መምጣታቸውን ይጠቁማሉ።

ዶክተር ሙሴ ገብረ ሚካኤል በጤና ሚኒስቴር




ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ዋነኛው ጠንቅ ጤናማ የአኗኗር ስርዓት አለመከተል ነው፣

ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ከፍተኛ ባለሞያ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን መቆጣጠር ቢቻልም በህክምና ማዳን ግን አይቻልም። የእድሜ ልክ ክትትልም የሚሹ ናቸው። የነዚህ በሽታዎች ዋነኛ አጋላጭ መንስኤዎች ደግሞ ድህነት፣ ደካማ የአኗኗር ሁኔታ፣ማህበራዊ መገለል፣ የከተማ ዲዛይንና አኗኗር ሁኔታ ደካማ መሆን፣ የተለያዩ ሸቀጦች መተዋወቅና ለግብይት ቀላል መሆን ናቸው።

ከዚህ ባለፈ ጤናማ አመጋገብ አለመኖር፣ በቂ የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎችን አለማድረግ፣ ሲጋራ ማጨስ፣ ከልክ ያለፈ አልኮል መጠቀምና የመሳሰሉትም ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች ያጋልጣሉ። ከባህሪ ጋር የተያያዙ አጋላጭ መንስኤዎችም ለከፍተኛ የሰውነት ውፍረት፣ በደም ውስጥ ከፍተኛ መጠን ስኳር መጨመርና በደም ውስጥ ቅባት መጨመርም ለዋና ዋና ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች ይዳርጋሉ። ተላላፊ ያልሆኑ ከሚባሉት በሽታዎች ውስጥ ደግሞ የልብ ህመም፣ የስኳር ህመም፣ ስትሮክ፤ ካንሰር፣ ስር የሰደደ የመተንፈሻ አካላት ህመሞች ይጠቀሳሉ።

ዶክተር ሙሴ እንደሚሉት፣ ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ከሚከሰተው አጠቃላይ ሞት ከአስሩ ሰባቱ ተላላፊ በሆኑ በሽታዎች ምክንያት ይከሰታል። ከነዚህ ውስጥ የሳምባ ምች፣ ተቅማጥና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ። ነገር ግን ከአስሩ ሞቶች ውስጥ ሶስቱ የሚከሰቱት ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ነው። ከነዚህ ውስጥ ደግሞ ስትሮክ በቀዳሚነት ሲጠቀስ፣ የጉበት፣ ልብና ሌሎች ህመሞች ተከታዩን ደረጃ ይይዛሉ። እነዚህ በሽታዎችም እ.ኤ.አ በ2019 በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመሩ መጥተዋል። ከዚህ በተቃራኒ ግን ተላላፊ የሆኑ በሽታዎች እ.ኤ.አ በ2018 ከነበሩበት እ.ኤ.አ በ2019 ቅናሽ አሳይተዋል።

በኢትዮጵያ የልብና የደም ስር በሽታዎች ዋነኛ ገዳይ መንስኤዎች ውስጥ ስትሮክ አንዱ ሲሆን ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ለሚከሰቱ ሞቶች 12 ከመቶውን ድርሻ ይወስዳሉ። ከዚህ አንፃር የልብና ደም ስር በሽታዎች 33 ነጥብ 4 በመቶ ለሚሆነው ሞት እንዲከሰት የሚያደርጉት በዋናነት ጤናማ የአመጋገብ ስረዓት አለመኖር ነው። በከፍተኛ ደረጃ ጨው መጠቀም ደግሞ ለነዚህ የልብና የደም ስር በሽታዎች በማጋለጥ ረገድ 11 ከመቶ ያህል ድርሻ ይወስዳሉ።

በቅርብ በተጠና ጥናት ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ላይ ትኩረት አድርጎ መሰራት በተለይ ደግሞ በጤና ተቋማት የሚሰጡ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ህክምና አገልግሎቶችን በማሳደግና በፖሊሲ ማሻሻያዎች 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሞትን መከላከል ወይም ሰዎች ያለእድሚያቸው እንዳይሞቱ ማድረግ እንደሚቻል ታውቋል። ነገር ግን ከ1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሞት ውስጥ አንድ ሶስተኛውን ጨውን ከልክ ባለፈ መልኩ ባለመመገብና የጨውን ፍጆታ በመቀነስ መቀነስ ይቻላል።

በቀላሉ ጨው አጠቃቀም ላይ ብዙ ቢሰራ ለውጥ ማምጣት ይቻላል እንደማለት ነው። በተጨማሪ ደግሞ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በስትሮክ አማካኝነት የሚከሰተውን አካል ጉዳተኝነትንም አብሮ መቀነስ ይቻላል። ይህም የልብና ደም ስር እና የስኳር ህመሞች ላይ የሚሰሩ ወጪ ቀናሽ የመከላከል ስራዎች ወሳኝ መሆናቸውን ያመለክታል።

ለአብነትም ጥናቱ የልብና ደም ስር በሽታዎችና የስኳር ህመም እንዲህ አይነቱ የመከላከል ስራ ቢሰራ 129 ሺ 522 ስትሮክ ህመሞችን መቀነስ ወይም ማስወገድ ይቻላል። በተመሳሳይ 96 ሺ 654 የልብ ህመሞችን መቀነስ ወይም መከላከል ይቻላል። 352 ሺ 693 በስትሮክ አማካኝነትና በልብ ህመም አማካኝነት የሚከሰተውን ሞት መከላከል ይቻላል። በጥቅሉ ደግሞ 1 ሚሊዮን 116 ሺ 896 ጤናማ ህይው እንዲያገኙ ማድረግ ይቻላል።

በሌላ በኩል ደግሞ በጨው ላይ ተመሳሳይ ስራዎች ቢሰሩ 442 ሺ 886 ስትሮክ በሽታን መቀነስና መከላከል ይቻላል። 189 ሺ 871 የልብ ህመምንም መቀነስ ይቻላል። 454 ሺ 954 ሞትን መቀነስ ወይም መከላከልም ያስችላል። ወደ 3 ሚሊዮን የሚጠጉ ጤናማ ህይወትን ሠዎች እንዲያገኙ ማድረግ እንደሚቻል ጥናቱ አሳይቷል።

ዶክተር ሙሴ እንደሚያብራሩት ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች በጤና ላይ ከሚያደርሱት በጎ ያልሆነ ተፅእኖ ባሻገር በዚሁ ጥናት መሰረት በአስራ አምስት አመት ውስጥ ተላላፊ በሽታዎችን ለማከምና በነርሱ ላይ ለመስራት 242 ቢሊዮን ብር ኢንቨስትመንት እንደሚጠይቅ አመላክቷል። ከዚህ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስደው በሆስፒታሎችና ጤና ተቋማት ጋር የሚሰራው ስራ ነው።

የልብና የደም ስር ህመሞች ወይም ደግሞ ከፍተኛ የደም ግፊት ላይ የሚሰራው ስራና በስኳር ህመም ላይ በአስራ አምስት ዓመት ውስጥ የሚሰሩት ስራዎች 221 ቢሊዮን ብር ይፈልጋሉ። በአስራ አመስት አመት ውስጥ በጨው ቅነሳ ላይ ቢሰራ ደግሞ 6 ቢሊዮን ብር ወጪ ብቻ ያስፈልጋል። ይህም ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለመቀነስ በሚደረገው ጥረት ምን ያህል ወጪ እንደሚወጣ ይጠቁማል።

242 ቢሊዮን ብር ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ቅነሳ ስራ ወጪ ሲደረግ ትርፉ 62 ቢሊዮን ብር ብቻ ይሆናል። ነገር ግን ጉዳዩ ከብር አንፃር ብቻ ሳይሆን ህይወትን ከማዳን አኳያም መታየት ይኖርበታል። ለአብነትም የጨው ፍጆታን ለመቀነስ በአስራ አምስት አመት ውስጥ 6 ቢሊዮን ብር ቢወጣ 455 ሺ ሰው ማትረፍ ይቻላል። የልብና የደም ስር ህመሞች ወይም ደግሞ ከፍተኛ የደም ግፊትን ለመቀነስ 221 ቢሊዮን ብር ወጪ ቢደረግ ወደ 353 ሺ የሚሆኑ ሰዎችን ከሞት መታደግ ይቻላል። ከዚህ አንፃር እንዲህ አይነቱ የፖሊሲ ኢንተርቬንሽን በጣም አዋጭ ይሆናል።

ዶክተር ሙሴ እንደሚገልፁት ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የሚሳድሩት አሉታዊ ተፅእኖ እየጨመረ መጥቷል። 2 ከመቶ የሚሆኑውን የሀገሪቱን አመታዊ የተጣራ ምርትም ይወስዳሉ። ኢትዮጵያ ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ምክንያት 31 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር በየአመቱ ታጣለች። ከዚህ ውስጥ 26 ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ምክንያት በተዘዋዋሪ የምታጣው ወጪ ነው።

ከዚህ አንፃር ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች በተዘዋዋሪ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ጫና እያሳደሩ መሆኑን ያሳያል። ለአብነትም በልብና በደም ስር በሽታዎች እንዲሁም በስኳር ህመም እየማቀቁ ያሉ ዜጎች ከስራ ሲቀሩ 1 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር ሀገሪቱን ወጪ ያስወጣሉ። ታማሚዎቹ ስራ ላይ ተገኝተው ስራቸውን በአግባቡ ባለመስራታቸው ምክንያት 14 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር ሀገሪቱን ያሳጣታል። ምርታማነትንም ይቀንሳል። በነዚህ ህመሞች ሞት ምክንያት ደግሞ 10 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር ሀገሪቱን ያስወጣታል። በጥቅሉ ተዘዋዋሪ ወጪ ሀገሪቱን 26 ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር ያስወጣታል።

በሌላ በኩል ደግሞ ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ምክንያት ቀድሞ ያለእድሜ መሞት ኢትዮጵያን ብዙ ወጪ እያስወጣት ይገኛል። በዋናነት ሀገሪቱ በልብና የደም ሥር በሽታዎች ምክንያት በሚከሰት ቀድሞ ያለእድሜ መሞት ከፍተኛ ወጪ ታወጣለች። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በካንሰር ምክንያት የሚከሰት ቀድሞ ያለአድሜ ሞት ሀገሪቱ ወጪ ታወጣለች። በስኳርና ስር በሰደደ የመተንፈሻ ችግር ግን ሀገሪቱ ብዙ ወጪ አታወጣም። ይህም ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች በጤና ላይ ከሚያደርሱት ጉዳት ባለፈ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያደርሱት ተፅእኖ ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል።

ከ15ኛው ገጽ የዞረ

ሲሉ ሙሉ ጊዜያቸውን፣ ጤናቸውን በመጨረሻም የማይተካውን ውድ ሕይወታቸውን ሰውተዋል፤ በመሆኑም የክቡር አቶ ግርማ የሺጥላ ጉልህ አገራዊና መንግሥታዊ አበርክቶ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ታሪክ ማህደር ፈፅሞ የሚዘነጋ አይሆንም። ታሪክ መዝግቦ የሚይዘው ይሆናል።

የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በክቡር አቶ ግርማ የሺጥላና በግል ጠባቂዎቻቸው በደረሰው አደጋ የተሰማውን ኀዘን ይገልፃል፤ ለወገኖቻችን ሞት ምክንያት የሆነውንም አሳፋሪ ፅንፈኛ ድርጊትና ጥቃት በፅኑ አውግዟል።

ለቤተሰቦቻቸው፣ ለወዳጅ ዘመዶቻቸውና ለሥራ ባልደረቦቻቸው በሙሉ መፅናናትን ይመኛል።

**የኢፌዴሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት**
**ሚያዝያ 20 ቀን 2015 ዓ.ም**

## - ከመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት የተሰጠ መግለጫ፡-

የጽንፈኝነትን ሰይጣናዊነት ያሳየ የግፍ ግድያ!

ጽንፈኝነት ብዙዎችን የሕዝብ ልጆች አሳጥቶናል። ጽንፈኞች ሰው መሆንን ይጠየፋሉ። ዛሬ የአማራ ክልል የብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ እና የፓርቲው ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ግርማ የሺጥላ ባደገበት ቀዬ በጽንፈኞች በግፍ ተገድሏል። ይህም የጽንፈኛው ኃይል የመርዝ ፖለቲካ በቀዬ የማይወሰን፣ ከጓዳ ጭምር ገብቶ ቤተሰብን የሚበትን መሆኑን አሳይቶናል።

**ውዱ የኢትዮጵያ ሕዝብ!**

አጀንዳ አልባ የጥላቻ ፖለቲካ ዘርተው ጽንፈኝነትን በማብቀል ልጆችህን በየአደባባዩ የሚቀጥፉ የደም ነጋዴዎችን ማስቆም ካልቻልክ፣ የግፍ በትራቸውን የብዙኃኑን ቤት ማንኳኳቱ አይቀሬ ነው።

ዓላማቸው ማተራመስና አገራችንን ዕረፍት መንሣት የሆኑ አካላት አሉ። የእነዚህ አካላት አርአያዎቻቸው ዓለም አቀፍ አሸባሪዎች ናቸው። የእነርሱን ተግባር በኢትዮጵያ ለመድገምና ኢትዮጵያን ለማጥፋት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ያልተፈጸሙ ዘግናኝ ተግባራትን ሁሉ ይፈጽማሉ።

ኢትዮጵያን ለማጽናትና ለማበልጸግ የጀመርነውን ትግል ጽንፈኞች አያስቆሙትም። ይሄንን ነውረኛ ዘግናኝ ተግባር የፈጸሙት የትም ቢገቡ ለሕግ ይቀርባሉ። ሌሎች በእነርሱ መንገድ መጓዝ የጀመሩ በሕግ ማስከበር እንዲቆሙ ይደረጋል።

**ነብስህ በሰላም ትረፍ!**
**ሚያዝያ 19 ቀን 2015 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ**
**የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት**

## - የብልጽግና ፓርቲ የኀዘን መግለጫ፡-

የፓርቲያችን ሥራ አስፈፃሚ አባል እና የአማራ ክልል ብልፅግና ጽ/ቤት ኃላፊ የሆኑት በአቶ ግርማ የሺጥላ በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ልዩ ቦታው መንዝ ጓሳ በተባለ አካባቢ ለሥራ እየተንቀሳቀሱ ባሉበት ወቅት በታጠቁ ፅንፈኞች በደረሰባቸው ጥቃት ሕይወታቸው አልፏል።

የብልጽግና ፓርቲ ዋና ጽሕፈት ቤት የተሰማንን መሪር እና ጥልቅ ኀዘን እየገለጽን ለመላ ቤተሰቦቹና ባልደረቦቹ ፈጣሪ ያፅናችሁ ማለት እንወዳለን።

ለመላ የአማራ ሕዝብ፣ ለፓርቲያችን አባላትና ደጋፊዎች በሙሉ መጽናናትንም እንመኛለን። ፓርቲያችን የአቶ ግርማ የሺጥላን ገዳዮች በአፋጣኝ ተከታትሎ ለሕግ እንደሚያቀርብ እና በፍትህ አደባባይም ደሙን በፍትህ እንደሚመልስ ለማረጋገጥ እንወዳለን።

በሃሳብ የተለየን ሰው በሃሳብ ሞግቶ፤ በአመለካከት የተለየን በአመለካከት ረትቶ መነጋገርና የሚበልጠውን የሚበጀውን ለአገርና ለወገን ፍሬ የሚያፈራውን ሃሳብ ማስፋትና ማሳደግ ሲቻል የሰውን ልጅ የመሰለ ክቡር ፍጡር:፣ ያውም እንደ ግርማ የሺጥላ ዓይነቱን የአገር- የሕዝብና የወገን አለኝታ የሆነ ምሁር ፖለቲከኛ በእንዲህ ዓይነት መልኩ መግደል መሸነፍ መሆኑን አሁንም ደግመን መናገር እንፈልጋለን።

የአቶ ግርማን በፅንፈኛ ኃይሎች ጥቃት መቀጠፍ ስንሰማ ልባችን በኀዘን ደምቷል። በዚያውም ልክ ፅንፈኝነትን አምርረን መታገልና ማክሰም ጊዜ የማይሰጠው ተግባር እንደሆነ አሳይቶናል።

በአገራችን እየታየ ያለው የፅንፈኝነት አስተሳሰብ እና ከአስተሳሰቡ የሚነጩ እኩይ ድርጊቶች ከፍተኛ አደጋ ውስጥ ሊከቱን እንደሚችሉ ምንም ጥያቄ የለውም። በመሆኑም ብልፅግና ፓርቲ ምልዓተ ሕዝቡን ያሳተፈ ጠንካራ የፖለቲካ ትግል በማድረግ እና ሕግ የማስከበር እርምጃዎችን በማጠናከር ጽንፈኝነትን ለመግታት ከምንጊዜውም በበለጠ ጠንክሮ እንደሚሠራ በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ እንወዳለን።

የብልፅግና ጉዟችን በጽንፈኞች እና ሌቦች እኩይ ተግባር ፈፅሞ አይደናቀፍም!

ወንድማችን ግርማ የሺጥላ ነፍስዎት በአፀደ ገነት ትረፍ!

**ብልፅግና ፓርቲ**
**ሚያዝያ 19/2015**

## - ከአማራ ክልል ምክር ቤት የተሰጠ መግለጫ፡-

የተከበሩ አቶ ግርማ የሺጥላ ሚያዝያ 19/2015 ዓ.ም የመንግሥትና የድርጅት ሥራዎችን በሰሜን ሸዋ ዞን ሠርተው ከመሀል ሜዳ ወደ ደብረ ብርሃን ሲመለሱ ልዩ ቦታው መንዝ ጓሳ አካባቢ በአማራ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን ባሶና ወረና ወረዳ ቀይት ምርጫ ክልልን ወክለው የተመረጡት የክልል ምክር ቤት አባል፣ የብልፅግና ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ አባል እና በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የብልፅግና ፓርቲ የአማራ ክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ በተከበሩ አቶ ግርማ የሺጥላ እና የግል ጥበቃዎቻቸው ላይ በታጠቁ ፅንፈኛ ኃይሎች በደረሰባቸው ጥቃት የተሰማን ኀዘን መራራ ነው።

የአማራ ክልል ምክር ቤት ለሟቾች ቤተሰብ፣ ወዳጅ ዘመድ እና መላው ሕዝብ መጽናናትን ይመኛል።

**የአማራ ክልል ምክር ቤት**
**ባሕር ዳር**

## - የኦሮሚያ ብልጽግና ፓርቲ መልዕክት፡-

ብሩህ ራዕይ በሀሳብ ድሆች አይሞትም!

የፖለቲካ አመለካከትን በዕውቀትና በእውነት ማራመድ የተሳናቸው የሀሳብ ድሆች ማሰብ የሚችሉ ባለ ብሩህ ራዕይ ሰዎችን ማጥቃት ብቸኛ አማራጫቸው ነው።

ግርማ የሺጥላ የኢትዮጵያውያንን ህብረ ብሔራዊ ወንድማማችነትና እህትማማችነት ለማጽናት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል ቀን ከሌሊት ሲሠራ የነበረ የቁርጥ ቀን የኢትዮጵያ ልጅ ነበር።

ሀሳብ የነጠፈባቸው ጽንፈኛ ብሔርተኞች ሰላማዊውን የሀሳብ መድረክ መቋቋም እንደማይችሉ ስለሚያውቁ ኢትዮጵያን የሰላምና የልማት ምድር ለማድረግ ዕድሜውን ሙሉ የለፋውን ብርቱ መሪ በልተውታል።

ወንድማችን ግርማ በሙሉ አቅሙ የታገለው ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ብሔሮች፣ ሃይማኖቶችና ሌሎች ማንነቶች እኩልነትና ለዜጎች ነፃነት ነበር። ይህ ያልተዋጠላቸው የሀሳብ ቆሞ ቀሮች ብሩ ሀሳብን በጥይት መግደል የሚቻል መስሏቸው ተራማጅ ሀሳብ የነበረውን ባለ ጽኑ አቋም መሪ ሕይወት ቀጥፈዋል።

ይህን አስነዋሪ የወንጀል ድርጊት በፈጸሙ ጽንፈኛ ወንጀለኞች ላይ የሚወሰደው እርምጃ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።

አክራሪነትንና ጽንፈኝነትን በሀሳብ የበላይነት እያመከንን በኢትዮጵያውያን መካከል አስተማማኝ ህብረ ብሔራዊ አንድነትን፣ የሕዝቦችን እኩልነት፣ ነፃነትና ወንድማማችነትን ለማረጋገጥ የሚደረገው የሕዝቦች ትግል ተጠናክሮ ይቀጥላል።

ወንድማችን ግርማ ነፍስህ በሰላም ትረፍ!

## - የከንቲባ አዳነች አቤቤ መልዕክት፡-

የአማራ ክልል ብልጽግና ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ በነበሩት አቶ ግርማ የሺጥላ መሰዋት እጅግ አዝኛለሁ።

ግርማ ላመነበት የወንድማማችነትና ህብረብሔራዊ አንድነት አላማ በጀግንነት የታገለ የአቋም ሰው ነው።

ግርማን መግደል ብትችሉም ሀሳቡንና የቆመለትን አላማ መግደል አትችሉም። የጽንፈኝነት ተሸናፊ ሀሳብ እየሞተ የወንድማማችነት ሀሳብ አሸናፊ ሆኖ ይቀጥላል።

ለቤተሰቦቹ ፣ ለወዳጆቹ እና ለሥራ ጓዶቹ መጽናናትን እየተመኘሁ ፈጣሪ ነፍሱን በአፀደ ገነት ያሳርፈው።

## - ከሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የተሰጠ የኀዘን መግለጫ፡-

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የብልፅግና ፓርቲ ሥራ አስፈፃሚ አባልና የአማራ ክልል ብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ግርማ የሺጥላ በፅንፈኛ ኃይሎች በደረሰባቸው ጥቃት ሕይወታቸው በማለፉ የተሰማውን ጥልቅ ኀዘን ይገልጻል።

የጥፋት መንገድን በተከተሉ፣ የአገርን ሉዓላዊነት ክብር ለማዋረድ ሌትተቀን በሚዳክሩ ኃይሎች ቅንጣት ታክል ትግላችንንና ሰላማችን አይቀለበስም።

እነዚህ ፅንፈኛ ኃይሎች በሰለጠነ መንገድ ፖለቲካዊ አካሔዳቸውን ማስፈፀም የማይችሉና ሁልጊዜ ፀብና ግጭት በመፍጠር አጀንዳቸውን ለማስፈፀም ነፍጥ የሚያነሱ ከዘመኑ ፖለቲካ ስልጣኔ አንፃር ችግሮቻቸውን በውይይት ለመፍታት አቅም የሌላቸው ፤ የህብረ ብሔራዊት ኢትዮጵያን ከፍታና አንድነት ለመናድ የሚታትሩ የአገር ጠላቶች ናቸው።

እነዚህ ፅንፈኛ ኃይሎች በፈፀሙት የወንጀል ድርጊት መላው የክልላችን ሕዝብና መንግሥት የተፈጠረውን አስነዋሪና አፀያፊ ድርጊት ከማውገዝ ባሻገር ወንጀለኞች ለሕግ ቀርበው ፍትህ እስኪረጋገጥ ድረስ ከወንድም አማራ ሕዝብና መንግሥት ጎን እንደሚቆም የክልሉ መንግሥት ያረጋግጣል።

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ለቤተሰቦቻቸው፣ ለወዳጆቻቸውና ለሥራ ባልደረቦቻቸው እንዲሁም ለመላው አማራ ሕዝብ የተሰማውን ጥልቅ ኀዘን ይገልጻል።

**ፈጣሪ ነፍሳቸውን በአፀደ ገነት ያሳርፍልን!!**
**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት**

## - የሶማሌ ክልል ርእሰ መስተዳድር አቶ ሙስጠፌ ሙሁመድ መልዕክት፡-

የሶማሌ ክልል ርእሰ መስተዳድር አቶ ሙስጠፌ ሙሁመድ በአማራ ብልፅግና ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ግርማ የሺጥላ ግድያ የተሰማቸውን ጥልቅ ኀዘን የገለጹ ሲሆን፤ ርእሰ መስተዳድሩ ኀዘናቸውን በገለፁበት መልእክታቸው፤ የትኛውም የፖለቲካ ልዩነት በአፈሙዝ መፍታት ጊዜ ያለፈበት ብቻ ሳይሆን ካለፍንባቸው የሩቅ እና የቅርብ ታሪኮቻችን መማር አለብን ብለዋል።

በአሁኑ ሰዓት አገራችን የአመለካከት ልዩነቶችን በሰላማዊ መንገድ እና በውይይት እንጂ በሙሣሪያ አፈሙዝ መፍታትን የምትሸከምበት ጫንቃ የላትም ሲሉም አሳስበዋል።

ለሟች ቤተሰቦች፣ ለመላው የአማራ ክልል ሕዝብ እና ለወዳጅ ዘመዶቻቸው መፅናናትን በመመኘትም፤ አሁን መላው ሕዝብ ይህን ግድያ መቃወም እና በቃ ሊባል እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

## - የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል መንግሥት ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ኢንጂነር ነጋሽ ዋጌሾ መልዕክት፡-

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የብልጽግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ በነበሩ በወንድሜ በአቶ ግርማ የሺጥላ ድንገተኛ ሞት የተሰማኝ ኀዘን በጣም ጥልቅ ነው::

አቶ ግርማ በሃሳብ ልዕልና የሚያምኑ፣ ለአገራዊ አንድነትና ለሕዝቦች ወንድማማችነት የሚታገሉ ኢትዮጵያዊ ነበሩ::

ለሥራ ባልደረቦቹ፣ ለወዳጅ ዘመዶቹና ለቤተሰቦቹ መጽናናትን እመኛለሁ::

ወንድሜ ነፍስህ የዘላለም እረፍት እንድታገኝ ፀሎቴ ነው::

## - የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ መልዕክት፡-

አክራሪ ኃይሎች ታታሪና ጀግና የሕዝብ አገልጋይ የነበረውን ወንድማችን አቶ ግርማ የሺጥላን ነፍስ ነጥቀዋል። ለሐሳብ ልዕልና በሐሳብ ሲታገል የነበረውን፣ በሙሣሪያ ቃታ መግደል የእነዚህን ኃይሎች መሸነፍ የሚያረጋግጥ ይሆናል እንጂ፤ የሕግ የበላይነት የተረጋገጠባትና ሀሳብ የሚከበርባት አገር ከመመስረት ለአፍታም ቢሆን የሚያቆመን አይሆንም።

አክራሪዎች በዚህ ዘመን ውስጥ በሀሳብ ሳይሆን፣ በአፈሙዝ ለማሸነፍ እንዲሁም በጦርነት ስልጣን ለመያዝ ሊያስቡ ይችላሉ፤ በተጨባጭ ግን የዚህ ዓይነቱ አስተሳሰብ በዚህ ዘመን አይሠራም። ወንድማችን የአማራ ክልል ብልፅግና ፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ግርማ የሺጥላ፣ ጠንካራ አመራርና በሀሳብ የበላይነት የሚያምን እና ይህን ለማረጋገጥ ሲተጋ የቆየ ነበር።

በድንገተኛው የአቶ ግርማ የሺጥላ ህልፈት የተሰማኝን ጥልቅ ኀዘን ስገልጽ፣ በተሰበረ ልብ ነው። ለቤተሰቦቹ፣ ለወዳጅ ዘመዶቹ፣ ለሥራ ባልደረቦቹና የትግል አጋሮቹ እንዲሁም ለመላው ሕዝባችን መፅናናትን እመኛለሁ።

ነፍስህ በሰላም ትረፍ።

## - የደቡብ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ርስቱ ይርዳው መልዕክት፡-

የደቡብ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ርስቱ ይርዳው የአማራ ክልል ብልጽግና ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ በነበሩት በአቶ ግርማ የሺጥላ ህልፈተ ሕይወት የተሰማቸውን ኀዘን ገልጸዋል።

አቶ ርስቱ ይርዳው በኀዘን መግለጫቸው፤ «አክራሪ ኃይሎች ታላቅ የሕዝብ አደራን ተቀብለው በጀግንነት እና በታታሪነት አገራቸውን እና ሕዝባቸውን በቅንነት ሲያገለግሉ የነበሩትን መሪ እንድናጣ ምክንያት ሆነዋል» ብለዋል።

አሁን ባለንበት ዘመን ልዩነት በምክክር እና በውይይት መፍታት ሲቻል የሙሣሪያ አፈ ሙዝን በመፍትሄነት መጠቀም ተስፋ ቢስነትን ያመላክታል ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ ጀግናችንን በሞት ብንነጠቅም እንደ አገር የጀመርነው የልማትና የእድገት ጉዞ ላፍታም ሊገታ አይችልም ነው ያሉት።

አክራሪ ኃይሎች በአቋራጭ ስልጣን ለመያዝ ያልፈነቀሉት ድንጋይ እንደሌለ ጠቁመው መግደልን አማራጭ ማድረጋቸው ምን ያህል በሕዝብ ደም የመነገድ ፍላጎት እንዳላቸው ማሳያ መሆኑን ጠቁመዋል።

አቶ ግርማ የሺጥላ በሥራ ክቡርነት የሚያምኑ የተጣለባቸውን የሕዝብ አደራ በብቃት እየተወጡ የነበሩ ጠንካራ አመራር መሆናቸውንም በኀዘን መግለጫቸው ገልጸዋል።

ለቤተሰቦቻቸው፣ ለወዳጅ ዘመዶቻቸው፣ ለሥራ ባልደረቦቻቸው፣ ለትግል አጋሮቻቸው እንዲሁም ለመላው ሕዝብም መፅናናትን ተመኝተዋል።

## - የሐረሪ ክልላዊ መንግሥት የኀዘን መግለጫ፡-

የሐረሪ ክልላዊ መንግሥት በአማራ ክልል ብልጽግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ በነበሩት አቶ ግርማ የሺጥላ ህልፈት የተሰማውን ጥልቅ ኀዘን የገለጸ ሲሆን፤ የክልሉ መንግሥት ባወጣው የኀዘን መግለጫ የፖለቲካ አመለካከትን በዕውቀትና በእውነት ማራመድ የተሳናቸው የሀሳብ ድሆች ማሰብ የሚችሉ ባለ ብሩህ ራዕይ ሰዎችን ማጥቃት ብቸኛ አማራጫቸው ነው ብላል።

በዚህ ዘመን ሐሳብን በሐሳብ ማሸነፍ ያቃታቸው አካላት ልዩነትን በሠለጠነ መንገድ መፍታት ባህል በሆነበት ክፍለ ዘመን፣ በሐሳብ የተለየንን ሁሉ በጠመንጃ ለማሳመን መነሣት የጽንፈኝነት የመጨረሻው ጥግ ማሳያ መሆኑን በመግለጽም፤ የክልሉ መንግሥት ለቤተሰቦቻቸውና ለወዳጅ ዘመዶቻቸው እንዲሁም ለመላው የአማራ ክልል ሕዝብ መፅናናትን ይመኛል ብሏል።

## - የአማራ የምሁራን መማክርት ጉባዔ፡-

በአማራ ክልል የምሁራን መማክርት ጉባዔ በአቶ ግርማ የሺጥላ ላይ በታጠቁ ኃይሎች የተፈፀመውን ግድያ በፅኑ በማውገዝ የተሰማውን ጥልቅ ኀዘን በመግለጽ፤ የሐሳብም ሆነ የፖለቲካ ልዩነቶችን በኃይልና በመግደል ለመፍታት መሞከር ለሕዝባችን እና አገራችን ዘለቄታዊ ሰላም አያመጣም ብሏል።

የምሁራን መማክርት ጉባዔው ለኢቢሲ በላከው መግለጫ ለቤተሰቦች እና ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥትና ሕዝብ መፅናናትን ተመኝቷል።

# በሕጋዊነት ሽፋን የተፈፀመው ዘረፋ



አስመረት ብስራት

አንድ ማለዳ ነው፤ ከእነአቶ ሽለመ ማስረሻ ቤት እልልታ ተሰማ። እልልል..... እልልልልል....... እልልልልል...ገና ጎህ ሲቀድ መንደሯን የሚያናጋ እልልታ መሰማቱ ያልተለመደ ነበር፡፡ ሁሉም ከየቤቱ ብቅ ብቅ እያለ የሆነውን ለማየትና ለመሰማት ይጣደፍ ጀመር። ለዘመናት የልጅ ጠረን ሸቶበት የማያውቀው የአቶ ሽለመ ቤት የበኩር ልጅ የሆነችው ጽጌ ሽለመ ያለምንም ጭንቀት በቀላል ምጥ ከእናቷ ማህፀን ወጥታ መሬት ስትረግጥ ነበር፡፡ ጎረቤቶች ደስታቸውን ለመግለፅ እልልታቸውን አቀለጡት። የፅጌ ወላጆች ለአመታት ልጅ ለማግኘት ያልሄዱበት ሀኪም ቤት ያልረገጡት ደጀ ሰላም አልነበረም፡፡ ይህችን ብርቅዬ የፈጣሪ ስጦታቸውን ተቀብለው በደስታ ማሳደግ ጀመሩ።

ፅጌ ለቤቱ ብቸኛ ልጅ ነበረች። የብርቅ ልጅ፤ አፈር አይንካሽ ተብላ ያደገችው ልጅ ሁሉንም ማግኘት መብቷ እንደሆነ እስኪሰማት ድረስ የጠየቀችው ሁሉ ተደርጎላት አደገች። ምንም እንኳን ገቢያቸው አነስተኛ ከሆኑ ቤተሰቦች ቤት ብትወለድም ከአካባቢው ልጆች በተለይ ተሞላቃ ቀብጣ አደገች።

ልጅቱ ዕድሜዋ እየጨመረ ሲሄድ፤ የምትፈልጋቸው ነገሮች በወላጆቿ አቅም የማይሆን በመሆኑ ያቺ አፈር አይንካሽ ተብላ ያደገችው ልጅ ጭቅጭቅ ጀመረች። ፍላጎቷ ሳይገደብ ያደገችው ወጣት በልክ ስትባል እምቢኝ አሻፈረኝ በማለት ከቤት ወጥታ ውሎ አዳሯ ሁሉ ከምታውቃቸው ከዱርዬዎች እና ከሱሰኞች ጋር ሆነ። ወጣቷ ለለመደቻቸው አጉል ሱሶች ገንዘብ ያስገኛል ብላ ያሰበችውን ነገር በሙሉ መሞከር ጀመረች።

በእዚህ ተግባሯም እንደዛ በደስታ እያነቡ የተቀበሏትን ቤተሰቦቿን በኀዘን አስነባቻቸው። በእልልታ ያወጁትን የልጅ ማግኘትን ብስራት፤ አንገት በመድፋት እንዲታዩ አደረገቻቸው። የለየላት ሌባ ሆነች። ነጋ ጠባ ስሞታ ቤት ድረስ ይመጣ ጀመር። ይህ ባህሪዋ አድጎ ከወንጀለኞች ቡድን ጋር አስተዋወቃት። በዚህም የበርካቶችን ንብረት ቀምታ ላልተገደበው ፍላጎቷ ማስፈፀሚያ አደረገችው። የበርካቶችን የወዝ ውጤት ምንም ሳትሳቀቅ የራሷ አደረገች። ለእዚህ እኩይ ተግባሯ ሌላ ምቹ ሁኔታ ተፈጠረላት። በአገሪቱ የነበረውን ወቅታዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ለዘረፋ የሚሆን ምቹ ሁኔታ ታመቻች ጀመር።

## የደከሙበትን የተነጠቁት አባት

አቶ ፍፁም ሐጎስ ገብሩ ይባላሉ። ከተወለዱባት ትግራይ ክልል ልዩ ስሙ ሙጉላት ከተባለ አካባቢ የወጡት በልጅነት ዕድሜያቸው ነው። ገና በአፍላው የወጣትነት ዘመናቸው፤ በአስመራ ከተማ ከጉልበት ሥራ ጀምረው የተለያዩ ሥራዎችን ሠርተዋል። አስመራ በጋራ ተከራይተው በኖሩባት ክፍል ውስጥ የሠሩበትን ገንዘብ ማስቀመጫ ቦታ ስላልነበራቸው ልብሳቸው ውስጥ ሰፍተው በመያዝ ገንዘብ አጠራቀመው ነበር፡፡ የያዙትን ይዘው ከአስመራ ወደ አዲስ አበባ መጡ።

ያየኔው ወጣት ፍፁም ያጠራቀሟትን ጥሪት ይዘው ሥራ እስከሚለምዱ ድረስ አንድ ልብስ ሰፊ ዘመዳቸው ጋር ተጠግተው ይሠሩ ጀመር። አገሩንም ሥራውንም በደንብ ሲለምዱ የስፌት መኪና ገዝተው ልብስ ጥገና ጀመሩ። ከጥገና ተነስተው ዘመናዊ የሴቶች አልባሳትን አሳምሮ የሚሰፋ ስመጥር ልብስ ሰፊ ሆኑ።

እኚህ ሰው ሀብትን በሥራ ካገኙ በኋላ ሚስት አገብተው ልጆች ወልደው አሁን እስከ የደረሱበት የእርጅና ዕድሜ ድረስ አዲስ አበባ ሲኖሩ፤ የጀመሩትን ሥራ አስፋፍተው ሀብት ለማፍራት በቅተዋል። በደስታና በሰላም ይኖሩ የነበሩት አባት፤ በአገራችን በተከሰተው የእርስ በእርስ ጦርነት ወቅት ሥራ ቀዝቅዞ ቤት መወላቸው ያስከፋቸው ጀመር።

ብዙም ወደ ሱቅ መለስ ቀለስ ባይሉም ከመወለድ ያለፈ ብዙም የማያስታወሷት የትወልድ ቀዬቸው ጦርነት ላይ መሆኗ እንቅልፍ ነስቷቸዋል። በወቅቱ የሚሰሙት የተለያዩ አስፈሪ አሉባልታዎችም ዘመናቸውን ሙሉ ከኖሩባት አዲስ አበባ እንዳያስወጣቸው ሰግተዋል።

በዚህ መሀል ግን አንድ ምሽት በርከት ያሉ ግለሰቦች ወደ መኖሪያ ቤታቸው መጥተው ቤቱን ለፍተሻ እንደሚፈልጉት ነገሯቸው። በወቅቱ የፖሊስ የደንብ ልብስ የለበሱ ሰዎች አብረው በመኖራቸው ሕጋዊ የሆነ ፍተሻ እንጂ ሌላ አላማ አንግበው የመጡ አልመሰላቸውም ነበር። ለፍተሻ ሲጠየቁ ያለምንም ማንገራገር ቤታቸውን ከፍተው እንዲገቡ ጋበዟቸው።

ሰዎቹ ዘጠኝ የአዲስ አበባ ፖሊስ ደንብ ልብስን የለበሱና ሁለት የሲቪል ሰው አለባበስ የለበሱ በድምሩ አስራ አንድ ሰዎች ነበሩ፡፡ አቶ ፍፁም ሐጎስ ገብሩ ቤት ሲገቡ ‹‹ፖሊሶች ነን ተጠቁመን ነው፤ ቤቱን እንፈትሻለን›› ብለው ገብተው ዝርፊያ ፈፅሙ። የሕግ ሰው መስለው በሕገ ወጥነት ከልጅነት እስከ እውቀት ያጠራቀሙትን ጥሪያቸውን ዘርፈው አመለጡ።

## የተቀነባበረው ዘረፋ

ነገሩ እንዲህ ነው፤ ጽጌ ሽለመ የተባለችው ወጣት ለሕገ ወጥ ሥራዋ የሚሆኗትን ሰዎች አደራጅታ መንቀሳቀስ ከጀመረች ሰነባብታለች። በዚህ ተግባሯ ጥሩ ገቢ በማግኘቷ፤ የተጠናና የማያስጠረጥሩ የዘራፋ ሁኔታዎችን ለማካሄድ አስፈላጊ ዕቃዎችን አሟልታለች። ወቅቱ የፈጠረውን ሁኔታ እንደ ጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም እውነት የሚመስል ሁኔታን አቀናብራ፤ ታሪክ ፈጥራ ግብረ አበሮቿን አደራጀች።

ከዚህ በኋላ በጦር መሣሪያ በታገዘና ወንጀልን ለመፈጸም ከተደራጀ የወንበዴ ቡድን ጋር በመሆን በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ዞን 5 መንገድ 9 ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ካልተያዙ 4 ክላሽንኮቭ መሣሪያ ከያዙ 9 የአዲስ አበባ ፖሊስ ደንብ ልብስን የለበሱና 2 የሲቪል ሰው አለባበስ የለበሱ በድምሩ ከሌሎች 11 ሰዎች ጋር ወደ አቶ ፍፁም ሐጎስ ገብሩ ቤት በመሄድ «ፖሊሶች ነን ተጠቁመን ነው ቤቱን እንፈትሻለን» በማለት ወደ ውስጥ ገቡ።

ወንበዴዎቹ የግል ተበዳይ ላይ መሣሪያ በመደቀን «ዶላር አምጣ» በማለትና የተበዳይን ቤት በመበርበር ተከሳሿ በቁጥር ሁለት የሆኑ ዴል ላፕቶፕ ኮምፒዩተሮችን ይዛው በነበረው ቦርሳ ስትከት፣ ሌሎች ግብረ-አበሮቿ ባለ 18 ካራት 23 ግራም ወርቅ እና ስልክ በድምሩ 125 ሺ ብር የሚያወጡ ንብረቶችን በመውሰድ ተሰወሩ።

ፖሊስ ስለሆነው ነገር ጥቆማ ከደረሰው በኋላ በሕጋዊነት አምሳል የተፈፀመ ወንጀል መሆኑን ተረድቶ ጉዳዩን ይከታተል ጀመር።

## የፖሊስ ምርመራ

ፖሊስ የግል ተበዳዮችን አነጋግሮ መረጃ በመውሰድ ጉዳዩን መከታተል ይጀምራል። ወንጀሉ የተፈፀመው በተጠና መልኩ መሆኑ ደግሞ ምርመራውን ፈታኝ አድርጎታል። ወንጀለኞቹ የፖሊስ ደንብ ልብስ በመልበስ መሣሪያ ይዘው ቤት እንፈትሻለን በማለት፤ ከባድ ውንብድና ወንጀል ከፈጸሙት ሰዎች መካከል ጽጌ ሽለመን በቁጥጥር ስር አውሏት።

የእሷ መያዝም ሌሎቹ እንዲያዙ መንገድ የጠረገ ሲሆን፤ አንዱ አንዱ ላይ እየጠቆመ አስራ አንድ ሰዎች በቁጥጥር ስር በመዋላቸው፤ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የልዩ ልዩ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ ክስ እንዲመሰርት ማስረጃዎችን አጠናቀሮ ላከ።

የዐቃቤ ሕግ የክስ መዝገብ እንደሚያስረዳው ጽጌ ሽለመ የተባለችው ተከሳሽ በጦር መሣሪያ በታገዘና ወንጀልን ለመፈጸም ከተደራጀ የወንበዴ ቡድን ጋር በመሆን ታኅሣሥ 22 ቀን 2014 ዓ.ም ወንጀል ፈፅመዋል፡፡ በለሚኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ዞን 5 መንገድ 9 ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ካልተያዙ 4 ክላሽንኮቭ መሣሪያ ከያዙ 9 የአዲስ አበባ ፖሊስ ደንብ ልብስን የለበሱና 2 የሲቪል ሰው አለባበስ የለበሱ በድምሩ ከሌሎች 11 ሰዎች ጋር በመሆን የግል ተበዳይ ቤት ገብተዋል፡፡ በግል ተበዳይ አቶ ፍፁም ሐጎስ ገብሩ ቤት በመሄድ «ፖሊሶች ነን ተጠቁመን ነው ቤቱን እንፈትሻለን» በማለት፤ ከግብረ-አበሯ ጋር በመሆን ተበዳይን «ዶላር አምጣ» በማለት የያዙትን መሳሪያ ተበዳይ ላይ በመደገን አንገቱን አንቀው በመያዝ ተከሳሿና ሌሎች ያልተያዙት የወንጀሉ ፈፃሚዎች የተበዳይን ቤት በመበርበር ተከሳሿ በቁጥር ሁለት የሆኑ ዴል ላፕቶፕ ኮምፒዩተሮችን ይዛው በነበረው ቦርሳ ስትከት፣ ሌሎች ግብረ-አበሮቿ ባለ 18 ካራት 23 ግራም ወርቅ እና ስልክ በድምሩ 125 ሺ ብር የሚያወጡ ንብረቶችን በመውሰድ የተሰወሩ በመሆኑ፤ ተከሳሿ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈፀመችው የከባድ ውንብድና ወንጀል ዐቃቤ ሕግ ክስ መስርቶባታል፡፡

## ውሳኔ

በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ 1ኛ ሰው ግድያና ከባድ ውንብድና ወንጀል ችሎት የቀረበችው ተከሳሽ የተከሰሰችበት ክስ በችሎት ተነቦላት የወንጀል ድርጊቱን አልፈፀምኩም ብላለች፡፡ ዐቃቤ ሕግም ማስረጃዎችን በማቅረብ በበቂ ሁኔታ ወንጀሉን ስለመፈጸሟ በማስረዳቱ ፍርድ ቤቱ እንድትከላከል በሰጠው ብይን መሠረት ቀጠሮ ቢሰጣትም ቀጠሮዋን አክብራ ችሎት ያልቀረበች፣ የመከላከያ ምስክርም ያላቀረበች በመሆኑ ተከሳሽ የመከላከል መብቷን መጠቀም እንዳልፈለገች ተቆጥሮ ትከላከል በተባለችበት ድንጋጌ ስር የጥፋተኝነት ፍርድ በመስጠት በሌለችበት በ12 ዓመት እስራት እንድትቀጣ፣ እንዲሁም ለ3 ዓመት ከሕዝባዊ መብቷ እንድትታገድ ሲል ወስኖበታል፡፡

## ማስታወሻ

ተከሳሽ በሕግ በተፈቀደላት መብት መሠረት በዋስትና ወጥታ ክርክር ስታደርግ ብትቆይም የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ እንደሚፈረድባት ስታውቅ የመከላከያ ማስረጃ እንድታቀርብ በተቀጠረ ቀጠሮ ሳትገኝ የቀረች በመሆኑ ፍርድ ቤቱ የመከላከል መብቷን አልፎ የጥፋተኝነት ፍርድ በመስጠት በ12 ዓመት እስራት እንድትቀጣ የወሰነባት ሲሆን የወንጀል ሕጉ ስለ ቅጣት ይርጋ በሚደነግገው አንቀጽ 224 ስር ከ10 ዓመት በላይ ለሆነ ነፃነትን ለሚያሳጣ ወንጀል የቅጣት ይርጋው 20 ዓመት በመሆኑ ተከሳሿ/ፍርደኛዋ የቅጣት ፍርዱ ተፈጻሚ ከሚደረግበት የካቲት 22/2015 ዓ.ም ጀምሮ ባሉ 20 ዓመታት ውስጥ በተገኘች በማንኛውም ጊዜ ቅጣቱ የሚፈጸምባት ይሆናል። በመሆኑም ተከሳሽ 20 ዓመታትን ከፍትህ በመሸሽ በድብብቆሽ በመሳቀቅ ከማሳለፍ ቀርባ ተገቢውን ቅጣት እንድትቀበል ጥሪ እያቀረብን ተከሳሽን በማንኛውም አጋጣሚ ያየ ወይም የሚያውቅ ለቦሌ ክፍለ-ከተማ ፖሊስ ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ፖሊስ እንዲያሳውቅ በማክበር እንጠይቃለን።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

# አከራይም ነፃነት ይፈልጋል!

**ዋስልኝ አየለ**

በአከራይና ተከራይ ዙሪያ ብዙ ተብሏል፤ እኔን ጨምሮ በዚሁ በትዝብት ዓምድ እንኳን ብዙ ተብሏል። በየመገናኛ ብዙኃኑ የሚሰጠው የአከራይና ተከራይ ትዝብት ግን የአከራዮች ክፋትና ጭካኔ ላይ የሚያተኩር ነው። በአከራዮች በኩል ያለው ችግር ብዙ ስለተባለበት እስኪ ዛሬ ደግሞ በተከራዮች በኩል ያለውን ችግር እንታዘብ።

አንዳንዴ በአከራይ ቦታ ሆኜ አስበውና ‹‹እኔ ብሆን ይህን እታገስ ነበር?›› ብዬ አስቤ አውቃለሁ። ይህን የምለው በተከራየሁበት ግቢ ውስጥም ሆነ በተለያዩ ጓደኞቼ የአንዳንድ ተከራዮችን ድርጊት በማየት ነው። አንዳንዴ ደግሞ በዚያ ልክ እንዴት ድፍረት ሊያገኙ ቻሉ? የሚለው ያስገርመኛል። ከእኔ ግላዊ ባህሪ አንፃር እያየሁት ነው መሰለኝ ለመቅናትም ይቃጣኛል። በዚህ ልክ ድፍረት ቢኖረኝ እላለሁ።

ለምሳሌ፤ የሚከፍቱት ሙዚቃ ልክ በጎዳናዎች ላይ የበዓል ሰሞን በሞንታርቦ የሚለቀቁ ማስታወቂያዎችን ይመስላል። ከመረበሽ አልፎ ጎረቤት ያለ ሰው ለማውራት እስከሚቸገር ድረስ(ባለመሰማማት) የሚያስጮሁ አሉ።

ሲወጡና ሲገቡ የውጭውን በር ሲዘጉት የሚጠቀሙት ኃይል ግንብ ካልሆነ አጥሩን ሁሉ ያነቃንቀዋል። አንዳንዴ እንዲያውም በግዴለሽነት ብቻ ሳይሆን ሆን ብለው ሁሉ ይመስለኛል፤ በሩን በእጅ ተከትሎ ቀስ ብሎ መዝጋት እየተቻለ ይወረውሩታል።

ግዴለሽነቱ አብሮ ያደገ እንዝላልነት ነው እንበል፤ ተከራይ መሆኑ ግን ይረሳል? በዚህ የቤት መጥፋትና መወደድ ዘመን ይህ ችግር መረሳት ነበረበት? ‹‹ውጡ!›› ከተባለ በኋላ ከማማረር በሥነ ሥርዓት መኖር አይሻልም? እዚህ ላይ ግን አንድ ልብ መባል ያለበት ነገር ‹‹ውጡ!›› የሚባለው በተከራዮች የሥነ ምግባር ችግር ብቻ አይደለም፤ አከራዮች የተጋነነ ዋጋ ሊጨምሩ ሲያስቡ መሆኑ አሁን አሁን የተረጋገጠ ሀቅ ሆኗል!

የአንዳንድ ተከራዮች ባህሪ አከራዮችን ብቻ ሳይሆን ሌላውን ሥነ ሥርዓት ያለውን ተከራይ ሁሉ የሚረብሽ ነው። አንድ የራሴን ገጠመኝ እንደ ማሳያ ልጠቀም። በአንድ በተከራየሁበት ግቢ ውስጥ የፍሳሽ ቆሻሻ መድፊያ ቱቦ ነበር። በግቢው ውስጥ አጥሩ ሥር ነው መድፊያው። መድፊያው የሽቦ ወንፊት መሰል ነገር ሲሆን ፍሳሽ ነገር ብቻ እንደሚያስተላልፍ ለማንም ግልጽ ነው። ደረቅ ቆሻሻ በፌስታል ወይም ማዳበሪያ አጠራቅሞ ቆሻሻ የሚያነሱ ሠራተኞች በሚመጡ ቀን ነው ጎዳናው ላይ የሚደረግ።

ዳሩ ግን ያንን የሽቦ ወንፊት መሰል የፍሳሽ ብቻ መድፊያ ጠጣር ነገር ይጥሉበት ጀመር። ተረፈ ምግብ፣ ድንች፣ ሽንኩርት፣ ፌስታል ሁሉ ሳይቀር ይጣልበታል። በተደጋጋሚ ቢነገር፣ ማሳሰቢያ ቢጻፍበት ችግሩ ሊቀረፍ አልቻለም። በመጨረሻም የሽቦ ወንፊቱ ተቀዳዶ የሚጣልበትን ጠጣር ነገር ማሳለፍ ጀመረ፤ ቱቦውም ተደፈነ። ባለቤቱ ቦታውን በቆርቆሮ ደፍኖ ‹‹ከዚህ በኋላ ወንዝ እየሄዳችሁ ድፉ›› አለ።

እስኪ አሁን እንግዲህ በማን ይፈረዳል? በቀላል ዘዴ መጠቀም እየተቻለ ባልዲ ሙሉ ቆሻሻ ውሃ ተሸክሞ መጓዝ ተጀመረ ማለት ነው። ቶሎ ቶሎ መድፋት ይቻል የነበረበትን አሠራር በማበላሸት ቆሻሻ ውሃ ታቅፎ መቆየት መጣ ማለት ነው። በእንዲህ ዓይነት ሰዎች ምክንያት በነፃነት መኖር ይችሉ የነበሩ አከራዮች በራሳቸው ግቢ መጉላላትና መቸገር ጀመሩ ማለት ነው።

አንዳንድ የተከራይ ድርጊቶችን ሳይ ‹‹እውነት የራሳቸው ቢሆን እንዲህ ያደርጋሉ?›› እላለሁ። በእርግጥ እስከኖሩበት ድረስ የተከራዩበትም የራሳቸው ነው። ግን ግዴለሽነታቸው ሲታይ ደግሞ የራሳቸው ቢሆን እንዲህ አያደርጉትም ብሎ ለመገመት ያስገድዳል።

እንዲህ ነው እንግዲህ በአከራይም በተከራይም ከሰዋዊ ሥነ ምግባር ያፈነገጡ ድርጊቶች የሚታዩ። ለተከራይ መብት የጮህነውን ያህል ለአከራዮች ነፃነትም ማሰብ አለብን። ባለቤት ስለሆኑ የተለየ ነፃነትና ከልክ ያለፈ አክብሮት ይኑረን ባይባልም ቢያንስ ግን እየተማረሩ የሚኖሩበትን ድርጊት መፈጸም ልክ አይደለም። ምንም እንኳን አለመሰልጠን እንደ አገር ያለብን ችግር ቢሆንም አከራዮች ግን ግለሰብ ናቸውና ‹‹ምን አገባህ!›› ልንላቸው አንችልም፤ ምክንያቱም ግለሰብ ስለሆኑ የማስወጣት ድርጊት ይፈጽማሉ።

ይህን ያህል ለአከራይ ስቆረቆር አከራይ እመስላለሁ አይደል?(ፌስቡክ ቢሆን የሳቅ ‹‹ኢሞጂ›› በተጠቀምኩ ነበር) ይግረማችሁ አከራይ ዘመድ እንኳን የለኝም። ዳሩ ግን ከላይ የጠቀስኳቸውን ዓይነት ተከራይ አይደለሁም፤ እነዚያን ድርጊቶች የማላደርጋቸው አከራዮቼን በመፍራት ሳይሆን ድርጊቶቹ ራሴን ስለሚረብሹኝ ነው። ቤት ቢኖረኝ የማላደርጋቸውን ነገሮች ስለማላደርግ ነው።

ከብዙ ተከራይ ጓደኞቼ ጋር የምጣላበት ነገር ቢኖር ‹‹ከፍዬ ነው እኮ የምኖር!›› ሲሉኝ ነው። በነፃ የሚኖር ከሆነ በሥነ ሥርዓት ሊኖር፣ ከፍሎ የሚኖር ከሆነ ግን እየረበሸ ሊኖር ማለት ነው? አከራዮቹ እኮ ቢያስወጡት ቀጣዩ ተከራይም ከፍሎ ነው የሚኖር። መከራከሪያው መሆን የነበረበት መብቱ የሆነውን ነገር እንዳይከለከል እንጂ ስለከፈለ ብቻ የትኛውንም ረባሽ ድርጊት ይፈጽማል ማለት አይደለም።

ሥነ ምግባር የሌላቸው ተከራዮች አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አንጀቴን ያሸሩኛል። እንዲህ ዓይነት ተከራዮችን የማመሰግናቸው ክብር የማይወድላቸው አከራዮችን ልክ ሲያስገቧቸው ነው። በጣም ተለሳላሽ የሆነውን ተከራይ በውሃ ቀጠነ ምክንያት ቁም ስቅል ሲያሳዩት ይከርማሉ፤ ይባስ ብሎ የተጋነነ ዋጋ ጨምሮ ለማከራየት ያስወጡታል።

ቀጣዩ ተከራይ የሙሉ ጊዜ ሰካራም ይሆናል። ልቀቅ ሲሉት ‹‹ማን ለቃቂ ማን አስለቃቂ እንደሚሆን እናያለን!›› እያለ ይፎክራል። በደረቀ ሌሊት እየመጣ በሩን ይነርተዋል። የሚገርመው ለእንዲህ ዓይነቱ ተከራይ ተሸቆጥቁጠው ነው የሚከፍቱለት። የሚነጫነጩት እንኳን ቤት ገብተው ለብቻቸው ነው። ከፊቱ የመናገር ነፃነት እንኳን የላቸውም። ይህ የሚሆነው ምናልባትም በተለሳላሹ ተከራይ ግፍ ሊሆን ይችላል።

የዛሬው ትዝብቴ ተከራዩ ላይ ብቻ ስለሆነ ወደዚያው ልመለስ። ተከራዮች ቤት ስንፈልግ እኛም እንደ አቅማችን ብዙ መስፈርት እናወጣለን። ለዋና መስመር ቅርብ የሆነ፣ በአካባቢው የሚረብሽ ነገር የሌለበት፣ ከዚያም አለፍ ሲል ተከራይ የማይበዛበት እንመርጣለን። ይህ ሁሉ የሚሆነው ምቾት ፍለጋ ነው፤ ነፃነት ለማግኘት ነው። በዚህ ልክ ለራሳችን ነፃነትና ምቾት ስንፈልግ ለአከራዮች ነፃነትም መታሰብ አለበት።

እውነቱን እንናገር ከተባለ፤ እኛ ተከራዮች እንኳን የማናውቀው ሰው በር ከፍቶ ሲገባ ምቾት አይሰጠንም፤ ነፃነት አይሰጠንም። ስለዚህ አንድ ተከራይ ጫት የሚቅሙ ብዙ ጓደኞችን ይዞ ቢመጣ አከራዮች ደህንነት አይሰማቸውም። ማንም እያንኳኳ ‹‹እገሌን ፈልጌ ነው!›› እያለ ሲገባ ነፃነት አይሰጣቸውም። ምክንያቱም ዘመኑም የማጭበርበርና የዝርፊያ ወንጀሎች የበዙበት ነው።

አንድ ተከራይ በአከራዮቹ ላይ እምነት የሚጣልበት መሆን አለበት፤ ከዚያ በኋላ ሰፊ ነፃነት ነው የሚኖረው። መጀመሪያ በሚረብሹ ነገሮች ከታወቀ ግን በጥርጣሬ ነው የሚያዩት። በአጠቃላይ ለራሳችን ነፃነት እንደምንፈልግ ሁሉ ለአከራዮችም ነፃነት እያሰብን ይሁን!

# ዓለም አቀፍ



## ታይዋን በተዋጊ ድሮኖች ተከብቤያለሁ አለች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በቻይና ሚዲያዎች ከፍተኛ ክብደት መሸከም ይችላል የሚባለው አዲሱ የቻይና ተዋጊ ድሮን ታይዋንን እየዞረ መሆኑን የታይዋን መከላከያ ሚኒስቴር ገልጿል። ታይዋንን እንደራሷ ግዛት የምታያት ቻይና ባለፉት ሦስት አመታት በደሴቷ ዙሪያ የምታደርገውን ወታደራዊ እንቅስቃሴ ጨምራለች፡፡

ታይዋንን እንደራሷ ግዛት የምታያት ቻይና ባለፉት ሦስት አመታት በደሴቷ ዙሪያ የምታደርገውን ወታደራዊ እንቅስቃሴ ጨምራለች። ይህ የቻይና ተግባር ታይዋን በጫና ውስጥ ሆና የቻይናን ሉአላዊነት እንድትቀበል ለማድረግ ነው።

የታይዋን ፕሬዚዳንት ጻይ ኢንግ ዌን ከአሜሪካ የተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ኬቨን ማካርቲ ጋር ከተገናኙ በኋላ ቻይና በታይዋን ዙሪያ የጦርነት ልምምዶችን አካሂዳለች። የታይዋን መከላከያ ሚኒስቴር ከትናንት በስቲያ ወዲህ 19 የሚሆኑ የቻይና ወታደራዊ አውሮፕላኖች በደሴቲቱ የአየር መከላከያ ቀጣና ገብተዋል ብሏል።

ሚኒስቴሩ እንደገለጸው ባለሁለት ጭራ እየተባለ የሚጠራው የቻይና ድሮን ታይዋንን ከፊሊፒንስ የሚለየውን የባሽ መስመር ካቋረጠ በኋላ ወደ ምሥራቅ ታይዋን አቅጣጫ በሯል። ድሮኑ በመጨረሻም ወደ ቻይና ድንበር መመለሱን ሚኒስቴሩ ጠቅሷል።

የቻይና አየር ኑክሌር መሸከም በሚችለው ኤች-6 ታይዋን በመክበብ እንቅስቃሴ አድርጓል። ምንም ዓይነት ተኩስ አለመተኮሱን እና የቻይና አየር ኃይልም የታይዋንን አየር ኃይል አልጣሰም ተብሏል።

ምንም ዓይነት ጥይት አልተተኮሰም እና የቻይና አውሮፕላኖችም የታይዋንን አየር ክልል አላቋረጡም ተብሏል። የቻይና ወታደራዊ አውሮፕላኖች ከባለፈው አመት ጀምሮ እንደወሰን የሚቆጠረውን የታይዋን ባህርን መካከለኛ መስመር በተደጋጋሚ በማቋረጥ ላይ ናቸው።

የታይዋን መንግሥት የቻይናን የሉዓላዊነት ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የወደፊት ዕጣ ፈንታቸውን መወሰን የሚችሉት የደሴቲቱ ሕዝብ ብቻ ነው ብሏል ሲል የዘገበው አል አይን ኒውስ ነው።



## የኡጋንዳ ፖሊስ 11 ሴት ሕግ አውጪዎችን በቁጥጥር ስር አዋለ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የኡጋንዳ ፖሊስ ሕገ-ወጥ ተቃውሞ አድርገዋል ያላቸውን 11 ሴት የፓርላማ አባላትን ሐሙስ ዕለት በቁጥጥር ስር አውሏል። ፖሊስ ሕግ አውጪዎቹ ሕገ-ወጥ ተቃውሞ ሲያደርጉ ይዣቸዋለሁ ብሏል፡፡

የሕግ አውጪዎቹ በዋና ከተማዪቱ ካምፓላ ከሚገኙት የፓርላማ ሕንፃዎች ወጣ ብሎ ወደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሰልፍ ለማድረግ ሲዘጋጁ በቁጥጥር ስር ውለዋል። አንዳንድ የሕግ አውጪዎች በቁጥጥር ስር በዋሉበት ወቅት ጉዳት እንደደረሰባቸውም ተነግሯል።

ከቅርብ ሳምንታት ወዲህ በሴት የሕግ አውጪዎች የተዘጋጁ የተለያዩ ተግባራትን ለመበተን ፖሊስ ከፍተኛ ኃይል መጠቀሙን በመቃወም ነበር ሰልፍ የወጡት። የፓርላማው ምክትል አፈ-ጉባኤ ቶማስ «በዛሬ ጠዋት ፖሊስ ሰላማዊ እና ትጥቅ ያልነበራቸውን 11 ሴት የፓርላማ አባላት ያሰረበትን መንገድ አጥብቄ አወግዛለሁ» ብለዋል።

የፖሊስ ቃል አቀባይ ሉክ ኦዎዬሲጊየር መኮንኖቹ ከመጠን ያለፈ ኃይል ተጠቅመዋል መባሉን አስተባብለዋል። ሕግ አውጪዎቹን በቁጥጥር ስር ለማዋል አንዳንድ የፖሊስ አባላትም ቆስለዋል ሲሉ ከሰዋል።

ሕግ አውጪዎቹ በሕገ ወጥ መንገድ ተቃውሞ ሲያደርጉ በቁጥጥር ስር መዋላቸውን ተናግረው በዋስትና መፈታታቸውንም ተናግረዋል። ባለፉት ዓመታት የኡጋንዳ የጸጥታ አባላት በተለይም በአንጋፋው መሪ ዩዌሪ ሙሴቬኒ ተቃዋሚዎች ላይ ጭካኔ የተሞላበት ድርጊት ፈጽመዋል ሲል ሮይተርስ ዘግቧል።

# መጋቢ አዕምሮ

# ጭንቀት እንዴት ይቆማል?

**አስናቀ ፀጋዬ**



ሃሳብና ጭንቀት የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ባህሪ ናቸው። ማንኛውም ጤናማ የሆነ ሰው በሚገጥሙት የተለያዩ ችግሮች ምክንያት ያስባል፤ ይጨነቃል። ልዩነቱ ግን ሁሉም ሰው እኩል አያስብም፤ እኩል አይጨነቅም። አንዳንዱ አብዝቶ ይጨነቃል። ሌላው ደግሞ ብዙ አይጨነቅም። አንዱ ከመጠን በላይ ሃሳብ ይገባዋል። ሌላው ብዙ አያስብም። ስለዚህ ሀሳብና ጭንቀት እንደየሰው ባህሪ፣ ችግሮችን የመጋፈጥና ተቀብሎ የማስተናገድ አቅም ይወሰናል። ምንም እንኳን ሃሳብና ጭንቀት የሰዎች ባህሪ ቢሆንም ታዲያ ‹‹ሲበዛ በሽታ ነው›› ይላሉ የአእምሮ ህክምና ባለሞያዎች። ስለሆነም አብዝቶ ማሰብንና መጨነቅን እንዴት ማቆም ይቻላል?

አብዝቶ ማሰብና መጨነቅ የብዙ ሰዎች ችግር ነው። ሰዎች ነብስ ካወቁ ጀምሮ እስከ ህይወታቸው ፍፃሜ ድረስ ማሰብና መጨነቅ እንደጥላ የሚከተላቸው ባህሪ ነው። መጠኑ ይለያይ እንጂ አብዝቶ የማያስብና የማይጨነቅ ሰው የለም። ማሰብ መልካም ነገር ነው፤ ህይወትንም ይቀይራል። ሲበዛ ነው መጥፎነቱ። ማሰብ ከበዛ እንቅልፍ የሚባል ነገር የለም። በዚህ ምክንያት አንዳንዴ ሰዎች የሚችሉትን ሁሉ መስራት አይችሉም። ወይም ብዙ ከማሰባቸው የተነሳ ለመስራት አቅም ያንሳቸዋል። ሲያስቡ ግዜው ይሄድባቸዋል።

ሌላ ግዜ ደግሞ ሰዎች ተመሳሳይ ብዙ ሃሳቦችን አስበው ይደክማቸዋል። ሃሳባቸው ወይ የትናንት ትዝታ ነው፤ አልያም ደግሞ ቁጭትና የሚያጨንቃቸው ጉዳይ ነው። አንዳንዴ ምን እንደሚያስቡ ሁሉ አያውቁትም። ግን ሃሳበቸው ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን እየተሻማባቸው ነው። ከሰው በታችም እያደረጋቸው ነው። ጭንቀታምም እያደረጋቸው ነው። ምን ይሻላል ታዲያ?

በዚህ አለም ከፍተኛ የስኬት ደረጃ ላይ የደረሱ የሃይማኖት ወይ የቢዝነስ ሰዎች ወይም የምናከብራቸው ሰዎች ብዙ ግዜ የሚያስቡት በፕሮግራም ነው። ስራ እየሰሩ ከሆነ መቶ በመቶ ስራው ላይ ብቻ ነው ትኩረታቸው። ከቤተሰባቸው ጋር ከሆኑም መቶ በመቶ እዛ ቦታ ላይ ናቸው። ቅፅበቱ ላይ ነው የሚያተኩሩት። ማሰብ ሲፈልጉ ደግሞ ቁጭ ብለው ነው። እኛ የከበደን እሱ ነው። በምንፈልገው ሰአት አይደለም የምናስበው።

ስራ እየሰራን ሃሳብ አለ። የምንፈልገውን እያደረግን ሃሳብ አለ። ልንተኛ ስንል ሀሳብ አለ። አስቡት እንግዲህ ሃሳባችሁን መቆጣጠር ብትችሉ ተአምር መፍጠር ትችላላችሁ። ብዙ ነገር በህይታችሁ ትቀይራላችሁ። ሀሳባችሁን ተቆጣራችሁ ህይወታችሁን መቀየር የምትችሉባቸው በጣም ቀላል የሆኑ ሳይንሳዊ መፍትሄዎች አሉ።

1ኛ. ራስን ማድመጥ አንዳንዴ ምን እንደምታስብ እንኳን አታውቀውም። እንደውም አንዳንድ ሰው በጣም ሃሳብ ውስጥ ይሰምጥና የሚነቃው ወይ ስልኩ ሲጠራ ነው፤ ወይ ደግሞ ‹‹እንዴ አንተ የት ሄድክ በሀሳብ›› ሲባል ነው። ከዛም ምን እያሰብክ ነው ሲባል ምን እንደሆነ አያውቀውም። ስለዚህ አሁን ራስህን ለማድመጥ ሞክር። ምንድን ነው የምታስበው? ልክ ስታስብ ንቃ። የሆነ ጭንቀትና ሃሳብ ውስጥ ስትገባ ‹‹አሁን እያሰብኩ ነው›› በል። የሆነ ሰው መጥቶ እስኪቀሰቅስህ ድረስ አትጠብቅ።

በመቀጠል ንቃና ምንድን ነው እያሳሳበኝ ያለው ነገር የሚለውን ለይተህ አውጣው። በርግጠኝነት በጣም አብዝተህ የምታስባቸው ነገሮች ከሁለትና ሶስት ጉዳዮች አይበልጡም። ወይ ኖሮ ነው፣ ወይ ትዳር ነው፣ ወይ ስራ ነው፣ ወይ ትምህርት ነው፣ ወይ ቢዝነስ ነው፣ ወይ ገንዘብ ነው፣ ወይ የፍቅር ግንኙነት ነው። ከነዚህ አይዘልም። ስለሆነም ስለምን እንደምታስብ ነቃ ብለህ ለማሰብ ሞክር። እንደዚህ የማድረግ ዓላማው ጫፉን ለመያዝ ነው። ስለምን እያሰብክ እንደሆነ ለማወቅ ነው። ያስጨነቀህን ጉዳይ ለይቶ ለማወቅ ነው። ከጭንቀትና አብዝቶ ከማሰብ መውጣት ከፈለክ ራስህን አድምጠውና ልክ ሀሳብ ውስጥ ስትገባ ነቃ ለማለት ሞክረህ ‹‹ይህን እያሰብኩ ነበር›› በል።

## 2ኛ. አምስት መፍትሔዎችን ፃፍ

ምን እንደሚያሳስብህ ማወቅ ከጀመርክ አሁን ወረቀት ላይ ማሰብ መጀመር አለብህ። ወረቀት ላይ የሚያስቡ ሰዎች ሃሳባቸውን መቆጣጠር ይችላሉ። ስለዚህ ይሄ ችግር በጣም እያሳሰበኝ ነው ብለህ ትፅፍና ወደአእምሮህ የሚመጡትን መፍትሄዎች መዘርዘር ጀምር። አምስት መፍትሄዎችን ፃፍ። ለምን መሰለህ አእምሮህ ትኩረቱን ከችግሩ ላይ አንስቶ ወደመፍትሄው መምጣት አለበት። ስለመፍትሄው ማሰብ አለብህ። ስለጨለማው አብዝቶ ማሰብ ብርሃን አይሰጥህም። በችግሩ ላይ ግዜ አታጥፋ።

አየህ በዚህ ምድር ሁለት አይነት ሰዎች አሉ። ለምሳሌ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ኑሮ ተወደደ ተብሎ ሲነገራቸው ‹‹አቤት! አቤት! ይሄኔ ዘይቱን ደብቀውት ነው፤ ሊገሉን ነው፤ እንደው ምን አደረግናቸው ሊያስርቡን ነው›› ይላሉ። ችግሩ ላይ ይራቀቁበታል። አብዝተው ስለችግሩ ያስባሉ። ሁለተኞቹ ግን ኑሮ ተወደደ ሲባልና ችግሩን ሲሰሙ ‹‹ምን ይሻላል ይባስ ሳይወደድ እቃውን ቶሎ ልግዛ እንዴ፤ ወይስ ገቢዬን ላሳድግ?›› ይላሉ። ወደ መፍትሄው ይገባሉ። ስለዚህ አንተ የትኛው ላይ ነህ ነው ጥያቄው። ችግሩ ላይ ነው ጊዜህን የምታጠፋው ወይስ መፍትሄው ላይ? የመፍትሄ ሰው መሆን አለብህ።

## 3ኛ.ጥድፊያውን አቁም

ከጊዜ ጋር አትታገል። ከጊዜ ጋር ስለምትታገል ነው አብዝተህ የምታስበው፤ የምትጨነቀው። ለምሳሌ ፈተና ክፍል ውስጥ አስተማሪው ‹‹አሁን አስር ደቂቃ ነው የቀራችሁ ፈጠን ብላችሁ ሰርታችሁ የፈተና ወረቀታችሁን እየሰጣችሁ ውጡ›› ሲል ትደነግጣለህ። ምክንያቱም ያለህ አስር ደቂቃ ቢሆንም አንተ የቀረህ ብዙ ጥያቄ ስለሆነ ነው። ስለዚህ ትደናበራለህ። ጥድፊያ ውስጥ ትገባለህ። ሁሉንም ለመመለስ ስትል የምታውቀው ሁሉ ይጠፋብሃል።

አንዳንዴ አንተ የምታስበው ነገር በምትፈልገው ፍጥነት አለመሳካቱ አብዝተህ እንድታስብ ያደርግሃል። አንዳንድ ሰው እኔ በሃያ አምስት አመቴ ጥሩ ቢዝነስ ገምብቼ ጥሩ ገቢ ይኖረኛል ይላል። ልክ ሀያ አምስት አመቱን ሲያከብር እንኳን ቢዝነስ ሊገነባ ተቀጥሮ እንኳን እየሰራ አይደለም። እርሱን የሚቀጥረው ሰው እንኳን የለም። ግራ ይገባዋል። በጣም ይጨነቃል።

ሁላችንም የሆነ ነገር እንፈልግና በምንፈልገው ፍጥነት ካልተሳካ አብዝተን እናስባለን፤ እንጨነቃለን። የጭንቀታችን ጉዳይ ጥድፊያ ነው። ህይወት ፎቅ ይመስል ስለሊፍት እናስባለን። አጭር መንገዶችን እንፈልጋለን። ይሄኔ ተረጋግተንና እጃችን ላይ ያለውን ነገር አስተካክለን ብንጓዝ ነገሮች ቶሎ ተስተካክለው በምንፈልገው ፍጥነት ልንደርስ እንችላለን። ግን ሁሌም ጥድፊያ ላይ ነን። ስለዚህ ወዳጄ ከግዜ ጋር አትወዳደር። የፈጀውን ይፍጅ እንጂ እኔ በሂደትም ቢሆን የምፈልግበት ደረጃ እደርሳለሁ በል። አየህ ትእግስት ማለት የምትችለውን ሁሉ እያደረክ የሚሮጠውን ግዜ ማሳለፍ መቻል ነው።

## 4ኛ.ለማሰቢያ የሚሆን ጊዜ መድብ

በዚህ ሰአት ለሃያና ሰላሳ ደቂቃ አስባለሁ በልና ፕሮግራም ያዝ። ልክ ያ ሰአት ሲደርስ አላርም ሙላ። ከዛ ማሰብ ጀምር። የባጥ የቆጡን የፈለከውን አስብ። ከዛ አላርሙ ሰላሳ ደቂቃ ሞልቶ ሲጮህ ወደስራህ ተመለስ። አሁን ለሀሳብህ ቦታ ሰጥተኸዋል። ስለዚህ በጣም ወሳኝ ስራ እየሰራህ ሃሳብ አይመጣብህም። አንዳንድ ጊዜ እኮ ለማሰቢያ የሚሆን ጊዜ ስላልመደብክ ወሳኝ ሰአት ላይ ሀሳብና ጭንቀት ይመጣል። ልትተኛ ስትል ሃሳቦች ይመጡና እንቅልፍ አይወስድህም። በጣም ወሳኝ ሰዓት ላይ ስራ ልትሰራ ስትል ሃሳብ ይመጣብሃል።

አሁን ግን ለሀሳብህ ጊዜ መድበህለታል። እንደውም የሜታኮግኒቲቭ ቴራፒስቶች ምን ይላሉ የሰው ልጅ ሃሳቡን መቆጣጠር ይችላል። ለምሳሌ ስልክህ ሲጠራ ያንን ጥሪ መቀበል ካልፈለክ እያየኸው ዝም ማለት ትችላለህ። ከዛ ጠርቶ ማቆሙ አይቀርም። አይምሮህ ውስጥም እንደዛ ነው። ሃሳቡ ይመጣል፤ ይጠራል። ስለዚህ ያን ሃሳብ አብዝተህ ማሰብ ከፈለክ እንደስልኩ ታነሳዋለህ። ካልፈለክ ዝም ትልዋለህ፤ታሳልፈዋለህ። ወይ ቀጠሮ ትይዝለታልህ። ስለዚህ ይህ ነው ሃሳብን መቆጣጠር ማለት። ለማሰብ ጊዜ መመደብ በጣም የሚገርም መፍትሄ ነው። ጭንቀትህንና አብዝቶ ማሰብህን ታቆማለህ።

## 5ኛ.ትንንሽ ሃሳቦችን አስቀይስ

ትንንሽ ሃሳቦች ሁሌም ትንንሽ ናቸው። ነገር ግን የትልቁን ሃሳብ ቦታ ይይዛሉ። አንዳንዴ በጣም ትንንሽ የሆኑ ሃሳቦች አይምሮህን ይቆጣጠሩታል። ምንም ስለማይጠቅምህ ሰው አብዝተህ ትጨነቃለህ። ወይ ደግሞ ከሰዎች ጋር ራስህን እያወዳደርክ እያሰብክ ረጅም ሰአታትን ትፈጃለህ። እንደነዚህ አይነት ሃሳቦች በጣም ትንንሽ ናቸው። ሆኖም አእምሮህ ላይ ትልቅ ቦታ ይይዛሉ። ጊዜህን ይሻማሉ። ጉልበትህን ይመጡታል። እንደነዚህ አይነት ሀሳቦችን ማስቀየስ ነው ያለብህ። መሸሽ ነው ያለብህ። ማለትም በድርጊት/በተግባራዊ ነገር መሸሽ/ አለብህ።

ለምሳሌ እነዚህ ትንንሽ ሃሳቦች ወደአእምሮህ ሲመጡብህ ተንስና ቤትህን አስተካክል።አልጋህን አንጥፍ። ቤትህን አፀዳዳ። ወይ ደግሞ ስፖርት ስራ። የእግር ጉዞ አድርግ። አጠገብህ ያለን ህፃን አንሳና አጫውት። ያን ሃሳብ በአንድ ጊዜ ትረሳዋለህ። ትናንሽ ሃሳቦች ካንተ መራቅ ይጀምራሉ። ነገር ግን ትልልቅ ሃሳቦችን መሸሽ የለብህም። ለትልልቅ ሃሳቦችን ሁልጊዜም ቁጭ ብለህ መፍትሄ ነው የምትፅፈው። ስለዚህ ትንንሽ ሃሳቦች ሲመጡብህ ‹‹አረ እኔ ይህን ማሰብ ለእኔ አይመጥንም፤ በጣም የወረደ ሃሳብ እኮ ነው›› ማለት አለብህ።

አንዳንዴ ስራ ስለፈታህ ይሆናል እንደነዚህ አይነት ትንንሽ ሃሳቦች የአዕይምሮህን ቦታ የሚያጣብቡት። ‹‹ስራ የፈታ ሰው የሴጣን መጫወቻ ይሆናል›› እንደሚባለው ስራ ስትፈታ የማይረቡ ሃሳቦች አእምሮህን ይሞሉታል። ስለዚህ ወደ ስራህ ተመለስ። የሆነ ስራ መስራት ጀምር። ያኔ ትንንሽ ሃሳቦችን ታስቀይሳቸዋለህ።

## 6ኛ. በእምነትህ ጠንክር

እንዴት ሰው ከፍሎ ይሸከማል በነፃ ማሸከም እየቻለ? አንተ ሃሳብህንና ጭንቀትህን ትልቁ ሸክምህን ለፈጣሪህ መስጠት እየቻልክ ለምን አንተ ትሸከማለህ? አንተ መቆጣጠር የምትችለው ነገር ብቻ ላይ አተኩር። መቆጣጠር የማትችላቸውን፣ የማትጨብጣቸውንና የማትታገላቸውን ነገሮች ለፈጣሪህ አስረክብ። አየህ አንዳንድ ግዜ እኮ አቅምን ማወቅ ጥሩ ነው። ቅልል ይልሃል። እኔ ይህን እቆጣጠራለሁ፤ ይህንን ግን አልቆጣጠርም ለፈጣሪ እሰጠዋለሁ በል።

ሁኔታዎችን አንተ አትቆጣጠራቸውም። የሀገሪቷን ሁኔታ፣ የሰዎችን እንቅስቃሴ፣ ኢኮኖሚውን፣ አንተ አትቆጣጠረውም። የሰዎችን ፀባይ አንተ መቀየር አትችልም። አንተ መቀየር ምትችለው ነገር ላይ ብቻ አተኩር። የማትችለውን ለፈጣሪ አስረክብ። ለባለቤቱ ስጠው። ታዲያ በጣም ያስቸገሩኝን ከባድ ችግሮች ለፈጣሪዬ እንዴት ላስረክበው? ልትል ትችላለህ። ወረቀት አውጣ። ያስጨነቁህንና ከአቅምህ በላይ የሆኑ ችግሮችን ዘርዝራቸው። ፈጣሪ ሆይ እነዚህን ችግሮች ለአንተ አስረክቤያለሁ በል።

የስራ ውል እንደምትገባ ሁሉ ከፈጣሪህ ጋር ውል ግባ። ትልቁ ችግርህን ከፈጣሪህ ጋር ንኡስ ኮንትራት አድርገው። ያኔ ቅልል ይልሃል። የሆነ ስሜት ይሰማሃል። አንበው ከአእምሮህ ወደወረቀቱ፤ ከወረቀቱ ወደፈጣሪህ ያ ችግር እንደሄደ ይሰማሃል። ስለዚህ አንተ የማትቆጣጠራቸውን ነገሮች አሳልፈህ ለፈጣሪህ ሰጥተሃል ማለት ነው። ህይወት ነፃ ታደርግሃለች። መጨነቅና አብዝተህ ማሰብ ታቆማለህ።

አንዳንዴ በጣም ለፍተህ ሰርተህ ውጤቱን መቆጣጠር አትችልም። ስለዚህ ውጤቱን ለፈጣሪህ አስረክበው። አንተ መዝራት ነው ስራህ። የሚያበቅለው ፈጣሪህ ነው። ለባለቤቱ አስረክብ። ነገን አትቆጣጠረውም። ሰዎችን አትቆጣጠርም። ሁኔታን መቆጣጠር አትችልም። አስረክበው ለፈጣሪህ። አይታወቅህም እንጂ ፈጣሪህ እንደሰው በግልፅ ስለማይሰራ ነው እንጂ ያን ችግርህን በስውር፤ በድብቅ እየፈታው ሊሆን ይችላል። አንተ ስለማታይ ነው። ስለዚህ ችግርህን ለፈጣሪህ አሳልፈህ ስጥ።

ከቅዱስ አማኑኤል የአእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# አማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የስልጠናና ምርምር አበርክቶዎች

ባለፉት ተከታታይ እትሞቻችን የሆስፒታሉን አመሠራረት እና በኢትዮጵያ የአዕምሮ ሕክምናን የረጅም ዘመን ጉዞ፤ ተቋሙ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ማስቃኘታችን ይታወሳል ለዛሬው ዝግጅታችንም በስልጠናና ምርምር ዘርፍ የተሠሩና እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችን እንዲሁም የላብራቶሪና የመድኃኒት አገልግሎትና የታካሚዎች ሁኔታ እንደሚከተለው አቅርበናል።

ከስልጠናና ምርምር ሥራው ጋር በተያያዘም ሆስፒታሉ ከተለያዩ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በሁለተኛ የዲግሪ መርሃ-ግብር በጋራ እየሠራ ይገኛል። በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የተቀናጀ የክሊኒካልና የሕብረተሰብ አዕምሮ ጤና ትምህርት የሚከታተሉ ተማሪዎች የንድፈ-ሃሳብና የተግባር ትምህርታቸውን በተቋሙ እንዲከታተሉ በማድረግ እና በማስተማር በርካታ የህክምና ባለሙያዎችን ማፍራትም ችሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ለሚገኙ የህክምና ተቋማት ባለሙያዎችን በመላክ በሚሰጥ ስልጠና (Outreach Training) እና የአዕምሮ ህመም ጉድለቶች (Mental health gap) በመለየት እውቅና ያለው የአሠልጣኞች ስልጠና እና የባለሙያዎችን የክህሎትና እውቀት ክፍተት ሥልጠናዎችን በመስጠትና የሱፐርቪዥን ድጋፍ በመዘርጋት አገልግሎቱን በስፋት እየሰጠም ይገኛል፡፡

የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ማዕከል

በሀገሪቱ ውስጥ ጥራቱን የጠበቀ የጤና አገልግሎትን በቀጣይነት ለማሻሻል ብቃት ያለው የጤና ባለሙያ እጅጉን አስፈላጊ መሆኑ ይታወቃል። ለዚህም የጤና ባለሙያዎች ብቃት ደረጃውን በጠበቀ የሥራ ላይ ሥልጠና በቀጣይነት ሊደገፍ እንደሚገባ የኢትዮጵያ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ መመሪያ ያስቀምጣል፡፡ በተጨማሪም የተከታታይ ሙያ



**የአማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል**

ማጎልበቻ ሥርዓት ዋናው ዓላማ ጥራቱን የጠበቀ የጤና አገልግሎትን ብቃት ባለው የጤና ባለሙያዎች ለመስጠት የተከታታይ ትምህርት መለኪያን (CEU) ከሙያ ሥራ ፈቃድ ጋር ማስተሳሰር እንደሚያስፈልግ ያስቀምጣል፡፡

የአማኑኤል አዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታልም የፌዴራል ጤና ሚኒስቴር ያዘጋጀውና ተግባራዊ እያደረገ ያለውን የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ መመሪያና ዳይሬክቲቭ ተግባራዊ ለማድረግ ከጥቅምት 09 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ሰጪ ፍቃድ በማግኘት የጤና ባለሙያዎችን የሥራ ላይ የክህሎት፣ የዕውቀትና የአመለካከት ክፍተቶችን በመለየት የአቅም ግምባታ ሥልጠና እያዘጋጀና እየተሰጠ ይገኛል፡፡

የተከታታይ ሙያ ማጎልበቻ ማዕከሉ የተለያዩ የጤና ዘርፍ ላይ ተመድበው እየሠሩ ላሉ ለጤና ባለሙያዎች ዘርፈ ብዙ ሥልጠናዎች ከመስጠት በተጨማሪ በሀገር ደረጃ እጥረት የሚታይበት የአዕምሮ ጤናና የአዕምሮ ህክምና የሥልጠና ማኑዋሎችን የማዘጋጀትና የማሠልጠን ሥራ ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ነው። በቅርቡ የሥልጠናዎቹን ተደራሽነት ለማስፋት በክፍል ውስጥ ከሚሰጠው ሥልጠና በተጨማሪ የኤሌክትሮኒክስ ሥልጠናም ጀምሯል፡፡ ከምድብ አንድ የሥልጠና አይነቶች በተጨማሪ የምድብ ሁለት የሥልጠና አይነቶችና በቪዲዮ ኮንፍረንስን በቅርቡ ለመጀመር ታቅዷል፡

የመድኃኒት አቅርቦት

ሆስፒታሉ መድኃኒቶችን በዋናነት ከኢትዮጵያ መድኃኒት አቅርቦት ኤጀንሲ (E.P.S.A) የሚያገኝ ሲሆን በተጨማሪም ከሌላ የግል የሕክምና ተቋማት ጋር በጋራ በመሥራት አቅርቦቱን ለማሻሻል ሰፊ ሥራ እየሠራ ይገኛል፡፡ የአዕምሮ ሕክምና መስጫ መድኃኒቶች አቅርቦት በግል ባለመገኘቱ ሆስፒታሉን ብቸኛ አቅራቢ ሆኖ እንዲሠራና የመድኃኒት አቅርቦት ጫና እንዲኖርበት አድርጓል፡፡ ይህ የሆስፒታሉ የመድኃኒት አቅርቦት በሦስት መሰረታዊ ደረጃ ላይ የተመሰረተ ነው፡ ፡ እነሱም አሁን ላይ የመድኃኒት አቅርቦቱን በተመለከተ (በ2014 በጀት ዓመት) ህይወት አድን መድኃኒቶች (Vital) 92 በመቶ፤ መሰረታዊ የሆኑ (Essential) 95 በመቶ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ሆስፒታሉ በአሁኑ ጊዜ መድኃኒቶችን ከጥራት፤ ከዓይነትና ከአቅርቦት አንፃር ወደ 94 በመቶ ማሳደግ የቻለ ሲሆን የመድኃኒት አቅርቦቱንም ለሕብረተሠቡ ተደራሽ ለማድረግና በተመጣጣኝ ዋጋ ማግኘት እንዲችል የማሕበረሰብ አቀፍ ፋርማሲ አገልግሎቶች በሦስት የተለያዩ ቦታዎች ላይ ተግባራዊ እንዲሆን አድርጓል፡፡ የላብራቶሪ አገልግሎትን በተመለከተ በሆስፒታሉ የሚታዘዙ የላብራቶሪ ምርመራዎች 84 ዓይነት ለማድረስ ታቅዶ 80 አይነቶችን መሥራት ተችሏል፡፡

የታካሚዎች ሁኔታ

የአማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በ2013 በጀት ዓመት ውስጥ ብቻ በተመላላሽ ሕክምና 116 ሺ 523 በተኝቶ ሕክምና 1ሺ 434 ፤ በድንገተኛ የአዕምሮ ሕክምና 7ሺ 067 ታካሚዎች የህክምና አገልግሎቱን ያገኙ ሲሆን በአጠቃላይ በ2013 በጀት ዓመት ውስጥ 125 ሺ 024 ታካሚዎች በ13 የሕክምና ክፍሎችና በ236 አልጋዎች ሕክምናቸውን የአገልግሎት ጥራቱንና ብቃቱን ጠብቆ እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን በ2014 ዓ.ም ደግሞ በተመላላሽ 128 ሺ 129 በተኝቶ 1ሺ 791 እንዲሁም በድንገተኛ 6ሺ 425 በአጠቃላይ 136ሺ 345 ታካሚዎች የሕክምና አገልግሎት ለመስጠት አቅዶ በእቅዱ መሰረት እየሰጠ ይገኛል፡፡


## ማስታወቂያ

የተቀናጀ ዘላቂ ልማት ፕሮጀክት በጎ አድራጎት ድርጅት የተባለ "ቦርድ መር" ሆኖ ለመመዝገብ ለሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን የምዝገባ ጥያቄ አቅርቧል፡፡ ተቃዋሚ ካለ እስከ ሚያዝያ 27 ቀን 2015 ዓ.ም. በኢ.ፌ.ዴ. ሪ ለሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ህብረት ኢንሹራንስ ህንፃ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 407 ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ይቅረብ፡፡

**የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን**

## ማስታወቂያ

ፓን-አፍሪካን የወባ ትንኝ መቆጣጠሪያ ማህበር የተባለ ድርጅት ከዚህ በፊት ያልነበረ ሲሆን ከዚህ በታች በተቀመጠው አርማ የሚጠቀም መሆኑን እያሳወቅን፡፡

ተቃዋሚ ካለ እስከ ሚያዝያ 27 ቀን 2015 ዓ.ም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ሕብረት ኢንሹራንስ ሕንፃ 4ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 407 ድረስ ከጠዋቱ 2፡30 ጀምሮ ማቅረብ የሚችል መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን**

## INVITATION FOR BID

**TENDER Ref. No. NCB/OCC-049/2023**

**Oromia Construction Corporation (OCC)** has intended to invite eligible bidders for the Procurement of **Different Electro mechanical Equipment** (Generator, surface pump, Submersible pump, Riser pipe, Over Head Crane, Surge vessel, Calcium hydrochloric preparation system, solar power for chlorination system) for yabelo town Bulbula and Hara kelo wadera water supply project.

Therefore, interested bidders are invited to participate for the supply of the item/items mentioned above on the basis of the following conditions.

Those who owned renewed relevant license, Supplier's Registration Certificate, VAT Reg. Certificate, TIN Number & Tax Clearance letter can purchase a complete bidding document upon payment of **nonrefundable** Birr **500 (Fife Hundred Birr and 00/100)** in cash.

1. Obligatory to provide bid security of ***Birr 500,000.00(Fife Hundred Thousand Birr and 00/100)the*** form of **C.P.O** or **unconditional bank guarantee.**
2. Bid will be closed on ***May* 25/2023 G.C at 2:00 P.M.** and opened on the same **date at 2:30 P.M.**
3. OCC reserves the Right to Accept or Reject Partially or the entire bid.

**Address: Procurement Directorate at Kality**
**Road in front of Drivers Training Center Near CCRDA**
**+251-11-439-04-78 FAX.** No. **0114396476/0114390546/0114396594**

**Oromia Construction Corporation (OCC)**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ቅሳነት ስዩም በርሀ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A45425 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር JALK6A13XG7102993 ሞዴል FSR6MF የሞተር ቁጥር 6HH1-489113 የሊብሬ ቁጥር 520198 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ18/8/2015 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የየካ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ብቃት የአሽከርካሪዎች ማሰልጠኛ ት/ቤት ሃ/የተ/የግ/ማ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-25477 የተሽከርካሪው አይነት አነስተኛ አውቶቡስ (ከ12 ያነሰ መቀመጫ) የሻንሲ ቁጥር JT121LHA200018096 ሞዴል LH102-RBMRSW የሞተር ቁጥር 2L-2412631 የሊብሬ ቁጥር 606761 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ17/8/2015 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን**
**የአዲስ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አብዱርሃማን ገና በየነ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-88753 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር JAMKP34H7D7P04547 ሞዴል NPR6SN የሞተር ቁጥር 4HG1-054436 የሊብሬ ቁጥር 215667 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ5/8/2015 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፤ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን**
**የአቃቂ ቃሊቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

አመልካች፡-እቴነሽ ሀድጋይ ዘውዴ ተጠሪ፡- ፍሬው ሀድጋይ ዘውዴ አመልካችና ተጠሪ ለአመልካች ወንድሜ ሲሁን ይህ ወንድሜ ከሚኖርበት ከጉለሌ ክ/ከ ወ/ 01 የቤት ቁጥር 474 ከሆነው ውስጥ ከጥር ወር 2005 ጀምሮ እንደወጣ እስከ አሁን ድረስ ሳይመለስ ቀርቷል፡፡


ስለዚህ ተጠሪ ወንድሜ ፍሬው ሀድጋይ ዘውዴ ያሉበትን ወይም አድራሻውን እናውቃለን የሚል ካለ በ 30/8/2015 ዓ.ም አ/አ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉለሌ ክፍለ ከተማ ምድብ ፍ/ብ/ችሎት 3፡30 ሰዓት ቀርቦ እንዲያስረዳ እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የጉለሌ ምድብ ችሎት**

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## ስለስልጡን ከተማ እውነነት




**መሳኩ ኤሮሴ**

የወደፊት ከተሞች ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ በዳታ ወይም መረጃ ትንተና ላይ ተመስርቶ እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ለነዋሪዎች ምቹ እንዲሆን ለማድረግ ስልጡን ከተማ ወይም “ስማርት ሲቲ” የተሰኘ ከተሞችን የማዘመን ሀሳብ በተለያዩ ሀገራት በተግባር እየተሞከረ ይገኛል፡፡ የስልጡን ከተማ ወይም ስማርት ሲቲ ሀሳብ የሰው ልጆችን ሀሳቦች በማሽን በመተግበር ሰዎች ያለባቸውን ውስንነት በሰው ሰራሽ አስተውሎት ወይም በአርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ የማበጀቱ አንዱ አካል ነው፡፡

በዓለማችን ከሚኖረው ህዝብ ግማሽ የሚሆነው በከተማ እንደሚኖር መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ የከተማ ነዋሪ ህዝብ ቁጥር እያደገ ስለመምጣቱም ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ የከተማ ህይወት በራሱ በርካታ ውስብስብ ሂደቶች ያሉት በመሆኑ እንዲሁም በነዋሪው ቁጥር መጨመር ሳቢያ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ይስተዋላሉ፡፡ የነዋሪው ጥግግት እና የትራፊክ መጨናነቅ፣ የአየር ብክለት እየጨመረ መምጣት፤ የውሃና የሀይል ፍላጎት እና አቅርቦት አለመጣጣም፣ ከብዙ በጥቂቱ የሚጠቀሱት ናቸው፡፡ ስልጡን ከተማም እነዚህን ፈተናዎች ቀላል የማድረግ ጽንሰ ሀሳብ ስለመሆኑ የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ፡፡

ለምሳሌ በስልጡን ከተማ ጽንሰ ሀሳብ የከተማ መብራት ያለ ምሰሶ አገልግሎት እንዲሰጥ ማስቻል፣ የብሮድ ባንድ ኢንተርኔት አገልግሎት፣ ሹፌር አልባ ተሽከርካሪዎች በመጠቀም የትራፊክ አደጋን መቀነስ፣ ድሮን እና ሮቦቶችን የህዝብ አገልጋይ እንዲሆኑ ማድረግ፣ የእሳት አደጋ መከላከል ስራን በአርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ የታገዘ እንዲሆን ማድረግ ባደጉት ሀገራት በስልጡን ከተማ ትግበራ ሙከራ ላይ ካሉ ሀሳቦች መካከል ይጠቀሳሉ፡፡

አንድ ከተማ ስልጡን ከተማ (ስማርት ሲቲ) ይሁን ከተባለ በከተማው ውስጥ ያሉ እንቅስቃሴዎችን የሚገነዘቡና ዳታ የሚሰበስቡ የኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂዎችን በየቦታው ተደራሽ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህም ስለትራፊክ ቁጥጥሩ፣ ስለአየር ብክለት እና ስለሌሎች ጉዳዮች የተፈለገውን መረጃ ለመሰብሰብ ያስችላል፡፡ ስለዚህ ግዙፍ መረጃዎችን መሰብሰቡ ብቻ ግብ አይደለም፡፡ ይህንን ዳታ በመሰብሰብና በሰው ሰራሽ አስተውሎት በመተንተን መፍትሄ ማፍለቅ ይጀመራል፡፡ ያኔ የስልጡን ከተማ ጽንሰ ሀሳብ ተግባር ላይ ዋለ ማለት ነው፡፡

በዚህ መንገድ በዓለማችን በርካታ ከተሞች ለችግሮቻቸው መፍትሄ እየተበጀላቸው ነው፡፡ ባደጉት ሀገራት በሚገኙ በአንዳንድ ከተሞች አረንጓዴ ስፍራዎች በተገጠመላቸው ሴንሰሮች ውሃ እንዲጠጡ ይደረጋል፤ የቆሻሻ ገንዳዎችም ገና ከመሙላታቸው ይነሳሉ፡፡ በአንዳንድ ከተሞች የተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ ክትትል የሚደረግላቸው በሰው ሰራሽ አስተውሎት ነው፡፡ በአንዳንድ ከተሞች ደግሞ የሮቦት ፖሊሶች የከተማ ጥበቃ ስራ ላይ ተሰማርተዋል፡፡ ከተሞች ሰው ሰራሽ አስተውሎትን ተጠቅመው የአገልግሎት አሰጣጥ ግልፅነትን በማስፈን ሙስናን መከላከል እየቻሉ ስለመሆናቸው መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

ጁኒፐር የተሰኘ በዘርፉ ጥናት የሚያደርግ ተቋም እንዳሳወቀው፤ በስልጡን ከተማ መረጃ መሰብሰብ የሁልጊዜም ስራ ነው፡፡ የሚሰበሰቡ መረጃዎችን ሰንዶና ተንትኖ መፍትሄ ለማምጣት ለሚሰሩ ኩባንያዎች በሀብት ፈጠራና በስራ እድል ፈጠራ አይነተኛ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡ እንደ ጥናት ተቋሙ ትንበያ ወደፊት ገበያ ይደራላቸዋል ተብለው የሚጠበቁት በአብዛኛው ግዙፍ ዳታ በመሰነድና በመተንተን ትልቅ ሚና የሚጫወቱት ስልተቀመር / አልጎሪዝም/ ባለቤት የሆኑ ተቋማት ናቸው፡፡

በሀገራችን ከተሞች ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት አለመዘርጋቱ፣ ከተሞቹ በፕላን እንዲመሩ ምቹ ሁኔታዎች አለመፈጠራቸውና በከተሞች ዕድገት ዙሪያ ወጥ ግንዛቤ አለመኖር በዜጎች ላይ የመልካም አስተዳደር ችግር እየፈጠረ ስለመሆኑ ሲገለጽ ቆይቷል፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍ እንደ መፍትሔም በሀገሪቱ በተመረጡ ከተሞች ከየሀገራቱ ስልጡንና ተመራጭ ከተሞች ልምድን በመቀመር የስልጡን ከተማ የ“ስማርት ሲቲ” ጽንሰ ሃሳብን ተግባራዊ ለማድረግ እየተሰራበት ይገኛል፡፡

በከተማና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ኢትዮጵያ በዴቻ እንደሚሉት፤ በኢትዮጵያም ከተሞችን ስልጡን ለማድረግ ስትራቴጂ ተነድፏል፡፡ ይህ ስትራቴጂ በቅድሚያ ስለ ስልጡን ከተማ ጽንሰ ሀሳብ በአግባቡ ማስተዋወቅ እንደሚያስፈልግ አስቀምጧል፡፡ በተለይም ለከተሞች አመራሮች ማስተዋወቅ እንደሚያስፈልግ አቅጣጫ ያስቀመጠ ነው፡፡ የማስተዋወቅ እና ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ከተሰራ በኋላ የሚመራበትን ስትራቴጂ ማዘጋጀት እንደሚያስፈልግም በግልጽ አስፍሯል፡፡

ይህንን ስራ ለመስራት ስትራቴጂውን በተለያዩ አካላት የማስተቸት እና ግብዓት የማሰባሰብ ስራ የተሰራበት አውደ ጥናት በቅርቡ በአዳማ ከተማ መካሄዱን የጠቆሙት አቶ ኢትዮጵያ፤ መድረኩም በሚኒስቴር መ/ቤቱ የከተማ ፕላንና አከታተም መሪ ስራ አስፈጻሚ እና በኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ስራ አስፈጻሚ በትብብር የተዘጋጀ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ በመድረኩ ላይም የክልል አመራሮች፣ የከተማ ስራ አስኪያጆችና የፌዴራል ተቋማት ኃላፊዎች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

በርካታ የከተማ አመራሮች ከሁሉም የሀገሪቱ ክልሎች፣ የከተማ አመራሮች፣ ከክልሎች ቢሮ ሀላፊዎች ጀምሮ እስከ ከተማ ከንቲባና፣ ከተማ ስራ አስኪያጅ ድረስ ያሉ አካላት በተገኙበት ስትራቴጂው ተተችቷል፡፡ ስትራቴጂው ከተተቸ በኋላ፣ የተለያዩ ግብዓቶችን በማሰባሰብና እንዲዳብር በማድረግ ከተሞቹ ላይ በቀጣይ መሰራት የሚገባቸው ነገሮችን አመላክቶ ወደ ስራ ይገባል ብለዋል፡፡

ከሌሎች ሀገራት ጋር ሲነጻጸር የሀገራችን የከትመት ምጣኔ ዝቅተኛ ቢሆንም፤ የከትመቱ ፍጥነት ግን ከፍተኛ ነው ያሉት አቶ ኢትዮጵያ፣ የከትመት ፍጥነት ከፍተኛ መሆን ማለት ከገጠር ወደ ከተማ በሚደረገው የሰዎች ፍልሰት የታጀበ ፈጣን የከተሞች መስፋፋት አለ ማለት ነው ይላሉ፡፡ ይህንን ሁኔታ በስልጡን ከተማ ጽንሰ የከተሜነት ምጣኔ ማስተካከል ካልተቻለ ከፍተኛ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጫናዎችን ሊፈጥር ይችላል፡፡ ከተሞች የሀይል አቅርቦት ችግር፣ የትራፊክ መጨናነቅ፣ ከቆሻሻ አያያዝ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ችግሮች እንዲሁም የደህንነት ስጋት የሆኑ ጉዳዮችን ማስተካከል ትልቅ የከተማ ተግዳሮቶች ናቸው ብለዋል፡፡

የከተማ ህዝብ ቁጥር መብዛት ከተጠቀሙበት ዕድል ካልተጠቀሙበት ደግሞ ስጋት መሆኑን ገልጸው፣ የከተማ ህዝብ ምጣኔ ዕድገትን ስልጡን ከተሞችን በመፍጠርና ምቹ የመኖሪያ አካባቢ እንዲሆኑ በማድረግ የከተማ ነዋሪውን የኑሮ ደረጃ ማሻሻልና ፍላጎቱን ማርካት ይቻላል ብለዋል፡፡

ስልጡን ከተማን ለመገንባት የሰለጠነ የሰው ኃይል፣ የፋይናንስ እና የቴክኖሎጂ አቅምን የሚጠይቅ መሆኑንም ጠቅሰው፣ በአንድ ጊዜ ተሰርቶ የሚያልቅ እንዳልሆነና የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት ብዙ መስራት እንዳለበት እንዲሁም የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማትን ማጠናከር እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

ከዚሁ ጋር በማያያዝ የስልጡን ከተማ ምሰሶዎች ናቸው በማለት የገለጿቸው ስልጡን ኢኮኖሚ፣ አስተዳደር፣ ሞቢሊቲ፣ አካባቢ፣ ነዋሪ እና ኑሮ ወሳኝ መሆናቸውን አመልክተው፣ ከተሞችን ጽዱ፣ ውብና ማራኪ እንዲሁም ለኑሮና ለስራ ምቹ ለማድረግ ቅንጅታዊ አሠራር ቁልፍ ጉዳይ እንደሆነና የሁሉንም ተቋማት የጋራ ርብርብ እንደሚጠይቅ ገልጸዋል፡፡

እንደ አቶ ኢትዮጵያ ማብራሪያ፤ እነዚህን ችግሮች ስልጡን በሆነው መንገድ ማስተካከል ሲቻል ብቻ ነው የከተሜነትን ምጣኔና የከተማን ህብረተሰብ ከችግር መታደግ የሚቻለው፡፡ ይህንን ደግሞ የተለያዩ ሀገሮች ተግባራዊ አድርገውት ውጤታማ ስራዎችን እየሰሩ ናቸው፡፡ ሀገራችን ዘመናዊ ስልጡን ከተማን ለመፍጠር ከዓለም ወደኋላ የቀረች መሆኗን ጠቅሰው፣ ሌሎች ሀገራት የፈጸሙትን ስህተት ባለመድገም ፈጥኖ የሰለጠነ ከተማን ለመፍጠር ዕድል የሚሰጥ ሁኔታ እንዳለም አመላክተዋል፡፡

ይህም ማለት ከተሞችን በፕላን ከመምራት ጀምሮ ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማቶችን መዘርጋት፣ ከተሞች ስልጡን አገልግሎቶችን በማቅረብ ለኑሮና ለስራ ምቹ እንዲሆኑ ማድረግ ስልጡን ከተማ ተግባራዊ ማድረግ የሚቻልበት አንዱ ትልቁ እሳቤ ነው፡፡

አንድ ስልጡን ከተማ ከተማውን የሚመራበት፣ የሚያስተዳድርበት፣ ነዋሪዎች የሚፈልጉትን አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ የሚያደርግበት በቂ የሆነ የራሱ እቅድ ሊኖረው ይገባል፡፡ ይህንን ተግባራዊ ማድረግ የከተማ ነዋሪን ተጠቃሚ የሚያደርግ ሲሆን፤ የመሰረተ ልማት ዝርጋታዎች እና የአገልግሎት አቅራቢ ተቋማትን ያደራጃል፡ ፡ በዚህ ረገድ እንደ ሀገራችን ከተሞችም ብዙም የተሰሩ ስራዎች የሉም ብለዋል፡፡

የሀገራችንን ከተሞች ወደ ስልጡን ከተማነት ለማሸጋገር የሚደረገው ጥረት በተለያዩ ተግዳሮቶች የተከበበ መሆኑን የጠቆሙት ዳይሬክተሩ፤ አንደኛው ተግዳሮት የግንዛቤ እጥረት ነው ይላሉ፡፡ ስልጡን ከተማ ሲባል ቴክኖሎጂ የተሟላለት ከተማ ብቻ ተደርጎ የማየት ሁኔታ አለ፤ ይህ ግን ትክክለኛ ግንዛቤ አይደለም ምክንያቱም ስማርት ወይም ስልጡን ቴክኖሎጂ ብቻ አይደለም ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ኢትዮጵያ ማብራሪያ፤ አገልግሎት አሰጣጥ፣ አጠቃላይ በከተሞች ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶችን የመምራት፣ የመግራት እና የማስተካከል ሂደቶችን ያካተተ ነው፡፡ ስለሆነም እነዚህ ነገሮች እውን እንዲሆኑ እንቅፋት እየሆኑ ያሉ ተግዳሮቶች ይፈታሉ ተብሎ የታሰበው ከዘርፉ ተቋማት ባሻገር ባለድርሻ ተቋማት አሉ፡፡ እነዚህ ባለድርሻ ተቋማት በዋናነት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር፣ ኢትዮ ቴሌኮም፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አጀንሲ፣ የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ ማዕከል፣ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣንን ጨምሮ ሁሉም የስልጡን ከተማ ስትራቴጂ ትግበራ ባለድርሻ አካላት ናቸው፡፡ እነዚህ አካላት በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ስራው የሚመለከታቸው ናቸው፡፡

የከተሞችን አገልግሎት ስልጡን ሲደረግ ከላይ የተጠቀሱ ተቋማት ሁሉ የጉዳዩ ባለቤት ሆነው የሚሰሩ መሆናቸውን በመጠቆም፤ በመሆኑም እነዚህ አካላት ባለድርሻ በመሆናቸው ዙሪያ በቂ ግንዛቤ አልነበረም፡ ፡ በመሆኑም የጋራ የሆነ አረዳድ ይዞ ወደ ስራ ለመግባት ታስቧል፡፡ የግንዛቤ ክፍተት የማጥራት ስራ ይሰራል፡፡ ግንዛቤ በአንድ ጀንበር አይፈጠርም፡፡ ግንዛቤ የማስጨበጥ እና ስትራቴጂውን ወደ ስራ የማስገባት ስራ እየተሰራ ይቀጥላል፡፡

የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚያብራሩት፤ ስልጡን ከተማን እውን ለማድረግ የነቃ አመራር መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ስለ ቴክኖሎጂ በቂ እውቀት ያለው አመራር ስልጡን ከተሞችን እውን ለማድረግ ለሚደረገው ጥረት ሚናው የላቀ ነው፡፡

በቅርቡ በአዳማ በተካሄደው አውደ ጥናት የመድረኩ ተሳታፊዎች ከተሞችን ወደ ስልጡን ከተማ ለማሸጋገር በሚቻልበት ሁኔታ ዙሪያ ውይይቶችን ከማከሄዳቸው ባሻገር የአዳማ ከተማን የስልጡን ከተማ አተገባበር በአካል ተገኝተው መጎብኘታቸውን የጠቆሙት አቶ ኢትዮጵያ፤ የቀረበውን ሰነድ እና የተደረገውን የአካል ምልከታ መነሻ በማድረግ በውይይት መድረኩ ላይ የስትራቴጂ ጥናት ሰነዱን ለማዳበር የሚያስችሉ ግብአቶች ተገኝተውበታል ብለዋል፡፡ የስልጡን ከተማ ትግበራን በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ለማስጀመር የሚያስችል መነቃቃትም የተፈጠረበት መድረክ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የስልጡን ከተማ ጽንሰ ሀሳብ የከተሞች አገልግሎትን በማቀላጠፍ ረገድ ያለው ትልቅ ድርሻ ቢሆንም የመረጃ ምንተፋ ትልቁ ተጋዳሮቱ እንደሆነ ይነገርለታል፡፡ ስልጡን ከተማ ግንባታ ላይ ትኩረት ያደረጉ ሀገራት ይህንን ችግር ለመቅረፍ በሚያችሉ መፍትሄዎች ላይ ጭምር ትኩረት አድርገው ይሰራሉ፡፡ ሀገራችንም በስልጡን ከተማ ግንባታ ላይ ከምታደርገው ርብርብ ጎን ለጎን ስልጡን ከተማ ሲተገበር ሊፈጸም የሚችለውን የመረጃ ምንተፋ ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል አሰራርን ታሳቢ ያደረገ እንቅስቃሴ ልታደርግ ይገባል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ጥይት ሰውን እንጂ ዓላማን አይገድልም!

በዓለማችን የሚገኙ የአክራሪና ፅንፈኛ አስተሳሰብና ዓላማ ባለቤቶች ሰዎችን በመግደል ዓላማቸውንና ሃሳባቸውን ለመጫን ጥረት ያደርጋሉ።እነዚህ ኃይሎች ይህን የሚያደርጉት ሃሳባቸው በፖለቲካና የሃሳብ ትግል ማሸነፍ እንደማይችል እንዲሁም በፖለቲካ ገበያው ተቀባይነትና ዋጋ እንደሌለው ስለሚረዱ ነው።

የሃሳብ ብዝሃነት ፀጋ ነው።ብዙ ሃሳብ ሲኖር የተሻለ ለመምረጥ ዕድል ይሰጣል።የተሻለው ሃሳብ ደግሞ አገርንና ሕዝብ ያበለፅጋል፤ ሰላምና መረጋጋት ለማስፈን ያስችላል።የሃሳብ ብዝሃነትን ለማስተናገድ አለመፈለግ ግና የጥፋት እና የግጭት መንገድ ስለሆነ ለአለመረጋጋት መንስኤ በመሆን ሕዝብን እና አገርን ለችግር ይዳርጋል።ፅንፈኝነትና አክራሪነት እንዲገነግንም ዕድል ይሰጣል።

በየትኛውም ሁኔታ ሃሳብን በሃሳብ እንጂ በኃይልና በግድያ ለማስፈፀም መሞከር ትክክል አይደለም።ሃሳብን በሃሳብ ለማሸነፍ ደግሞ እውቀትም ብልሃትም ጥበብም ይጠይቃል።እውቀት፣ ብልሃትና ጥበብ ሳይኖር ሲቀር ሃሳብን በኃይል ለመጫን ጥረት ስለሚደረግ የሚወሰደው እርምጃም ግድያ ስለሚሆን ዳፋው ለብዙዎች ይደርሳል።ስለዚህ ይህ የጥፋትና የፅንፈኝነት መንገድ መወገዝ አለበት።ምክንያቱም የሃሳብ ልዩነትን በጉልበትና በኃይል ለመፍታት መሞከር ወይም መተግበር ጥፋት እንጂ ትርጉም የለውምና።ሰውን በጥይት መግደል ቢቻልም ሃሳብና ዓላማን ግን አይገድልም።ሃሳብንና ዓላማን በሃሳብና በዓላማ ማሸነፍ ካልተቻለ ደግሞ ተሸናፊው ገዳዩ ነው።

ከትናንት በስቲያ ሃሳብን በሃሳብ ማሸነፍ ያቃታቸው የታጠቁ ፅንፈኞች የብልጽግና ፓርቲ የአማራ ክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ግርማ የሺጥላን በሰሜን ሸዋ ዞን ልዩ ቦታው መንዝ ጓሳ በተባለ አካባቢ ለሥራ እየተንቀሳቀሱ ባሉበት ወቅት ጥቃት ፈጽመው ነፍሳቸውን ነጥቀዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ባስተላለፉት የኀዘን መግለጫ «ልዩነትን በሠለጠነ መንገድ መፍታት ባህል በሆነበት ክፍለ ዘመን፣ በሃሳብ የተለየንን ሁሉ በጠመንጃ ለማሳመን መነሳት የፅንፈኝነት የመጨረሻው ጥግ ነው። ተወልዶ ባደገበት አካባቢ፣ ከእኛ የተለየ ሐሳብ ማሰብ አልነበረበትም ብለው የሚያምኑ ነውጠኛ ፅንፈኞች የፈፀሙት አስነዋሪና አሰቃቂ ተግባር፣ ፅንፈኝነትን በጊዜ ታግለን ካላስወገድነው ወደ መጨራረስ እንደሚወስደን ጉልሕ ማሳያ ነው» ብለዋል።

የአንድን ሰው ሕይወት በመንጠቅ የሰውየውን ሃሳብና ዓላማ ማስወገድና ማሸነፍ እንደማይቻል፤ በአሁኑ ዘመን ልዩነትን በውይይትና በንግግር የሚፈታበት ሁኔታና ሥርዓት እያለ በኃይል ሃሳብንና ዓላማን ለመጫን የሚደረግ ጥረት የአክራሪነትና የፅንፈኝት እኩይ ተግባር መሆኑን ማረጋገጫ ነው።በየትኛውም ወቅት ሃሳብና ዓላማቸውን በኃይል ለመጫን ጥረት የሚያደርጉ ኃይሎች መቼም ቢሆን ሕዝባዊ ቅቡልነት የላቸውም።

አክራሪና ፅንፈኛ ኃይሎች ለሃሳብ ልዕልና በሃሳብ መታግልን ከመምረጥ ይልቅ በመሣሪያ ቃታ ሰውን መግደል እንደ ስልት ወስደዋል።ነገር ግን ይህ ተግባር የእነዚህን ኃይሎች መሸነፍ የሚያረጋግጥ እንጂ፤ የሕግ የበላይነት የተረጋገጠባትና የሃሳብ ብዝሃነት የሚከበርባት አገር ለመገንባት የተጀመረውን ጥረትና ጉዞ ማስቆም አይችሉም።ምክንያቱም የሚገድሉት ሰውን እንጂ አገርን የሚያሻግር ሃሳብንና ዓላማን አይደለምና።በተጨባጭ የዚህ ዓይነቱ አስተሳሰብ በዚህ ዘመን አይሠራም። ወደፊትም አይሠራም።

አሁን ባለንበት የ21ኛው ክፍለ ዘመን ልዩነት በምክክር እና በውይይት መፍታት ሲቻል የመሣሪያ አፈ ሙዝን በመፍትሄነት መጠቀም ተስፋ ቢስነትን ያመላክታል።ከዚህ ቀደምም አክራሪና ፅንፈኛ ኃይሎች በአቋራጭ ስልጣን ለመያዝ ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም።ነገር ግን አልተሳካላቸውም።ሰውን መግደልን አማራጭ ማድረጋቸው ግና ሃሳባቸው ወይም ዓላማቸው በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት እንደሌለው ከማረጋገጥ ውጪ የሚፈይደው ሌላ ነገር አይኖርም።

እነዚህ አክራሪና ፅንፈኛ ኃይሎች በሰለጠነ መንገድ ፖለቲካዊ አካሔዳቸውን ማስፈፀም የማይችሉና ሁልጊዜ ፀብና ግጭት በመፍጠር አጀንዳቸውን ለማስፈፀም ነፍጥ የሚያነሱ ከዘመኑ ፖለቲካ ስልጣኔ አንፃር ችግሮቻቸውን በውይይት ለመፍታት አቅም የሌላቸው፤ የህብረ ብሔራዊት ኢትዮጵያን ከፍታና አንድነት ለመናድ የሚታትሩ የአገር ጠላቶች ናቸው። በሃሳብ የተለየን ሰው በሃሳብ ሞግቶ፤ በአመለካከት የተለየን በአመለካከት ረትቶ መነጋገርና የሚበልጠውን የሚበጀውን ለአገርና ለወገን ፍሬ የሚያፈራውን ሃሳብ ማስፋትና ማጎልበት ሲቻል ክቡር የሆነውን የሰውን ልጅ እስከ መግደል መሄዳቸው መሸነፋቸውን ነው የሚያረጋግጠው።

በአቶ ግርማ ላይ የተፈጸመው ግድያ በአገራችን እየታየ ያለው የአክራሪነትና ፅንፈኝነት አስተሳሰብ እና ከአስተሳሰቡ የሚነጩ እኩይ ድርጊቶች ከፍተኛ አደጋ ውስጥ ሊከቱን እንደሚችሉም ተጨባጭ ማሳያ ነው። በአጠቃላይ ሰውን መግደል እንጂ ሃሳብንና ዓላማን መግደል አይቻልም!


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**የብልፅግና ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ አባል እና በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የብልፅግና ፓርቲ የአማራ ክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ የአቶ ግርማ የሺጥላ ህልፈተ ሕይወትን አስመልክቶ ከመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ ከክልሎችና ሌሎችም አካላት የተላለፉ የኀዘን መግለጫ መልዕክቶች፤**

## -የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ መልዕክት፡-

ሐሳብን በሐሳብ ማሸነፍ ያቃታቸው አካላት የወንድማችንን የግርማ የሺጥላን ነፍስ ነጥቀዋል። ልዩነትን በሠለጠነ መንገድ መፍታት ባህል በሆነበት ክፍለ ዘመን፣ በሐሳብ የተለየንን ሁሉ በጠመንጃ ለማሳመን መነሣት የጽንፈኝነት የመጨረሻው ጥግ ነው።

ተወልዶ ባደገበት አካባቢ፣ ከእኛ የተለየ ሐሳብ ማሰብ አልነበረበትም ብለው የሚያምኑ ነውጠኛ ጽንፈኞች የፈጸሙት አስነዋሪና አሰቃቂ ተግባር፣ ጽንፈኝነትን በጊዜ ታግለን ካላስወገድነው ወደ መጨራረስ እንደሚወስደን ጉልሕ ማሳያ ነው።

ነፍስህ በሰላም ትረፍ!



### - ከኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን የተላለፈ የኀዘን መግለጫ፡-

በወንድማችን አቶ ግርማ የሺጥላ በሥራ ላይ እያሉ በታጠቁ ኃይሎች በተፈጸመባቸው ጥቃት መገደላቸውን ስሰማ ከፍተኛ እና ጥልቅ የሆነ ኀዘን ተሰምቶኛል።

አቶ ግርማ እና የግል ጠባቂዎቻቸው ላይ የተፈጸመው ድርጊት ፍጹም ተቀባይነት የሌለው፣ የሕዝባችንን እሴት የማይመጥን ነውር እና ሕገወጥ ድርጊት ነው።

አቶ ግርማ የሕዝብ ሕይወት እንዲሻሻል የተሰጠውን ሕዝባዊ ኃላፊነት እየተወጣ የሚገኝ መሪ ሲሆን ህልፈቱ ለመላው ለክልላችን እና አገራችን ሕዝቦች ከፍተኛ ጉዳት ነው።

መንግሥት ይህን ድርጊት የፈጸሙ አካላትን ለሕግ በማቅረብ ተጠያቂ እንዲሆኑ ይሠራል።

ለወንድማችን ግርማ ፈጣሪ ነፍሱን በገነት እንዲያኖረው፣ ለቤተሰቦቹ፣ ለወዳጅ ዘመዶቹ እና መላው ሕዝባችንም መጽናናትን እንዲሰጥልን እመኛለሁ።

### - ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የተሰጠ መግለጫ፡-

ሚያዝያ 19 ቀን 2015 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ የብልፅግና ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ አባል እና በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የብልፅግና ፓርቲ የአማራ ክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ የተከበሩ አቶ ግርማ የሺጥላ እና የግል ጥበቃዎቻቸው ላይ የመንግሥትና የድርጅት ሥራዎችን በሰሜን ሸዋ ዞን ሠርተው ከመሀል ሜዳ ወደ ደብረ ብርሃን ሲመለሱ ልዩ ቦታው መንዝ ጓሳ አካባቢ በታጠቁ ፅንፈኛ ኃይሎች በደረሰባቸው ጥቃት ሕይወታቸው አልፏል።

በደረሰው ልብ ሰባሪ ጥቃት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የተሰማውን መሪር ኀዘን ይገልጻል፡፡ እነዚህ ፅንፈኛ ኃይሎች በሀሳብ ትግል ማሸነፍ ያልቻሉትን በኃይል ለማስፈፀም ያደረሱት ጥቃት ዓላማውን ማሳካት የማይችልና ጊዜው ያለፈበት፣ ዘመኑን ያልዋጀ የጥፋት መንገድ ስለሆነ አምርረን የምንታገለው ተግባር ነው፡፡

እነዚህ ፅንፈኛ ኃይሎች በክልሉ ውስጥ የሚፈጽሙትን ሥርዓት አልበኝነትና የሽብር ድርጊት ለመከላከል፤ ለመቆጣጠርና ሕግ ለማስከበር የክልሉ መንግሥት እርምጃ ይወስዳል:: የጥቃቱን አድራሾችም ለሕግ ያቀርባል፡፡ ማንኛውም በጥቃቱ የተሳተፉ ኃይሎችንና ተባባሪዎችን ሁሉ ከያሉበት ለሕግ በማቅረብ አስፈላጊው ፍትሕ እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡

መላው የክልላችን ሕዝብ የተፈጠረውን የሽብር ድርጊት ከማውገዝ ጀምሮ ወንጀለኞች ለሕግ ቀርበው ፍትህ እንዲረጋገጥ፣ አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርግና እንዲረጋጋ ጥሪ እናቀርባለን፡፡

የጥፋት ኃይሎች ከዚህ በላይ ዓላማ ያላቸው እና ክልሉን የማፍረስ ተልዕኮ ይዘው የሚንቀሳቀሱ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ከዚህ በኋላ የክልሉ መንግሥት እንደማይታገስ እና ጥብቅ እርምጃ እንደሚወስድ እናረጋግጣለን፡፡

የክልሉ መንግሥት ለቤተሰቦቻቸው፤ ወዳጆቻቸው፤ ለሥራ ባልደረቦቻቸው እንዲሁም ለመላው የክልላችን ሕዝብ የተሰማውን ጥልቅ ኀዘን ይገልጻል፡፡ ፈጣሪ ነፍሳቸውን በአፀደ ገነት ያሳርፍልን!

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ሚያዝያ 19 ቀን 2015 ዓ.ም
ባሕር ዳር

### - የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ ያስተላለፉት የኀዘን መግለጫ:-

ወንድማችን አቶ ግርማ የሺጥላ በሥራ ላይ በነበረበት በታጠቁ ኃይሎች ግድያ ተፈጽሞበታል። እንዲህ ዓይነት እብሪተኝነት ውድቀትን እንጂ ድልን አያጎናጽፍም። ጥፋትን እንጂ ሰላምን አይሰጥም።

የሕዝባችን የቆየ መገለጫው ሥርዓታዊነት፣ ፍትሐዊነትና እኩልነት ነው። ከዚህ ታሪኩና ሥነ ልቦናው ጋር የሚቃረኑ ተግባሮች በሙሉ ሥርዓት አልበኝነት የወለዳቸው ናቸው።

በሕግና ሥርዓት እንጂ በደቦ ፍርድ የግልም ሆነ የቡድን፤ እንዲሁም የሕዝብም ሆነ የአገር ጥቅምና ፍላጎት ማሳካት አይቻልም። ምክንያቱም የሥርዓት አልበኝነት የመጨረሻ መዳረሻው ጥፋትና መጠፋፋት ነው።

ስለሆነም የክልላችን ሕዝብ ዘላቂ ሰላሙን ለማረጋገጥ እንዲህ ዓይነት ሥርዓት አልበኝነትንና ሕገወጥ ተግባሮችን ከመንግሥት ጎን ቆሞ ሊያወግዝና ሊታገል ይገባል።

በወንድማችን አቶ ግርማ የሺጥላ ህልፈት የተሰማኝን ጥልቅ ኀዘን በክልሉ መንግሥትና በራሴ ስም እየገለጽኩ፤ ለክልላችን ሕዝብ፤ ለቤተሰቦቹና ለወዳጅ ዘመዶቹ በሙሉ መጽናናትን እመኛለሁ።

### - የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት:-

የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በክቡር ግርማ የሺጥላ ህልፈተ-ሕይወት የተሰማውን ጥልቅ ኀዘን ይገልፃል።

የብልጽግና ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ አባልና የአማራ ክልል የብልጽግና ፓርቲ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ክቡር አቶ ግርማ የሺጥላ ሚያዝያ 19 ቀን 2015 ዓ.ም በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን መንዝ ጌራ ወረዳ ልዩ ስሙ ጓሳ ተብሎ በሚጠራ አካባቢ የታጠቁ ፅንፈኛ ኃይሎች ባደረሱት ጥቃት የግል ጠባቂዎቻቸውን ጨምሮ ሕይወታቸው በግፍ ሊያልፍ ችሏል፡፡

ምክር ቤቱ በክቡር አቶ ግርማ የሺጥላ ሞት የተሰማውን ጥልቅ ኀዘን ገልጿል።

ክቡር አቶ ግርማ የሺጥላ በኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል የመቻቻልና የመከባበር የፖለቲካ ባህል እንዲያብብ፣ አብሮነትና ወንድማማችነት እንዲጠናከርና እንዲፀና ደከመኝ ታከተኝ ሳይሉ ሲለፉና ሲጥሩ ነበር።

እኩልነትና ማህበራዊ ፍትህ የነገሰባት ጠንካራ ሕብረብሔራዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት በሚደረገው ርብርብ ክቡር አቶ ግርማ የሺጥላ ከሌሎች የሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን የተሰጣቸውን ታላቅ ሕዝባዊ፣ ድርጅታዊና መንግሥታዊ ኃላፊነት በልበሙሉነት፣ በትጋትና በኃላፊነት ስሜት የተወጡ አመራር ናቸው፡፡

ክቡር አቶ ግርማ የሺጥላ አገር ወዳድ፣ ብልህ ቁርጠኛ የፖለቲካ አመራር የነበሩ ሲሆን ለአገርና ለወገን

የብልፅግና ፓርቲ ሥራ...ወደ 9ኛው ገጽ ዞሯል

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካሳቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

## ሕመም ያልጣለው፣ ችግር ያልፈታው ማንነት

መልካምሥራአፈወርቅ

መለስ ቀለስ የሚለው የጤናቸው ችግር በእጅጉ እየፈተናቸው ነው። እንዲህ መሆኑ ሮጠው ለሚያድሩት ወይዘሮ የበዛ ዕንቅፋት ሆኗል። ሁሌም ቢሆን ሀሳብ አያጣቸውም። ያለአባት የሚያድጉት ልጆች፣ የእሳቸውን እጅ ይጠብቃሉ። ያለገቢ የሚያድረው ጎጆም የግላቸው ዕዳ ነው።

ወይዘሮ ደጊቱ መኮንን እጃቸው ከሥራ፣ እግራቸው ከመንገድ ታቅቦ አያውቅም። ቤተሰብ ለማሳደር፣ ልጆች ለማሳደግ ለፍቶ አዳሪ ናቸው። ኑሮን ለማቅናት ለዓመታት በጉልት ንግድ ቆይተዋል። ማለዳ ነቅተው አትክልት ማምጣት፣ ያመጡትን ለይተው በችርቻሮ መሸጥ የእስከዛሬ መተዳደሪያቸው ነበር።

ደጊቱ አትክልቱን ተሸክመው ሰፈር ለማድረስ ሰፊ ትከሻ፣ ጠንካራ ጉልበት ያሻቸዋል። እስካሁን ይህን ለማድረግ ደክመው አያውቁም። አቅማቸው የቻለውን አምጥተው ለጉልት ሥራቸው ይደርሳሉ። አሁን ግን ይህ ዓይነቱ እውነት ታሪክ ብቻ ሆኗል። ትናንት ከእርሳቸው የነበረ ብርቱ ጉልበት ደክሟል። ብርቱ እጆቻቸው ከትጋት፣ ፈጣን እግሮቻቸው ከመሮጥ ታቅበዋል።

ወይዘሮዋ እንዲህ የሆኑበትን የክፉ አጋጣሚ ፈጽሞ አይረሱትም። የሕመማቸውን መነሻ ዛሬም ያስታውሱታል። አንድ ማለዳ ደጊቱ ማልደው ከቤት ወጡ። በጠዋት የመነሳታቸው ምክንያት እንደልማዳቸው ከአትክልት ተራ ለመሄድ ነበር። ዛሬም ክፉኛ እየሳሉ ነው። በጀርባቸው የሚወርደው የሞቀ ላብ ወበቅ ሆኖ ያጋያቸው ይዟል። የሰቀዛቸው ውጋት ቢያስጨንቃቸውም እጅ መስጠትን አልፈለጉም። ጥርሳቸውን ነክሰው ጉዞ ጀመሩ።

ሲመለሱ የጉልት ንግዱ ይቆያቸዋል። በዕለት የሚያገኙት ጥቂት ገቢ ቤት የሚደግፍ፣ ችግር የሚታደግ ነው። ይህን እያሰቡ ከአትክልት ገበያው ገቡ። እንደወትሮው ከሽንኩርቱ፣ ከድንቹ፣ ሸማመቱ። ሁሉም ማዳበሪያ ሆዱ ሲሞላ ታያቸው። አልበቃቸውም። ሊጨምሩ ፈለጉና ከቲማቲሙ በርከት አድርገው አከሉ። እያመማቸው ነው። ሳላቸው በርትቷል። ትኩሳቱ አይሏል።

የአትክልት ሸመታው እንዳለቀ ደጊቱ የሚሸከም ልጅ ጠርተው ከታክሲው አናት ማዳበሪያውን አስጫኑ። ውስጥ ገብተው ወንበር ሲይዙ ሕመማቸው እየበረታ፣ እየዞረባቸው ነበር። ልባቸውን ደግፈው ከሰፈር ደረሱ። ታክሲው የተጫኑ ማዳበሪያዎችን ሊያወርድ ከሰፈራቸው ቆመ።

### የተፈተነ ብርታት...

ደጊቱ ከነበሩበት ተነስተው ሊራመዱ ሞከሩ። እጅ እግራቸው ዛለ። ሰማይ ምድሩ ዞረባቸው፣ አቅም እየከዳቸው የጫኑትን ለማውረድ ሞከሩ። አልቻሉም። ማዳበሪያው እንደቀድሞ ልምዱ ከጉልቱ አልደረሰም። በሌሎች ትከሻ ተጭኖ ከቤታቸው ገባ።

ቀናት ተቆጠሩ። ደጊቱ ክፉኛ ታመዋል። ደረታቸውን ደግፈው ያለአፍታ እየሳሉ ነው። አትክልት የታጨቁ ማዳበሪያዎች እንደተቋጠሩ ሳይፈቱ ተቀምጠዋል። ቤት ከገቡ ጀምሮ ለገበያ አልበቁም። ተማሪዋ ልጃቸው ከቤት አትውልም። የእሳቸው መታመምና የሚተካቸው ሰው አለመኖር ዋጋ ያስከፍል ይዟል።

አሁን ለትርፍ የገዟቸው አትክልቶች እየተበላሹ ነው። ደጊቱ አንዳች ማድረግ አልቻሉም። ዓይናቸው እያየ ለኪሳራ ተዳረጉ። ቆጫቸው፣ አንገበገባቸው። ወይዘሮዋ ያለአንዳች መፍትሄ እንደተኙ ከረሙ። ለትርፍ የተገዙት አትክልቶች እንደዋዛ በስብሰው ከተጣሉ በኋላ የኑሮ ጉዳይ አስጨነቃቸው። አሁን እንደ ትናንቱ ለገበያ የሚተርፍ፣ ሮጦ የሚገባ ጉልበት የላቸውም። ልሞክር ቢሉም ሥራው ከሕመሙ አይስማማም። ተጨነቁ። ጊዜ ወስደው ስለነገው አሰቡ።

### ዳግም ስመቆም...

ደጊቱ አንድ ቀን ያሰቡትን ሥራ ጀመሩት። ከሰል በጋሪ አስምጥተው በችርቻሮ መሸጥ ያዙ። የተቋጠረው የላስቲክ ከሰል ዕለቱን መሄዱ ለገበያው መልካም ሆነ። የጤና ጉዳይ ግን መላ ታጣለት። ደጊቱ አሁንም ልባቸውን ይዘው ይስላሉ። ላብ ያጠምቃቸዋል፣ እጅ እግራቸው እየዛለ ይደክማቸዋል።

ሁሌም ለከሰል ችርቻሮው ማዳበሪያውን ፈተው ማዘጋጀት አለባቸው። ደቃቁን ከአንኳሩ፣ እንጨቱን ከድንጋዩ፣ ሊለዩት ግድ ነው። ይህ ሥራ እጅን ብቻ አቆሽሾ አያልፍም። ለእሳቸው የበዛ ድካም አለው። ሁሌም የከሰሉ ብናኝ በአፍ በአፍንጫቸው ይገባል፣ እያሳላቸው ይሠራሉ፤ እየደከማቸው ይቋጥራሉ።

> **በእሳቸው ዘንድ ደቃቅ ይሉት ከሰል አይባክንም። ያለው ተጠራቅሞ ከአመድ ከአፈሩ ተለውሶ «ጥፍጥፍ» ይሠራበታል። ጥፍጥፉ ልክ እንደከሰሉ ለማገዶ ይፈስጋል**

ሕመሙ ባስ ሲል ለጤናቸው ትኩረት ሰጡ። ከጤና ተቋም ተመላለሱ። ቆይቶ የሀኪም ውጤት ታወቀ። ጤናቸውን ክፉኛ ያወከው ችግር የሳንባ ሕመም ነበር። ደጊቱ ይህን እንዳወቁ ሕክምናውን ቀጠሉ። ለሦስት ወራት ከሥራ ታቅበው ከቤት ዋሉ። ሻል ሲላቸው አልዘገዩም። የታዘዘላቸውን የስድስት ወር መድኃኒት ጀምረው ወደ ሥራ ተመለሱ።

የከሰል ችርቻሮው ከሕመማቸው አይስማማም። ለመኖር ግን ከእሱ መታገል ግድ ይላል፤ ለመኖር በዚህ መስመር ማለፍ ያሻል። በታመሙ ጊዜ የተዝረከረከው የከሰል ትራፊ ዛሬም በደጃቸው ነው። ገንዘብ አውጥተውበታል፤ ጉልበት አፍሰውበታል። ላለመክሰር እሱን መሰብሰብ፣ ማስተካከል አለባቸው። የወቅቱ ዝናብ ደግሞ የሚያላውሳቸው አልሆነም። ከሰሉ የእንጀራቸው ምንጭ ነውና ከአፋቸው ‹‹ማስክ›› ሳይለዩ ሲተጉ፣ ሲደክሙ ይውላሉ። ሁሌም ፊታቸውን ከልለው ከሰሉን ይሸጣሉ።

### ኑሮን በትግል ...

በእሳቸው ዘንድ ደቃቅ ይሉት ከሰል አይባክንም። ያለው ተጠራቅሞ ከአመድ ከአፈሩ ተለውሶ ‹‹ጥፍጥፍ›› ይሠራበታል። ጥፍጥፉ ልክ እንደከሰሉ ለማገዶ ይፈለጋል። እሱም ቢሆን የገቢውን ያህል የራሱ ወጪ አለው። የተመረጠ አፈርና ደቃቅ ከሰል በኩንታል መግዛት አለባቸው።

የዝግጅቱ ድካም የበዛ ነው። ሲጠፈጠፍ ከተሰበረ ያከስራል፣ ርጥበት ካለ ለመድረቁ ጊዜን ይሻል። ሁሌም የእሱ ሥራ በፀሐይዋ ሙቀት የሚወሰን ነው። ያሉበት ሰፈር ውሃ የለውም። ጥፍጥፉን በአመድና አፈር ለውሶ ለመጋገር በቂ ውሃን ይጠይቃል። ይህን ለማድረግ ደጊቱ ውሃ መግዛት፣ ለጉልበት ዋጋ መክፈል አለባቸው። ምርጫ የላቸውም። የተጠየቁትን ሰጥተው ጥፍጥፉን እንደከሰሉ ለማገዶነት ይሸጡታል።

አንዳንዴ ውሃውን የሚያመጣ፣ የሚታዘዝ ይጠፋል። ደጊቱ ምርጫ ሲያጡ፣ ስለሥራው ሲጨነቁ ለሸክም ትከሻቸውን ይሰጣሉ። ዕለቱን እንዳሰቡት ቢሞክሩም ማግስቱን መመለስ አይችሉም። ደጋግሞ ሕመም የጎበኘው አካላቸው ይዝላል። በድካም ይንቀጠቀጣል።



ፎቶ፡ ኤዮብ ተፈሪ

ደጊቱ በተለያዩ ጊዜያት ቀዶ ሕክምና አድርገዋል። በእጅና እግራቸው ላይ የቀረው የጠባሳ ምልክት ዛሬም ድረስ ይታያል። ልጃቸውን ሲወልዱም ከዚህ አጋጣሚ አላለፉም። እንዳይሸከሙ፣ ሥራ እንዳያበዙ የተሰጣቸው የሀኪም ትዕዛዝ ተከብሮ አያውቅም። እስከዛሬ ደንበኞቻቸው ከሰል ሲገዙ ይታዘዛሉ። ካሰቡት የሚያደርሱትም በእሳቸው ጉልበት ነው።

### ብርቱ ማንነት...

ከሰልና ጥፍጥፍ መሸጥ ከጀመሩ ወዲህ የጎደለውን ለመሙላት ዕንቅልፍ ይሉት የላቸውም። የቀድሞው ብርታታቸው ቢፈተንም ለሥራ ያላቸው ፍላጎት አልጠፋም። ከብናኙ እየታገሉ፣ ከሸታው እየተጣሉ ኑሮን መግፋት ይዘዋል።

ወይዘሮዋ ቀጣዩን አዲስ ቀን መድኃኒት በመውሰድ ይጀምራሉ። መድኃኒቱ በቂ ምግብ፣ ወተትና ሌላም ድጋፍ ይፈልጋል። ቤት ያፈራውን ቀምሰው፣ ፈጣሪያቸውን አመስግነው ይውላሉ።

ደጊቱ ከሰል የመሸጥ ሕይወት ከባድ መሆኑን ያውቁታል። ሥራውን ለመለወጥ ግን ሌላ ምርጫ አላገኙም። ትንሽዋ ልጃቸው ዛሬም ድረስ ተማሪ ናት። አባቷ እሷን ነፍሰጡር ሳሉ ነበር በሞት የተለዩት። ለብቻቸው አሳድገው፣ አስተምረው ካሰበችው ለማድረስ ብዙ ዋጋ ከፍለዋል። በቀን ከአራት ቤት ልብስ አጥበው፣ እንጀራ ጋግረው ቀን ወጥተዋል። ዛሬ ልጃቸው በእርሳቸው ጥረትና ልፋት በግል ዩኒቨርሲቲ እየተማረች ነው። በአስራሦስት ዓመታቸው የወለዱት ትልቁ ልጅ ግን በኑሮ መክበድና በቤት ጥበት ከእሳቸው ከራቀ ቆይቷል።

### ዛሬን በነገ ውስጥ...

ወይዘሮዋ ከጥቂት ጊዜያት በፊት የቀበሌ ቤት አግኝተዋል። ይህ በመሆኑ ምስጋናቸው የላቀ ነው። እንዲያም ሆኖ የቤቱ ወጪ የዋዛ አይደለም። ለውሃ፣ ለመብራት፣ ያስፈልጋል። ለዕለት ወጪ፣ ለጓዳው ድጎማ፣ ለዕድርና ማህበራዊ ሕይወት ሁሉ መቀነታቸውን ሊፈቱ፣ ቦርሳቸውን ሊፈትሹ ግድ ይላል።

ደጊቱ ኑሮን አሸንፎ፣ ልጆች ለማሳደግ ያልሞከሩት የለም። በክፍያ የድግስ ወጥ ሠርተዋል። እጃቸው እስኪዝል በየቤቱ ልብስ አጥበዋል። እንጀራ መጋገር፣ የቀን ሥራ መከወን፣ የዕለት ተግባራቸው ነበር። በኮሮና ሰበብ ሥራው እስኪቀዛቀዝ ኑሯቸው በዚህ ጸንቶ ቆይቷል።

ቀድሞ የቆዩበት የወጥ ሥራ ይበልጥ ቤታቸውን ሲደጉም ነበር። አሁንም ቢሆን ዕድሉን ቢያገኙ ልባቸው ያሰበውን መሥራትን ያስባል። በእርግጥ ለዚህ ሥራ አቅምና ጉልበት ግድ ነው። እሳቸው እጀ መልካም ባለሙያ ሴት መሆናቸውን ያውቃሉ። አልቻሉም እንጂ ዛሬም ቢሆን ሁሉን ተቋቁመው ሥራውን ቢሞክሩት ይወዳሉ ።

ዘመነ ኮሮና ከእሳቸው ሕመም ተዳምሮ ደንበኞቻቸውን አርቋል። ይህን የሚያውቁት ወይዘሮ ፈተናውን ሰብረው መውጣት ይሻሉ። እንዲህ ማሰባቸው የተለየ ጉልበት አግኝተው አይደለም። ዛሬም በወጉ ያልሞላ ጓዳቸውን ያስባሉ። የከበደው የኑሮ ጫና አሁን ባላቸው ገቢ ብቻ አለመገፋቱ ያሳስባቸዋል።

የደጊቱ ከእጅ ወደአፍ ኑሮ ፈተናው ብዙ ነው። ጠንክረው ለመሥራት የጤና ችግር ይዟቸዋል። ይሁን ብለው እንዳይተዉት የሚተማመኑበት፣ ነገን የሚሻገሩበት በቂ ጥሪት የለም። የሕይወት መርሀቸው ግን ሁሌም በብርታት የተሞላ ነው። እሳቸው ያለፉበትን ፈታኝና ሻካራማ መንገድ ልጆቻቸው እንዲደግሙት አይሹም። የአቅማቸውን ሠርተው ድህነትን ማለፍ፣ መሻገር ይፈልጋሉ።

### ብሩህ ተስፋ ስስ ልጆች ...

ዘወትር እንደሚሉት እሳቸው በሕይወት እሳካሉ የልጆቻቸውን ትካዜ ማየት አይፈልጉም። በራሳቸው ትከሻ፣ በእጆቻቸው ብርታት ጥንካሬን ማሳየትና ማስተማር ዕቅዳቸው ነው። አሁን የሚኖሩበት የከሰል ንግድና አድካሚ ሥራው በየቀኑ ከሕይወታቸው አንድ ክር እንደሚመዝ ያውቃሉ። ጥቂት ቢያገኙበትም ብዙውን የሕይወት መልክ በግልጽ እየነጠቃቸው ነው።

ሁሉም የሆነው ስለልጆቻው መሆኑን ሲያስቡት ግን ውስጣቸው ደምቆ ይፈካል። በሥራ የሚዝል አካላቸው በብርታት ይቆማል። ደጊቱ አቅሙ ቢኖራቸው ከአቧራ የራቀ፣ ከብናኝ የጸዳ ንጹህ ቤት ቢገነቡ ይወዳሉ። ፍላጎት እንጂ በቂ አቅም ከእሳቸው እንደሌለ ሲያውቁ ግን ኀዘን ሲጎበኛቸው ይውላል። አንዳንዴ ደግሞ ሸክማቸውን የሚያቀል፣ ቀኝ እጃቸው የሚሆን አጋር ከጎናቸው ያለመኖሩ ትካዜን ይጠራባቸዋል።

ደጊቱ ዛሬም ቢሆን እንደቀድሞው መሥራትን ይሻሉ። ይህ እንዳይሆን በመውደቅ የተሰበረው ቀኝ እጃቸው ጥንካሬን ተነፍጓል። እንደትናንቱ እንጀራ መጋገር፣ ልብስ ማጠብ፣ ወጥ መሥራት አልቻሉም።

ደጊቱ ከዚህ ቀድሞ ሕመማቸውን ውጠው ለመሥራት ሞክረዋል። የውስጣቸውን ድካም ችለውም ከሥራ ውለዋል። ሁሉም ግን እንዳሰቡት አልሆነም። ሰባራው እጃቸው ከእሳቸው አላበረምና የልባቸውን አልሰማም፣ ከሀሳባቸው አልተስማማም።

ደጊቱ ብዙ የለፉላቸውን ልጆቻቸውን ዓለም ማየት ምኞታቸው ነው። ስለእነሱ ብዙ ሆነዋል፣ ጠቁረው ከስተዋል፣ አግኝተው አጥተዋል። እናም ያለፈው ድካማቸው ዛሬን አልፎ ነገን እንዲከፍላቸው ይሻሉ።

ደጊቱ ሁሌም እንዳለፈው ትናንት ብቻ መኖር ፍላጎታቸው አይደለም። ነገን በጤና ከቆሙ ኑሯቸውን መለወጥ፣ ሕይወታቸውን ማሻሻል ያቅዳሉ። ለዚህ ምኞታቸው መንግሥት ቀኝ እጃቸው እንዲሆን ማሰባቸው አልቀረም። ደሳሳዋ የንግድ ቤት በኮንቴነር ተለውጣ፣ በአካባቢው ውሃ መብራት ገብቶ፣ የእጃቸው ጥሪት ጨምሮ ማየት የዘወትር ህልማቸው ነው።

ይህ ህልም ዕውን እንዲሆን የአካባቢው አቅመ ደካማ እናቶች፣ ኑሯቸው ከእጅ ወደአፍ የሆነ ነዋሪዎች ሕይወት መለወጥ አለበት ብለው ያምናሉ። በአካባቢው አንዱ ከአንዱ የተሻለ ኑሮ የለውም። ሁሉም በዕድሜው የገፋና ተደጋግፎ መኖር የማይችል ነው።

ደጊቱ ስፍራውን ለአነስተኛ ንግድ ለማቋቋም የአስር ብር ዕቁብ ጥለው ቦታውን ካቆሙ ወገኖች አንዷ ናቸው። ዛሬ አብዛኞቹ በጤና ማጣትና በዕድሜ መግፋት ከቤት ውለዋል። እንዲህም እንዲያም ብለው የሚኖሩት እነ ደጊቱ የአንድ ወገን ድካማቸው በአንድ እጅ የማጨብጨብ ያህል ጎድሎባቸዋል። እሳቸውን መሰል ጠንካራ ሴቶች ዛሬን ኖረው ነገን ለመሻገር ተስፋ የሚሰጣቸው፣ ‹‹አለን፣ አለናችሁ›› የሚላቸውን አንደበት ይናፍቃሉ።

ኢኮኖሚ

ስኬት

# እፎይታን የፈጠረው የ«ሚካል» የንጽህና መጠበቂያ አቅርቦት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

የማህበረሰቡ ግማሽ አካል እንደሆኑ የሚነገርላቸው ሴቶች በማህበራዊና ኢኮኖሚ ዘርፎች ጉልህ አበርክቶ እያበረከቱ መሆናቸው ይታወቃል። ‹‹ሴት ልጅን ማስተማር ማህበረሰብን ማስተማር ነው›› የሚባለውም ሴቶች በተለይም በማህበራዊ ተሳትፏቸው የላቀ አበርክቶ ያላቸው በመሆኑ ነው። እነዚህ ሴቶች አቅምና ችሎታቸውን አውጥተው መጠቀም እንዲችሉ ትምህርት ዋናው ቁልፍ ጉዳይ ቢሆንም፤ ሴቶችን ከትምህርት ገበታ የሚያጎድሏቸው በርካታ ጉዳዮችን መጥቀስ ይቻላል። ከእነዚህ መካከልም የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ ምርትን በቀላሉ አለማግኘት አንዱ የራስ ምታት ነው።

የአብዛኞቹ ሴት ተማሪዎች ወርሃዊ ጭንቀት የሆነውን ከባድ ሸክም ለማቅለል ጥረት የሚያደርጉ ጥቂቶች ቢኖሩም፤ እነዚህ ጥቂቶች በርክተው ችግሩን በዘላቂነት መቅረፍ አልተቻለም። ዓመት ጠብቆ የሚከበረውን የሴቶች ቀን ወይም ማርች ስምንትን ጨምሮ የተለያዩ ቀኖችን በማስመልከት ሴት ተማሪዎች በንጽህና መጠበቂያ እጦት ምክንያት ከትምህርት ገበታ አይጉደሉ በማለት ጥረት የሚያደርጉ ግለሰቦችና ድርጅቶች ጥቂት የሚባሉ አይደሉም።

ከእነዚህም መካከል አደይ ዘላቂ የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ ድርጅት አንዱ ነው። የድርጅቱ መስራች ወይዘሮ ሚካል ማሞ፤ የብዙ ሴቶች በተለይም የበርካታ ተማሪዎች ወርሃዊ ፈተናን ለማቃለል የሚታጠብ የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ እያመረተች ከከተማ እስከ ገጠር ተደራሽ ለመሆን እየተጋች ትገኛለች።

አዲስ አበባ ከተማ ተወልዳ ካቴድራል ትምህርት ቤት የተማረችው ሚካል፤ የመጀመሪያ ዲግሪዋን በንግድ አስተዳደር አግኝታለች። በአብዛኛውን ጊዜዋንም በሥራው ዓለም በግል ሥራ አሳልፋለች። ከተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ የውጭ ድርጅቶች ጋር የመሥራት ዕድልም አግኝታለች። በተለይም ዓለም አቀፍ ከሆኑ እርዳታ ለጋሽ ድርጅቶች ጋር በነበራት ቀረቤታና የሥራ ግንኙነት ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የወር አበባ መቀበያ ድህነት መረዳት ችላለች።

ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሴት ተማሪዎች በንጽህና መጠበቂያ ምርት እጦት በብዙ እየተፈተኑ እንደሆነና ችግሩ ስር የሰደደ መሆኑን የተረዳችው ሚካል፤ በወቅቱ የልጆች ልብስ በማምረት ሥራ ላይ ተሰማርታ እንደነበር ታስታውሳለች። የችግሩ አሳሳቢነት የቱን ያህል እንደሆነ ለመረዳት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ባሉ የተለያዩ ትምህርት ቤቶች ተዘዋውራለች። በወቅቱ ተማሪዎች በንጽህና መጠበቂያ እጥረት ምክንያት ከትምህርት መጉደላቸው ሳያንስ የሚፈጠርባቸውን የስነልቦና ጫና አሳዛኝና አስገራሚ በሆኑ ገጠመኞች ታጅቦ ከተማሪዎች አንደበት መረዳት ችላለች።

በመሆኑም ከወር አበባ ጋር ተያይዞ ያለውን ችግር በሚገባ ለመረዳት ጊዜ አልፈጀባትም። ያደመጠቻቸው ለማመን የሚከብዱ ታሪኮችም እንቅልፍ አልሰጧትም፤ እናም ሳትውል ሳታድር የህጻናት አልባሳት ማምረቷን አቁማ የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ ምርቶችን ለማምረት ስትወስን ሁለት ጊዜ አላሰበችም። የአፍሪካ መዲና በሆነችው አዲስ አበባ ከተማ ሳይቀር የወር አበባ መቀበያ ድህነቱ ሥር የሰደደ መሆኑን የተረዳችው ሚካል፤ ተማሪዎች በአማካኝ በአንድ ወር ውስጥ ከሶስት እስከ አምስት ቀናት በወር አበባ ምክንያት ከትምህርት ገበታቸው እንደሚጎድሉ፤ እንዲሁም ጭርሱኑ ትምህርት እንደሚያቋርጡ አጫውታናለች።

‹‹በወር አበባ ቁሳቁስ እጥረት ተማሪዎች እንዲሁም ሠራተኞች ሳይቀሩ ይቸገራሉ›› የምትለው ሚካል፤ ወደ ሥራው ስትገባ 10 ሚሊዮን ብር መነሻ ካፒታል በመያዝ የተለያዩ መነሻዎችን ወስዳ ማሽኖችን ከውጭ በማስመጣት ወደ ምርት ገብታለች። በወቅቱ ያመረተቻቸውን የንጽህና መጠበቂያ ምርቶች በምትኖርበት ለገጣፎ አካባቢ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች እንዲሁም ለተፈናቃዮች በመለገስ የጀመረች ሲሆን፤ በዋናነት ግን ትኩረቷ ተማሪዎች ከትምህርት ገበታ እንዳይጎድሉ ለማድረግ ነውና ትልቁን ትኩረት ለተማሪዎች አድርጋለች።

‹‹አደይ የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ ድርጅት እንደማንኛውም ቢዝነስ በንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለ ቢሆንም በዋናነት በማህበረሰቡ ላይ በጎ ተጽዕኖ የሚያሳርፍ ድርጅት ነው›› የምትለው ሚልካ፤ የንጽህና መጠበቂያ ምርቶቹን በተመጣጣኝ ዋጋ ለማህበረሰቡ የሚያደርስ



ወ/ሮ ሚካል ማሞ

እንደሆነና ማህበረሰቡ ላይ በሚያሳድረው በጎ ተጽዕኖ ደግሞ በሺዎች ለሚቆጠሩ ተማሪዎች ምርቶቹን የሚለግስ እንደሆነ ታስረዳለች። በቀጥታ ከሚለገሱት ተማሪዎች በተጨማሪ ከየትምህርት ቤቶቹ የሚመጡ የሴቶች ክለብ፣ ስካውትና ሌሎችም በበጎ ፈቃድ አገልግሎት የተሰማሩ ሴቶችን ለማነቃቃት በሚል ምርቶቹን በመለገስ ታግዛለች።

አደይ ዘላቂ የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ እየታጠበ ለሁለት ዓመት የሚያገለግል ሲሆን፤ አንዱ እሽግ አራት የንጽህና መጠበቂያዎችን በውስጡ ይይዛል። አንዲት ሴት አራቱን የንጽህና መጠበቂያዎች በንጽህና በመያዝ እየቀያየረች ለሁለት ዓመታት መጠቀም የሚያስችላት ይሆናል። ምርቶቹን ለማምረት ንጹህና ጥራት ያላቸውን ኮተን የሆኑ ጨርቆችን በግብዓትነት የምትጠቀም መሆኑን የጠቀሰችው ሚካል፤ ፈሳሽ የመምጠጥ አቅማቸውም የተሻለና ምቹ እንደሆነ ነው ያስረዳችው። ምርቱም በተለይም ገና የወር አበባ ማየት ለጀመሩ ኮረዳዎች ሴቶች ደስ እንዲላቸውና እንዲወዱት በማሰብ ባለአበባና ሳቢ በሆኑ ኮተን ጨርቆች ይዘጋጃል።

የጨርቅ ግብዓቶቹን ከዚህ ቀደም ከውጭ አገራት ታስመጣ እንደነበር የምታስታውሰው ሚካል፤ በአሁኑ ወቅት ግን በአገሪቷ ውስጥ ካሉ ትላልቅ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ጋር ትስስር በመፍጠር በብዛትና በጥራት እያመርቱ እንደሆነም ገልጻለች። ከዚሁ ጋር በተያያዘም ዘላቂ የንጽህና መጠበቂያ ዘላቂነቱ መረጋገጥ የሚችለው ሙሉ በሙሉ በአገር ውስጥ ምርት መመረት ሲችልና ከውጭ የሚገባውን ሞዴስ ማስቀረት ሲቻል እንደሆነ የምትናገረው ሚካል፤ አገር በቀል ምርቶችን በማበረታታት ከማህበራዊ አገልግሎቱ ባለፈ ኢኮኖሚውን መደገፍ እንደሚገባ አስረድታለች።

‹‹ለዚህም ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር እንዲሁም ከሴቶችና ህጻናት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ጋር በጋራ በመሆን ሴቶችን መደገፍ እንዲቻል እየተሠራ ነው›› የምትለው ሚልካ፤ ‹‹የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ›› እንዲሉ የሴቶች የራሳቸው ጉዳይ የሆነውን ዘላቂ የንጽህና መጠበቂያ ለማምረት ሴቶች ተሳታፊ እንዲሆኑና ምርቱም ሙሉ ለሙሉ በአገር ውስጥ እንዲመረት በማድረግ ከውጭ የሚገባውን ምርት ለማስቀረት በግሏ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቶቹ ጋር በመነጋገር ጥረት እያደረገች እንደሆነ አጫውታናለች።

የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ እጥረት እንደ አገር የሴት ተማሪዎች ፈተና ሆኖ መቀጠሉን ያመለከተችው ሚልካ፤ ሴት ተማሪዎች በዚህ ምክንያት ከትምህርት ገበታ ከመቅረታቸው ባለፈ ዛሬም የውስጥ ሱሪ ምን እንደሆነ የማያውቁ፣ የተፈጥሮ ህግ የሆነው የወር አበባ በመጣ ጊዜ ከቤተሰብ የሚገለሉና የሚሸማቀቁ ሴቶች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም ትላለች። ስለዚህ ከምርቱ ጎን ለጎንም የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶችን እንዲሁም የተለያዩ ቅስቀሳዎችና ጉትጎታዎች የግድ እንደሆኑ ነው ያስረዳቸው።

ምርቶቹን ከመለገስ በተጨማሪ ቅስቀሳ በማድረግና ግንዛቤ በመፍጠር ጭምር ማህበራዊ ኃላፊነቷን የምትወጣው ሚካል፤ አደይ ዘላቂ የንጽህና መጠበቂያን አምስት ሺ ለሚደርሱ ተማሪዎች በቋሚነት የምትለግስ ሲሆን፣ በተጓዳኝ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶችንና ቅስቀሳዎችንም ለተማሪዎችና ለሌሎችም ታደርጋለች። በተለይም ስለጉዳዩ ምንም አይነት ግንዛቤ ለሌላቸው እንዳይፈሩና የንጽህና መጠበቂያውን እንዲጠቀሙ ትምህርት ትሰጣለች። ይህን ተግባር የሚደግፉ አይ ኬር እና ጀግኒት ኢትዮጵያ የተባሉ ሁለት የበጎ ፈቃድ ድርጅቶች ስለመኖራቸው ያነሳችው ሚካል፤ ብርቄ በሚል መጠሪያ ‹‹አበባ አየሽ ወይ ትምህርት ቤት ትሄጃለሽ ወይ›› የሚል ንቅናቄው በ2014 ዓ.ም እንደጀመሩና በአሁን ወቅትም 50 ሺ ተማሪዎች ጋር መድረስ እንደቻሉ ነው ያስረዳችው።

በንቅናቄው አደይ ዘላቂ የንጽህና መጠበቂያ ምርቶቹን በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ እንዲሁም ሳሙናና ፎጣ በመጨመር ሁሉን አቀፍ በሆነችው የብርቄ ባልዲ ‹‹አበባ አየሽ ወይ ትምህርት ቤት ትሄጃለሽ ወይ›› በሚል የሚቀርብ ነው። የንቅናቄው ዋና ዓላማም በንጽህና መጠበቂያ እጦት ምክንያት ከትምህርት ገበታቸው የሚጎድሉ የሴት ተማሪዎችን ቁጥር ለመቀነስ እንደሆነ ሚካል አስረድታለች።

የ‹‹አበባ አየሽ ወይ ትምህርት ቤት ትሄጃለሽ ወይ›› ንቅናቄ ተማሪዎችን ብቻ ዓላማ አድርጎ የተነሳ ቢሆንም በአገሪቱ ውስጥ በነበረው ጦርነት ምክንያት ተማሪዎችን ጨምሮ በርካታ ሴቶች ተፈናቃይ በመሆናቸው ከተማሪዎች ውጭም በተለያዩ አካባቢዎች ተደራሽ መሆን ችላለች። አዲስ አበባ መርካቶ አካባቢ የሚገኙ እንደ ሃሌሉያ፣ ሜዴይና ፈለገ ዮርዳኖስ ትምህርት ቤቶች ላሉ ሴት ተማሪዎች የሚታጠብ የንህጽህና መጠበቂያ ምርቶቹን በቋሚነት ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪ ለአብነትም አፋር፣ ሀመር፣ ዋግህምራ፣ ሰቆጣ፣ ባሌ፣ ደብረብርሃንና ከሚሴ በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብና ተደራሽ መሆን ተችሏል።

ውሃ መቅጃ፣ ማጠቢያና ማስቀመጫ መሆን በምትችለው ባልዲ ሴቶች ዘላቂ የንጽህና መጠበቂያውን ጨምረው ምንም ሳይሳቀቁ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ እንደሚችሉ ያነሳችው ሚልካ፤ በተዘዋወረችባቸው አካባቢዎች የንጽህና መጠበቂያ ብቻ ሳይሆን የውስጥ ሱሪም የሌላቸው በርካቶች እንደሆኑ መታዘብ ችላለች። ሳሙናውና ውሃውም ቢሆን የብዙዎች አንገብጋቢ ችግር እንደሆነም ነው ያጫወተችን።

በአገሪቱ በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች በተለይም ርቀት ባላቸው አካባቢዎች ጭምር አደይ ዘላቂ የንጽህና መጠበቂያ ተደራሽ መሆን እንዲችል መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ የውጭ ድርጅቶች ጋር በጋራ እየሠራች እንደሆነ የተናገረችው ሚልካ፤ እነዚህ ድርጅቶች ምርቶቹን ከድርጅቱ ገዝተው በተለያዩ አካባቢዎች ተደራሽ የሚያደርጉ እንደሆነና የገበያ መዳረሻዋም በዚህ መልኩ እንደሆነ ነው ያስረዳችው። አንዳንድ ድርጅቶች ከንጽህና መጠበቂያው በተጨማሪም የውስጥ ሱሪዎችንም ጨምረው በመግዛት ተደራሽ እንደሚደርጉ ገልጻለች።

ዛሬም ድረስ ከባድ ራስምታት የሆነው የንጽህና መጠበቂያ በተለያዩ አካባቢዎች በተለየ መንገድ ይታያል ያለችው ሚካል፤ የውስጥ ሱሪ እንኳን የማያውቁ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ በርካታ ሴቶች የወር አበባው ፈሶ እስኪያልቅ አመድ ላይ በመቀመጥና ከቤታቸው ራቅ ብለው ላስቲክ አንጥፈው በመቀመጥ ጊዜውን የሚያሳልፉ ስለመኖራቸውም ትናገራለች። ሩቅ ሳንሄድ በየዩኒቨርሲቲው የሚገኙ ፍራሾች ስፖንጃቸው ተቦጫጭቆ የሚታየው የንጽህና መጠበቂያዎች መግዛት በሚቸገሩ ሴት ተማሪዎች ምክንያት ነው የምትለው ሚልካ፤ የችግሩ አሳሳቢነት ጥልቅና ሰፊ ነው ትላለች።

ከኮቪድ 19 ወረርሽኝ አስቀድሞ በተካሄደ ጥናት 72 በመቶ የሚሆኑ የወር አበባ ማየት የጀመሩ ሴቶች የንጽህና መጠበቂያ ማግኘት የማይችሉ እንደሆኑ የጠቀሰችው ሚልካ፤ ይህን ችግር ለማቃለል አገር በቀል የሆኑ ዘላቂ የንጽህና መጠበቂያ ምርቶች በሁሉም አካባቢዎች ተደራሽ መሆን እንዲችሉ መሥራት ያስፈልጋል ትላለች። አገር በቀልና ዘላቂ በሆኑ ምርቶች የእሴት ሰንሰለቱ ከምርቱ ጀምሮ እስከ ስርጭቱ ሁሉን ያማከለ መሆን አለበት። በተለይም ከምርት እስከ ስርጭት ሴቶች የሚመሩት ቢሆን ይበልጥ ውጤታማ መሆን ይቻላልም ብላለች።

ከአደይ ዘላቂ የንጽህና መጠበቂያ አምራች ድርጅት በተጨማሪ ሌሎች ተመሳሳይ ደርጅቶች ስለመኖራቸው ያመለከተችው ሚልካ፤ እነዚህን አምራቾች መንግሥት እንደ ሌሎች አምራች ድርጅቶች ሁሉ በአንድ አሰባስቦ ድጋፍና ክትትል ቢያደርግ በብዙ መልኩ ውጤታማ መሆን እንደሚቻል አስታውቃለች። በተለይም ከስልጠና ጋር በተያያዘ ሴቶችን በማሰልጠን የሰለጠኑት ሴቶች ደግሞ በየአካባቢያቸው አምርተው ተደራሽ ማድረግ እንዲችሉ በማድረግ ትርጉም ያለው ውጤት ማምጣት እንደሚቻል ነው ያስረዳችው።

‹‹አመቺ የሆነ የወር አበባ ቁስ ሳይቀርብ ሴቶችን ማብቃት አይቻልም›› የምትለው ሚካል፤ ሴት አምራቾችን ማበረታታት ተደራሽነትን ማስፋት እንደሚገባ ታስገነዝባለች። በወር አበባ ቁስ ምክንያት አንዲት ሴት በአማካኝ በዓመት 50 የትምህርት ቀናት ከትምህርት ቤት የምትቀር ሲሆን በዚህ ሁኔታ ሴቶችን ማብቃት የማይቻል እንደሆነና ብቁ ሴቶችን ማፍራት የሚቻለው የንጽህና መጠበቂያን ከማሟላት ጀምሮ እንደሆነ ነው ያስታወቀችው።

በአደይ ዘላቂ የንጽህና መጠበቂያ አምራች ድርጅት ውስጥ ለሚሠሩ 80 ሴቶች የሥራ ዕድል የፈጠረችው ሚካል፤ በቀጣይም ከንጽህና መጠበቂያ ምርቶች በተጨማሪ ሌሎች አልባሳትን ለማምረት ባገኘችው የማስፋፊያ ቦታ ላይ ተጨማሪ ማሽኖችንና ከ150 እስከ 200 ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር በዝግጅት ላይ ናት። በአሁኑ ወቅትም መደበኛ ከሆነው የንጽህና መጠበቂያ በተጨማሪ ለእርጉዞች የሚሆን የውስጥ ሱሪና አካል ጉዳተኛ ሆነው ዊልቸር ላይ ለዋሉ ሴቶች አመቺ የሆነ የንጽህና መጠበቂያ እያመረተች ለገበያ ታቀርባለች።

ተደራራቢ የአካል ጉዳት ላለባቸውና የአዕምሮ እድገት ውስንነት ለተጋለጡ ሴቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት የግድ እንደሆነ የጠቆችው ሚካል፤ በተለይም የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ሴቶች ስለምንነቱ መረዳት ባለመቻላቸው መጠቀም አይፈልጉም። ስለዚህ ለእነሱና መሰል ችግር ላለባቸው ሴቶች ማስተማር ግንዛቤ መፍጠር የግድና ዋና ሥራ እንደሆነም አጫውታናለች።

በመጨረሻም ዘላቂ የንጽህና መጠበቂያ ምርቶቹን ለሁሉም ኢትጵያዊ ሴቶች በተለይም ለተማረዎች ተደራሽ ማድረግ ዋናውና የሁልጊዜ ምኞትና ዕቅዷ እንደሆነ የገለጸችው ሚልካ፤ ይህን እቅድ ለማሳካትም ከላይ ታች በማለት ግስጋሴዋን ቀጥላለች። እኛም ይህ ዕቅዷ ተሳክቶ ዘላቂ የንጽህና መጠበቂያ ምርት ኢትዮጵያ ውስጥ ችግር መሆኑ እንዲቀር ልባዊ ምኞታችን ነው። ሰላም!

# ስፖርት





## ደራርቱ ቱሉ የአፍሪካ አትሌቲክስ ኮንፌዴሬሽን ምክትል ፕሬዚዳንት ሆና ተመረጠች

ቦጋለ አበበ

ረዳት ኮሚሽነር ጄነራል ደራርቱ ቱሉ የአፍሪካ አትሌቲክስ ኮንፌዴሬሽን ምክትል ፕሬዘዳንት ሆና ተመረጠች። የኢትዮጵያን አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በፕሬዚዳንትነት እየመራች የምትገኘው የቀድሞዋ የረጅም ርቀት ኮከብ አትሌት ደራርቱ በዛምቢያ ሉሳካ ከትናንት በስቲያ በተካሄደው የኮንፌዴሬሽን ኦፍ አፍሪካ አትሌቲክስ ኮንግረስ የአፍሪካ አትሌቲክስን በምክትል ፕሬዚዳንትነት እንድትመራ ካውንስሉ በሙሉ ድምፅ እንደመረጣት የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አስታውቋል።


ካሜሮናዊው ሃማድ ካልካባ የኮንፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት ሲሆኑ፤ አራት ምክትሎች አሏቸው። ከነዚህ መካከል ሶስቱ ወንዶች ሲሆኑ ደራርቱ ብቸኛዋ እንስት ምክትል ፕሬዚዳንት ሆናለች። ለቀጣዩ አራት አመታትም በዚህ ማዕረግ የአህጉሪቱን አትሌቲክስ ታገለግላለች።

"ሀገሬን ወክዬ በመመረጤ ደስ ብሎኛል፤ ኢትዮጵያ በአትሌቲክሱ አመራርነት በአፍሪካም ሆነ በአለም ከዚህ የበለጠ መወከል ይገባታል፤ አመራሮቻችንና ባለሙያዎቻችን ከፌዴሬሽናችን ባለፈ በአህጉራችንና በአለም የአትሌቲክስ ተቋማት ላይ ገብተው እንዲሰሩ ጠንክረን መስራት አለብን፤ በዚህ ኮንፌዴሬሽን የኬኒያው ጃክሰን ቲዊ ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት ሲሆኑ እኔ ምክትል ነኝ፤ ከምስራቅ አፍሪካ ኢትዮጵያና ኬኒያ በአመራርነት አለን፤ የተጣለብኝን ሀላፊነትና አደራ ለመወጣት ዝግጁ ነኝ" በማለት ደራርቱ ከሹመቱ በኋላ ለጋዜጠኛ ታምሩ አለሙ አስተያየቷን ሰጥታለች።

በአፍሪካ የመጀመሪያውን የአስር ሺ ሜትር የኦሊምፒክ የወርቅ ሜዳሊያ እኤአ 1992 ባርሴሎና ላይ በማስመዝገብ ዘመን ተሻጋሪ ታሪክ የሰራችው ደራርቱ ከኢትዮጵያ ባለፈ የአትሌቲክሱ ዘርፍ ላይ በትልቅ የአመራርነት ቦታ ስትሾም ይህ የመጀመሪያዋ አይደለም።ደራርቱ ከዓመታት በፊት የምስራቅ አፍሪካ አትሌቲክስ ዞን አምስት ምክትል ፕሬዚዳንት በመሆን ተመርጣ እያገለገለች እንደምትገኝ ይታወቃል።

30ኛው የአፍሪካ አትሌቲክስ ኮንፌዴሬሽን ኮንግረስ እና ካውንስል ስብሰባ ከትናንት በስቲያ ጀምሮ በዛምቢያ ዋና ከተማ ሉሳካ የተካሄደ ሲሆን፤ በዚህ ስብሰባ ላይ ኢትዮጵያን በመወከል ረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት እንዲሁም የምሥራቅ አፍሪካ አትሌቲክስ ሪጅን ምክትል ፕሬዚዳንትና የአፍሪካ አትሌቲክስ ኮንፌዴሬሽን ካውንስል አባል በመሆን ተሳታፊ ሆናለች።በተጨማሪም ዶክተር ተስፋዬ አስግዶም የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልና የአፍሪካ ከ18 እና አ20 አመት አትሌቲክስ ቻምፒዮና የኢትዮጵያ ቡድን መሪ፣ አቶ ዮሐንስ እንግዳው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጽህፈት ቤት ተወካይ በስፍራው ተገኝተው ስብሰባውን ተካፍለዋል።

ከኮንግረስ ስብሰባው አስቀድሞ የካውንስል ስብሰባ የተካሄደ ሲሆን፤ ኮንግረሱ ሲጀመር የዛምቢያ ስፖርት፣ ባህልና አርት ሚኒስትር፣ የዓለም አትሌቲክስ ፕሬዚዳንት ሎርድ ሳባስቲያን ኮይን ጨምሮ ጥሪ የተደረገላቸው የክብር እንግዶች ተገኝተዋል።ጉባኤው ያለፈውን አመት ስብሰባ ቃለ ጉባዔን፣ የስራ አፈጻጸምን፣ የቴክኒካዊና ልማት ሪፖርቶችን አቅርቦ በመመርመር ያጸደቀ ሲሆን የአፍሪካ አትሌቲክስ ልማት ማእከልን (AADC) የስራ እንቅስቃሴ፣ እንዲሁም የአፍሪካ አትሌቲክስ ኮንፌዴሬንን የውድድር መርሀ ግብር ለጉባኤው አቅርቦ አፈጻጸሙን ተመልክቷል።በማያያዝም የአየር ንብረትና ብክለት ጉዳይን እንዲሁም የሴቶች ኮሚቴ የጾታ ፖሊስን አስመልክቶ ገለፃ ያደረገ ሲሆን በቀጣይ አመት ኮንግረሱ የሚካሄድበትን አገር ምርጫም በማቅረብ አቅጣጫ ሰጥቷል።



ረዳት ኮሚሽነር ጄነራል ደራርቱ ቱሉ በሉሳካው ጉባዔ የአፍሪካን አትሌቲክስ በምክትል ፕሬዚዳንትነት እንድታገለግል ተመርጣለች፣

ዛምቢያ ጉባዔውን ያስተናገደችው የአፍሪካ የታዳጊና ወጣት አትሌቲክስ ቻምፒዮናን ከማስተናገዳ ማግስት ሲሆን በቻምፒዮናው ኢትዮጵያን የሚወክለው ቡድን ትናንት ማለዳ ወደ ዛምቢያ ተጉዟል።ከ18 እና ከ20 አመት በታች የአፍሪካ አትሌቲክስ ቻምፒዮና ከዛሬ ሚያዝያ 21 – 25/2015 ዓ.ም ጀምሮ ለ5 ተከታታይ ቀናት በዛምቢያ - ኒዶላ ከተማ ለ2ኛ ጊዜ ይካሄዳል።

በዚህ የአፍሪካ አትሌቲክስ ቻምፒዮና ላይ ኢትዮጵያን የሚወክለው የታዳጊና የወጣት ብሄራዊ ቡድን ውስጥ 15 ሴቶችና 15 ወንዶች በድምሩ 30 አትሌቶች እና 7 አሰልጣኞች፣ 1 ሐኪምና 1 ማሳጅ ባለሙያ ተካትተዋል።

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የውድድርና ተሳትፎ ዳይሬክተር አቶ አስፋው ዳኜ እና የፌዴሬሽኑ ጽህፈት ቤት ተወካይ አቶ ግርማ ለማ ቡድኑ ሲሸኝ በስፍራው ተገኝተው መልካም እድል በመመኘት አሸኛኘት አድርገዋል።


## የግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ

### የጨረታ ቁጥር፡ ኢኢግ/ሰቺማ/ግጨ/2015/008

ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ላፕቶፕ ኮምፒውተርና ኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

1) በጨረታው መሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች ማሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች፡-

1.1 የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ብር መጠን ብር 50,000.00

1.2 ተጫራቾች የግብር መክፈያ ግዴታቸውን የተወጡ መሆኑን የሚያረጋግጥና በግብር ሰብሳቢ ባለስልጣን የተሰጠ ማስረጃ ቅጂውን ማቅረብ የሚችሉ፡፡

1.3. አግባብ ያለው በዘመኑ የታደሰ የንግድ ስራ ፍቃድ ቅጂውን ከመጫረቻ ሰነድ ጋር ማቅረብ የሚችሉ፡፡

1.4 የተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገቡ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ቅጂውን ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

1.5 በመንግሥት መስሪያ ቤቶች በዕቃ አቅራቢነት በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የተመዘገቡበት የምዝገባ የምስክር ወረቀት (በድረ ገፅ ላይ መረጋገጥ የሚችል)፡፡

2) ተጫራቾች የመወዳደሪያ ሰነዱን ቴክኒካልና ፋይናንሽያል በተለያየ ፖስታ በማሸግ ገርጂ በሚገኘው ዋና መስሪያ ቤት (የቀድሞ ኢምፔሪያል ሆቴል ህንፃ) ግዢ ክፍል ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀው ሳጥን ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡

3) ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር 300.00 (ሦስት መቶ ብር) በኢትጵያ ንግድ ባንክ ሒሳብ ቁጥር 1000028606177 በኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ስም ገቢ በማድረግ ጨረታ ሰነድ መውሰድ ይችላሉ፡፡

4) ጨረታው ለተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ጊዜ ጨረታው በጋዜጣ ከወጣበት የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ ለ15 ተከታታይ ቀናት ይሆናል። ጨረታው በ16ኛው ቀን 4፡00 ሰዓት ተዘግቶ 4፡30 ይከፈታል፡፡

5) ግሩፑ ጨረታውን በከፊል ወይም በሙሉ የመሰረዝ መብት አለው።

**ተጨማሪ መረጃ ሲፈልጉ፡-ስልክ ቁጥር +251 114707741**

**ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ**



## የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

በፍ/ባለመብት ወ/ሮ አፀገነት ዘላለም እና በፍ/ባለዕዳ ዋና ሳጅን ሰለሞን መንግስቱ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 86862 በ13/5/2014 ዓ.ም እና መ/ቁ 84549 በ29/3/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 3 የቤ.ቁ 309 የሆነው ቤት ተከሳሽ ከሰሯቸው የግላቸው የሆኑት አራት ሰርቪስ ቤቶች ውጪ ያለው ከሟች ወ/ሮ ዘነበች እና አቶ መንግስቱ የወረሱት ቤቶች የሆነ በአጠቃላይ የቦታ ስፋት በካርታ ቁጥር 05/29/21019/00 የሆነ ስፋቱ 219 ካ/ሜ በጂ አይ ኤስ ላይ የሚታዩት 2 ቤቶች ሲሆን የቦታ ስፋት 24 ካ/ሜ መሆኑ ነገር ግን በአካል ተስፋፍተው 4 ክፍል የሆነው 85 ካ/ሜ ከሆነው ውጭ ያለው የፍርድ ያረፈበት የውርስ ሀብት ጂ አይ ኤስ ላይ ዋናው ቤት ብቻ የሚታይ ሲሆን የቦታ ስፋቱም 68 ካ/ሜ እና ጂ አይ ኤስ ላይ ከሚታየው ቤት ውጪ ያሉት ቤት 17 ካ/ሜ አጠቃላይ የውርስ ሀብት የተባሉት ቤቶች ስፋታቸው 85 ካ/ሜ ሆኖ የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 850,000 (ስምንት መቶ ሀምሳ ሺ ብር) ሆኖ የትራንዛክሽን ታክስ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ግንቦት 22 ቀን 2015 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል፡፡ የተጫራቾች ምዝገባ በ9፡00 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል፡፡

የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3፡30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፖርት ንብረቱን ለመጐብኘት የሚችሉ ሲሆን እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4 ኛውን በባንክ በተረጋገጠ C.P.O ማስያዝ ይኖርበታል፡፡ ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም፡፡ በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጐድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎችን ዳይሬክቶሬቱ የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍ/ቤት የፌዴራል ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት**